የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ፣
ወደ ፊልሞና

መግቢያ

ጸሓፊው፣ የተጻፈበት ጊዜና ቦታ

ጳውሎስ ይህን አጭር መልእክት የጻፈው የቄላስይስን መልእክት በጻፈበት ጊዜ ነው (በ60 ዓ.ም.፣ ቄላስይስ መግቢያ ላይ፣ "ጸሓፊው፣ የተጻፈበት ጊዜና ቦታ" የሚለውን ይመ)። ይህን መልእክት ወደ ቄላስይስ የላከው በአናሲሞስና በቲኪቆስ እጅ ነው። ጳውሎስ ሁለቱን መልእክቶች የጻፈው ኤፌሶን በነበረበት ጊዜ ነው የሚሉ ቢኖሩም (በፊልጵስዩስ መግቢያ ላይ፣ "ጸሓፊው፣ የተጻፈበት ጊዜና ቦታ" የሚለውን ይመ)፣ በሮም እስር ቤት እያለ መጻፉ ግን ግልጽ ነው።

ተደራሲው፣ ዳራውና ዐላማው

ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው፣ ከቄላስይስ ባሪያ አሳዳሪዎች አንዱ ለነበረውና ፊልሞና ለሚባል አማኝ ነው (ከቄላ4፥1 ጋር ያነጻጽሩ፤ የባሪያ ሥርዐት በአዲስ ኪዳን ምን እንደሚመስል የኤፌ6፥5 ማብ ይመ)። ከባሪያዎቹ አንዱ አናሲሞስ፣ ከጌታው ሳይሰርቅ አልቀረም (ከሥ18 ጋር ያነጻጽሩ) በዚሁ ምክንያት ከቤት ጠፍቶ የኰበለለ ይመስላል፤ በሮም ሕግ ይህ ዐይነት ወንጀል በሞት የሚያስቀጣ ነበር። አናሲሞስ ከጳውሎስ ጋር የመገናኘት ዕድል በማግኘቱ በእርሱ አገልግሎት ክርስቲያን ሆነ (ቊ10 ይመ)። ከዚህም የተነሣ አናሲሞስ ወደ ጌታው ሊመለስ ፈቃደኛ በመሆኑ እንደ ክርስቲያን ወንድም እንዲቀበለው ጳውሎስ ይህን የግል መልእክት በመጻፍ ፊልሞናን ይማጠነዋል (ቊ16 ይመ)።

አቀራረቡና ውቅሩ

አናሲሞስን ለመቀበል ፊልሞና ፈቃደኛ እንዲሆን ጳውሎስ በጥበብና በትሕትና መልእክቱን አለዝቦ ጽፎለታል (የቊ11 ማብ ይመ)። ለፊልሞና ያቀረበውን ልመና (ቊ4-21)፣ ጳውሎስ የጻፈው፣ የጥንት ግሪክና የሮም መምህራን ይህን ዐይነት ጽሑፍ የሚያዘጋጁበትን ዘዴ በመከተል ነው። ይህም የፍቅር ግኑኝነትን ለመመሥረት (4-10)፣ አስተሳሰብን ለመቀየርና (11-19) አንድን ሰው ለማሳመን (20-21) የሚጽፉበትን ዘዴ በመጠቀም ነበር። አናሲሞስ የሚለውን ስም የጠቀሰው፣ በእርሱና በፊልሞና መካከል ያለውን ፍቅርና ቅርርብ ከገለጠ በኋላ ሲሆን (ቊ10) ልመናውንም ያቀረበው በመልእክቱ መጨረሻ አካባቢ (ቊ17) ነው።

አስተዋፅኦ

1. ሰላምታ (1-3)
2. ምስጋናና ጸሎት (4-7)
3. ጳውሎስ ስለ አናሲሞስ ያቀረበው ልመና (8-21)
4. የመጨረሻ ጥያቄ፣ ሰላምታና ቡራኬ (22-25)

1 የክርስቶስ ኢየሱስ እስረኛ ከሆነ ጳውሎስና ከወንድማችን ከጢሞቴዎስ፥

ለውድ ወዳጃችንና አብሮን ለሚሠራው ለፊልሞና፣ 2ለእኅታችን ለአፍብያ፣ አብሮን ወታደር ለሆነው ለአርክጳና በቤትህም ላለችው ቤተ ክርስቲያን፥

3ከእግዚአብሔር ከአባታችን፣ ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

4አንተን በጸሎቴ በማስብህ ጊዜ ዘወትር አምላኬን አመሰግናለሁ፥ 5ምክንያቱም በጌታ በኢየሱስ ያለህን እምነትና ለቅዱሳንም ሁሉ ያለህን ፍቅር ሰምቻለሁ። 6በክርስቶስ ስላለን መልካም ነገር ሁሉ በሚገባ ትረዳ ዘንድ፣ እምነትህን ለሌሎች በማካፈል እንድትተጋ እጸልያለሁ። 7ወንድሜ ሆይ፥ የቅዱሳንን ልብ ስላሳረፍህ ከፍቅርህ ታላቅ ደስታና መጽናናት አግኝቻለሁ።

8ስለዚህ ማድረግ የሚገባህን እንድታደርግ አዝህ ዘንድ በክርስቶስ ድፍረት ቢኖረኝም 9በፍቅር እለምንሃለሁ፤ እንግዲህ ሽማግሌና አሁን ደግሞ የክርስቶስ ኢየሱስ እስረኛ የሆንሁት እኔ ጳውሎስ፣ 10በእስር እያለሁ ስለ ወለድሁት ልጄ ስለ አናሲሞስ እለ ምንሃለሁ። 11አስቀድሞ የሚጠቅምህ አልነበረም፤ አሁን ግን ለአንተም ሆነ ለእኔ የሚጠቅም ሰው ሆኖአል።

12የልቤ ሰው ያሆነውን እርሱን መልሼ ወደ አንተ ልኬዋለሁ። 13ስለ ወንጌል በታሰርሁበት ጊዜ በአንተ ፈንታ ሆኖ እንዲያገለግለኝ ለራሴ ላስቀረው ፈልጌ ነበር፤ 14ነገር ግን አንተ የምታደርገውን መልካም ነገር ሁሉ በውዴታ እንጂ በግዴታ እንዳይሆን ሳላማክርህ ምንም ማድረግ አልፈለግሁም። 15ምናልባት ለጥቂት ጊዜ ከአንተ የተለየው፣ ተቀብለህ ለዘለቄታው አንተ ዘንድ እንድታቈየው ነው፤ 16ከእንግዲህ ወዲህ ግን እንደ ባሪያ ሳይሆን ከባሪያ በላይ የሆነ ተወዳጅ ወንድም ነው። ለእኔ ተወዳጅ ነው፤ ለአንተ ግን በሥጋም በጌታም እንዴት ይበልጥ ተወዳጅ ነው!።

17እንግዲህ እንደ ባልንጀራ ከቈጠርኸኝ እኔን እንደምትቀበለኝ አድርገህ ተቀበለው። 18አንተን የበደለህ ነገር ቢኖር ወይም የአንተ ብድር ቢኖርበት በእኔ ላይ ቍጠረው። 19እኔ ጳውሎስ ይህን በእጄ ጽፌልሃለሁ፤ ያለበትን እኔው እከፍልሃለሁ። አንተም ራስህ የእኔ ስለ መሆንህ ምንም አልናገርም። 20ወንድሜ ሆይ፤ በጌታ እንድትጠቅመኝ እፈልጋለሁ፤ በክርስቶስ ልቤን አሳርፍልኝ። 21ታዛዥ መሆንህን በመተማመን፣ ከምጠይቀውም በላይ እንደምታደርግ በማወቅ እጽፍልሃለሁ።

22ከዚህም ሌላ፣ ጸሎታችሁ መልስ አግኝቶ ወደ እናንተ ለመምጣት ተስፋ ስለማደርግ ማረፊያ አዘጋጅልኝ።

23ከእኔ ጋር የክርስቶስ ኢየሱስ እስረኛ የሆነው ኤጳፍራ ሰላምታ ያቀርብልሃል፤ 24እንዲሁም አብረውኝ የሚሠሩት ማርቆስ፣ አርስጥሮኮስ፣ ዴማስና ሉቃስ ሰላምታ ያቀርቡልሃል።

25የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን።

ᵍ10 አናሲሞስ ማለት የሚጠቅም ማለት ነው

1-2፤ ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው ለማለሰብ በመሆኑና መልእክቱም በጣም ግላዊ ስለሆነ፣ "እኛ" ወይም፣ "እናንተ" የሚለውን ሳይሆን "እኔ" የሚለውን ተውላጠ ስም ይጠ ቀማል። ጳውሎስ "እኛ" እና "እናንተ" የሚሉትን ተውላጠ ስሞች የሚጠቀመው በቍጥር 22 እና 25 ላይ ብቻ ነው።

1 *አስረኛ፤* የኤፌ 3፥1 እና የፊል1፥13 ማብ ይመ። *ጢሞ ቴዎስ፤* የቈላ1፥1 ማብ ይመ። *ፊልሞና፤* በቈላስይስ ከተማ ወይም በአካባቢዋ ይኖር የነበረ ክርስቲያን እንዲሁም የአናሲሞስ አሳዳሪ ጌታ የነበረ ሰው ነው።

2 *ለፍብያ፤* የፊልሞና ሚስት ልትሆን ትችላለች። *አርክጳ፤* ቈላ4፥17 ይመ።

4 *አንተን በጸሎቴ በማስብህ ጊዜ...አመሰግናለሁ፤* የፊል1፥3-4 ማብ ይመ።

5፤ ከቈላ1፥4 *ጋር* የሚነጻጸር ሲሆን፣ "በጌታ ኢየሱስ ያለህን እምነትና ለቅዱሳንም ሁሉ ስላለህ ፍቅር ሰምቻለሁ" የሚለው ዐረፍተ ነገር የግሪኩ አወቃቀር "ኬይዝም" በመባል የሚታወቀውን ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ የተከተለ ነው። "ኬይዝም" የሚለው ቃል የመጣው ካይ ከሚለው የግሪክ ፊደል ነው (X)።

እምነት ፍቅር

ለቅዱሳን በጌታ በኢየሱስ

7 *ልብ፤* የግሪኩ ቃል በቃል ሲተረጐም፣ "አንጀት" የሚል ፍቺ አለው፤ በግሪኮች ምሳሌያዊ አነጋገር "አንጀት" የአዘኔታና የፍቅር መግለጫ ነው።

10 *ለናሲሞስ፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ፤ ከጌታው ከፊልሞና የኰበለለው አናሲሞስ ወደ ክርስትና የመጣው በሐ ዋርያው ጳውሎስ አማካይነት ነው (መግቢያውን ይመ)። *ልጄ፤* የ1ጢሞ 1፥2 ማብ ይመ።

11 *የሚጠቅምህ አልነበረም...ጠቃሚ ሆኖአል፤* በአናሲሞስ የስም ትርጕም ላይ የተደረገ ጎብር አገላለጽ ነው (የቍ10 ማብ ይመ)።

11-19፤ ሉተር ይህን ክፍል፣ "ክርስቶስ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ እንዳደረገልን ሁሉ ጳውሎስም በፊልሞና ዘንድ ለአናሲሞስ እንደዚሁ አድርጎለታል" ሲል ይገልጸዋል።

20 *እንድትጠቅመኝ፤* የዚሁ ቃል በግሪኩ ሲታይ በአናሲሞስ ስም ላይ የተደረገ ጎብር አገላለጽ ነው።

22 *ከዚህም ሌላ፤* በጥንት ደብዳቤ አጻጻፍ ከዋናው ርእሰ ጕዳይ በተጨማሪ ሌላ ነገር ማውሳት የተለመደ ነው። እዚህም ላይ እንደምንመለከተው ብዙውን ጊዜ ተጨማሪው ነገር ጸሓፊውና ተቀባዩ እንዴትና መቼ መገናኘት እንደሚችሉ የሚያመላ ነው።

23 *ኤጳፍራ፤* ቈላ 4፥12 ይመ።

24 *ማርቆስ፤ አርስጥሮኮስ፤* የቈላ 4፥10 ማብ ይመ። *ዴማስና ሉቃስ፤* የቈላ 4፥14 ማብ ይመ።

ወደ ዕብራውያን የተጻፈ መልእክት

ጸሓፊው

የዚህ መልእክት ጸሓፊ፣ ማንኑቱን አልገለጠም፤ ሆኖም ግን በመጀመሪያዎቹ የመልእክቱ ተደራሲያን ዘንድ የታወቀ ነው፤ መጽሐፉ ለ1200 ዓመታት ያህል (ከ400-1600 ዓ.ም.)፣ "በተለምዶ የጳውሎስ መልእክት ወደ ዕብራውያን" በመባል የሚታወቅ ቢሆንም በመጀመሪያዎቹ ምእተ ዓመ ታት ግን ተቀባይነት አላገኘም ነበር። ከቤተ ክርስቲያን ዘመነ ተሐድሶ ወዲህ፣ ጳውሎስ የመልእክቱ ጸሓፊ እንዳልሆነ ይታሰባል። የዕብራውያን መልእክትና የጳውሎስ መልእክቶች በሚያስተላልፉት ትምህርቶች መካከል አለመጣጣም አይታይም፤ ነገር ግን በልዩ ሁኔታ አጽንዖት በሚያደርጉባቸው ጉዳዮችና በአጻጻፍ ስልታቸው መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ። ጳውሎስ በጻፋቸው መልእክቶች ውስጥ ስሙን ይገልጻል፤ የዕብራውያን መልእክት ጸሓፊ ጸታው ወንድ መሆኑን ከመግለጹ በስተቀር ማን እንደሆነ በየትም ስፍራ አላመለከተም (የ11፥32 ማብ ይመ)። በተጨማሪም፣ "ይህ ድነት በመጀመሪያ በጌታ ተነገረ፤ ከእርሱም የሰሙትም ለእኛ አረጋገጡ ልን።" (2፥3) የሚለው አረፍተ ነገር፣ ኢየሱስ በምድር ሲያገለግል የመልእክቱ ጸሓፊ ከእርሱ ጋር እንዳልነበረ፣ እንደ ጳውሎስም ከሞት ከተነሣው ጌታ ልዩ መገለጥን በቀጥታ እንዳልተቀበለ (ገላ1፥11-12) ያመለክታል የሚሉ አሉ።

የዕብራውያንን መልእክት ጸሓፊ በተመለከተ፣ የመጀመሪያው አስተያየት የተገኘው "20 ዲ ፕዲሲሺያ" (200 ዓ. ም.) በተባለው የጠርጡሊያኖስ ጽሑፍ ውስጥ ነበር፤ እርሱም በዚህ መጽሐፉ ውስጥ "በበርናባስ ስም ከተጻፈው፣ የዕብራውያን መልእክት" በማለት ጠቅሶ ጽፎአል። የዕብራ ውያን መልእክት በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥልጣን ያለው፣ የብሉይ ኪዳን ሊቅ፣ እንዲ ሁም ዕብራዊ ክርስቲያን መሆኑን መልእክቱ ያስረዳል። በርናባስም የተጠቀሱትን እነዚህን ሁኔታዎች የሚያሟላ ነበር፤ እርሱም አይሁዳዊ፣ ከካህናት ወገን የሆነ ሌዋዊ (ሐዋ4፥36) ነው። ጳውሎስ ከተለወጠ በኋላም የእርሱ የቅርብ ጓደኛ ነበር። የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በርናባስንና ጳውሎስን ለወንጌል ሥራ ለይታ በመጀመሪያው የወንጌል ጉዞ ላከቻቸው (ሐሥ 13፥1-4)። የዕብራውያንን መልእክት ሳይጽፍ አይቀርም ተብሎ ትልቅ ግምት የሚሰጠው ሌላው ሰው ደግሞ፣ አጵሎስ ነው። አጵሎስ የዚህ መልእክት ጸሓፊ እንደሆነ በመጀመሪያ የተነገረው በማርቲን ሉተር ሲሆን፣ ብዙ ምሁራንም ይደግፉታል። አጵሎስ የእስክንድሪያ ተወላጅ ሲሆን፣ በዕውቀቱና በንግግር ችሎታው፣ የታወቀ አይሁዳዊ ክርስቲያን ነበር። የተማረና ቅዱሳት መጻሕፍትን ጠንቅቆ የሚያውቅ እንደነበርም ሉቃስ ጽፎአል (ሐሥ18፥24)። በቆሮንቶስ የወንጌል ሥራ ሲጀመር፣ አጵሎስ የጳውሎስ የሥራ ባልደረባ እንደነበረም እናውቃለን (1ቆሮ1፥12፤3፥4-6:22)።

መልእክቱ የተጻፈበት ጊዜና ቦታ

የዕብራውያን መልእክት የተጻፈው፣ የኢየሩሳሌም ከተማና ቤተመቅደሱ በ70 ዓ.ም. ከመደምሰሳቸው በፊት መሆን አለበት፤ ምክንያቱም:- (1) ከተጠቀሰው ዘመን በኋላ ተጽፎ ቢሆን ኖሮ፣ ጸሓፊው የቤተመቅደሱን መፍረስና የአይሁድን የመሥዋዕት ሥርዐት እንደ ቆመ በጠቀሰ ነበር (2) ጸሓፊው ስለቤተ መቅደሱና በቤተ መቅደሱ ውስጥ ይፈጸም ስለ ነበረው የካህናት አገልግሎት ሲናገር፣ በግሪክ ቋንቋ የቅርብ ጊዜን አመልካችን ተጠቅሞአል (5፥1-3፤7፥23:27፤8፥3-5፤9፥6-9:13:25፤10፥1:3-4:8:11፤13፥10-11 ይመ)።

የመልእክቱ ተደራሲያን

መልእክቱ በመጀመሪያ የተጻፈው፣ ብሉይ ኪዳንን ጠንቅቀው ለሚያውቁ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች ሲሆን፣ ይኸውም ወደ ይሁዲነት በመሳብ ላይ ለነበሩ ወይም ወንጌልን ከአይሁድ እምነት ጋር ለመቀላቀል (ከገላ 2፥14 ጋር ያነጻጽሩ) ይጥሩ ለነበሩ ምእመናን ነው። እነዚህ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች፣ በሙት ባሕር አጠገብ በሚገኘው ቁምራን በተባለ ስፍራ ከነበረው አንድ የአይሁድ ሃይማኖት ክፍል ጋር ለመደባለቅ ፍላጎት እንደነበራቸው የሚናገሩም አሉ። እንዲ ሁም፣ የዚህ መልእክት ተቀባዮችን አስመልክቶ፣ ለእምነት ታዛዥ ከሆኑት አያሌ ካህናት መካከል የነበሩ ሰዎች (ሐሥ6፥7) ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚናገሩም አሉ።

የመልእክቱ መሪ ሐሳብ

የዕብራውያን መልእክት መሪ ሐሳብ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመግለጥና በእርሱም በኩል ይህ ጸጋ ወደ ሰው እንዲደርስ፣ ፍጹም ወደር የማይገኝለት ብቃት ያለው መሆኑን ለማሳየት ነው። የመልእክቱ መግቢያ (1፥1-4)፣ ክርስቶስን እንከን የሌለበትና ከሁሉ የላቀ የእግዚ አብሔር መገለጥ አድርጎ አቅርቦታል። እርሱ ቀደም ሲል በብሉይ ኪዳን ተሰጥቶ ከነበረው መገለጥ ጋር ሲነጻጸር እጅግ የሚበልጥ ነው። በብሉይ ኪዳን የተነገሩት ትንቢቶችና የተስፋ ቃሎች የተፈጸሙት ክርስቶስ መካከለኛ በሆነበት በአዲስ ኪዳን ነው። ክርስቶስ፣ በብሉይ ኪዳን ከነበሩት ከነቢያት፣ ከመላእክት፣ የአሮጌው ኪዳን መካከለኛ ከነበረው ከሙሴ፣ ከአሮንና ከእርሱ

ዘር ከሆኑት ካህናት ሁሉ የላቀ መሆኑ በግልጽ ተጠቅሶአል። በዚህ መልእክት ውስጥ "የተሻለ" እና "የላቀ" ለሚሉት ቃላት አቻ የሆኑ ሁለቱ የግሪክ ቃላት ዐሥራ አምስት ጊዜ ስለ ተጠቀሱ፣ መልእክቱ "የተሻለ ነገር መጽሐፍ" ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

ይህ መሪ ሐሳብ፣ በአማኝ ሕይወት እንዴት ተግባራዊ ሊሆን እንደሚገባው በመጽሐፉ ውስጥ በስፋት ተገልጸአል። አሮጌው የአይሁድ ሥርዐት፣ ልዩ በሆነ የክርስቶስ ክህነት ስለ ተተካ፣ ወደዚያ መመለስ ወይም በዚያ ሥርዐት መቀጠል፣ ከቶ ሊታሰብ እንደማይችል ለአንባቢው ተገልጸአል። ከእንግዲህ የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ እውነተኛ ወደ ሆነው ወደ ሰማያዊው የእግዚአብሔር መቅደስ፣ መግቢያ ስርየት ወዳገኘበት ወደ ኢየሱስ ሞት፣ ትንሣኤና ዕርገት ብቻ መመልከት ይኖርበታል። አማኞች ወደኋላ እንዲያፈገፍጉ የሚታገላቸውን ፈተና በመቋቋም፣ የጀመሩትን መንፈሳዊ ውጊያ ጸንተው መቀጠል አለባቸው፤ አለበለዚያ፣ በምድረ በዳ የነበረው ዐመፀኛው የእስራኤል ሕዝብ የደረሰበት ዐይነት ቅጣት ሊደርስባቸው ይችላል።

አስተዋፅኦ

(1) *መግቢያ*፦ የእግዚአብሔር አዲስ መገለጥ የበላይነት (1፥1-4)
(2) ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን መሪዎች የላቀ መሆኑ (1፥5-7፥28)
  ሀ. ክርስቶስ ከመላእክት የላቀ ነው(1፥5-2፥18)
    1. እንዴት እንደላቀም፣ የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃ (1፥5-14)
    2. እግዚአብሔር በልጁ በኩል ራሱን መግለጡን ቸል እንዳይሉ የተሰጠ ምክር (2፥1-4)
    3. ከመላእክት እንደሚልቅ የቅዱሳት መጻሕፍት ተጨማሪ ማስረጃ (2፥5-18)
  ለ. ክርስቶስ ከሙሴ የላቀ ነው(3፥1-4፥13)
    1. ክርስቶስ እንዴት እንደላቀ ማስረጃ (3፥1-6)
    2. ወደ ድነት ዕረፍት ስለ መግባት የተሰጠ ምክር (3፥7-4፥13)
  ሐ. ክርስቶስ ከአሮናዊ ክህነት የላቀ ነው(4፥14-7፥28)
    1. በያዙት እምነት እንዲጸኑ የተሰጠ ምክር (4፥14-16)
    2. የካህን *መመዘኛ* (5፥1-10)
    3. ከመንፈሳዊ ድካም እንዲበረቱ የተሰጠ ምክር (5፥11-6፥12)
    4. የእግዚአብሔር ተስፋ እርግጠኝነት (6፥13-20)
    5. የክርስቶስ ክህነት የላቀ ስለመሆኑ (ም7)
(3) የሊቀ ካህናችን የላቀ የመሥዋዕትነት ሥራ (ም8-10)
  ሀ. የተሻለ ኪዳን (ም8)
  ለ. የተሻለ መቅደስ (9፥1-12)
  ሐ. የተሻለ መሥዋዕት (9፥13-10፥18)
  መ. ልዩ ልዩ ምክር (10፥19-39)
(4) በእምነት ስለ መጽናት የቀረበ የመጨረሻ ልመና (ም11-12)
  ሀ. የቀድሞ የእምነት አርበኞች ምሳሌነት (ም11)
  ለ. በእምነት ስለ መጽናት የተሠጠ ማበረታቻ (12፥1-11)
  ሐ. በእምነት ለመጽናት የተሠጠ ምክር (12፥12-17)
  መ. በእምነት ለመጽናት መነሣሣት (12፥18-29)
(5) *ማጠቃለያ* (ም13)
  ሀ. ስለ ክርስቲያናዊ ኑሮ የተሰጠ ተግባራዊ *መመሪያ* (13፥1-17)
  ለ. የጸሎት ጥያቄ (13፥18-19)
  ሐ. ቡራኬ (13፥20-21)
  መ. የግል አስተያየት (13፥22-23)
  ሠ. ሰላምታና የመጨረሻ ቡራኬ (13፥24-25)

ልጁ ከመላእክት በላይ ነው

1 እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በተለያየ ጊዜና በልዩ ልዩ መንገድ በነቢያት በኩል ለአባ
ቶቻችን ተናግሮ፣ 2በዚህ መጨረሻ ዘመን
ግን ሁሉን ወራሽ ባደረገውና ዓለማትን
በፈጠረበት በልጁ ለእኛ ተናገረን። 3እርሱ
የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅና የባሕርዩ ትክ
ክለኛ ምሳሌ ሆኖ፣ ቡኒያል ቃሉ ሁሉን
ደግፎ ይዞአል፤ የኀጢአት መንጻት ካስገኘ
በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ።
4ስለዚህ የወረሰው ስም ከመላእክት ስም
እንደሚበልጥ ሁሉ፣ እርሱም ከመላእክት
እጅግ የላቀ ሆኖአል።

5እግዚአብሔር፣
"አንተ ልጄ ነህ፤
እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ፤"[ሠ]

ወይስ ደግሞ፥
"እኔ አባት እሆነዋለሁ፤
እርሱም ልጅ ይሆነኛል" ያለው ከመላ
እክት ከቶ ለማን ነው?

1፥1 ዘኍ12፥6፡8፤ ሉቃ1፥70፡ሥራ9፥29፤ ሥሥ2፥30፡ዕብ2፡2፡ 3፤4፡11፡2፥25
1፥2 ቈላ1፡16፤ ዘዳ4፥30፡ መዝ2፥8፡ማቴ3፥17፤ 11፥27፡ 28፡18፤ ሐ1፡3፤ ዕብ3፥6፡5፥8፡7፥28፤ 9፥26፡11፥3፡ራእ1፥20
1፥3 ግሮ16፥19፤ ዮሐ1፥14፡1፡4፥9፤ ቈላ1፥17፡ቲቶ2፥14፤ ዕብ7፥27፡9፥11-14
1፥4 ኤፌ1፥21፤ ፊል2፥9፡10፡ዕብ8፥6
1፥5 2ሳሙ7፥14፤ መዝ2፥7፡ማቴ3፥17

1፥6 ዘዳ32፥43፤ መዝ97፥7፡ዮሐ3፥16፤ ቈላ1፥18፡ዕብ10፥5
1፥7 መዝ104፥4
1፥8 ሉቃ1፥35
1፥9 ኢሳ61፥1፡3፤ መዝ45፥6፡7፤ፊል2፥9
1፥10 መዝ8፥6፤ ዘፍ1፡2፥1

6ደግሞም እግዚአብሔር በኵሩን ወደ ዓለም
ሲያስገባ፣
"የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ ይስገዱለት"
ይላል።

7ስለ መላእክትም ሲናገር፣
"መላእክቱን ነፋሳት፣
አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል ያደርጋል"
ይላል።

8ስለ ልጁ ግን እንዲህ ይላል፤
"አምላክ ሆይ፤ ዙፋንህ ከዘላለም እስከ
ዘላለም ጸንቶ ይኖራል፤
ጽድቅም የመንግሥትህ በትር ይሆናል፥
9ጽድቅን ወደድህ፤ ዐመፃን ጠላህ፤
ስለዚህ እግዚአብሔር ስምሃክህ ከባልንጀ
ሮችህ በላይ አስቀመጠህ፣
የደስታንም ዘይት ቀባህ

10ደግሞም እንዲህ ይላል፤ "ጌታ ሆይ፥ አንተ
በመጀመሪያ የምድርን መሠረት አኖርህ፥

[ሠ]5 ወይም እኔ ዛሬ አባት ሆንሃህ
[ሰ]6 የሙት ባሕር ጥቅልሎችንና ሰብዓ ሊቃናትን ይመ

1፥1 *ከጥንት ጀምሮ*፡ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ከመምጣቱ በፊት ያለውን ጊዜ የሚያመለክት ሲሆን፣ "በዚህ መጨረሻ ዘመን" (ቍ 2) ከሚለው ጋር የሚነጻጸር ነው፤ የመሲሑ ዘመን የተጀመረውም ሰው ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ነው (የሐሥ 2፥17፤ 1ጢሞ4፥1፤1ዮሐ2፥18 ማብ ይመ::) *እግዚአብሔር ... ተናግሮ፤* "ተናገረን" ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ (ቍ 2)። የብሉይም ሆነ የአዲስ ኪዳን ምንጭ እግዚአብሔር ነው። *ለአባቶቻችን* "ለእኛ" (ቍ 2) ጋር ያነጻጽሩ። *በነቢያት* በኩል፤ የብሉይ ኪዳን ጸሓፊዎች ሁሉ ምስክርነታቸው የመሲሑን መምጣት የሚያሳይ ስለ ነበር፣ እዚህ ላይ እንደ ነቢያት ተቁጥረዋል፤ "በልጁ" ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ (ቍ 2)፤ ይህም ከነቢያት ጋር ሲነጻጸር በዐይነቱ አዲስና ልዩ የሆነ መገለጥ ነው። *በተለያየ ጊዜና በልዩ ልዩ መንገድ*፡ የብሉይ ኪዳን መገለጥ ከፊል ግለትም ሙሉነትና ፍጹምነት የሚጐለው ነው።

1፥2-3 በልጁ የመጣው መገለጥ የላቀ መሆኑን ለማሳየት ስለ ልጁ ሰባት ታላላቅ ነገሮች ተናግሮናል። (1) *ሁሉን ወራሽ ባደረገውና* ሥጋ የለበሰው ልጁ፣ የማዳን ሥራውን ከፈጸመ በኋላ የእግዚአብሔር በኵር ወራሽ ወደ ሚቀመጥበት ክብር ከፍ ከፍ አለ፤ ማለትም የእግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ ርስት አድርጎ ተቀበለ ሮሜ 8፥17 ይመ። (2) *ዓለማትን በፈጠረበት*፡ ዮሐ 1፥3፤ ቈላ 1፥16 ይመ። (3)*የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅና* የፀሐይ ብርሃን ከራሷ ከፀሐይ ሊለይ እንደማይችል ሁሉ፣ የልጁ ም ነጸብራቅ እንዲሁ ከመለኮት ሊለይ አይችልም፤ ምክንያቱም እርሱ ራሱ አምላክና ከሥላሴ አካላት አንዱ ነው (ዮሐ 1፥14፤ 18)። (4)*የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ*፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔር አምሳል ወይም ነጸብራቅ ብቻ አይደለም፤ ልጁ ራሱ አምላክ ስለሆነ የእግዚአብሔር ህላዌ ትክክለኛ መልክ ነው። (ዘፍ ሐ 14፥9፤ ከቈላ 1፥15 *ጋር ያነጻጽሩ*)። (5) *ሁሉን ደግፎ ይዞአል*፤ ክርስቶስ ዓለምን በትክሻው እንደተሸከመው እንደ ግሪኩ አምላክ አንደ አትላስ አይደለም። ልጁ በእርሱ አማካይነት የተፈጠረውን ሁሉ (ቈላ 1፥17) በሥርዐት እንዲመራ አገባጥሞ ይዞታል። (6) *የኀጢአት መንጻት ካስገኘ በኋላ*፤ መንጻትን ያስገኘው በመስቀል ላይ በፈጸመው ቤዛነት ነው። (7)*በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ*፤ በእግዚአብሔር ቀኝ መቀመጡ የቤዛነት ሥራው የተፈጸመ መሆኑንና ክርስቶስ አሁን ከእግዚአብሔር ጋር በሁሉ ላይ ጌታ ሆኖ እንደሚገዛ *ያመለክታል* (ሮሜ13፡8፡1፡10፡12፡ዘዳ12፥2፡ ኤፌ1፥20፤ ቈላ3፡1፡1ጴጥ3፥22 ይመ እንዲሁም የግር 16፥19 ማብ ይመ)።

1፥4 *ከመላእክት ይጅግ የላቀ*፤ ለብዙ አይሁዳውያን መላእክት ከፍ ያሉ ፍጡራን ናቸው፣ አይሁድ ለመላእክት ከፍ ያለ ቦታ የሚሰጡት፣ የእግዚአብሔር ታላቅ መገለጥ አድርገው የሚቈጥሩት ሕግ በሲና ተራራ ላይ ሲሰጥ (የ2፥2 ማብ ይመ) መላእክትም በነገሩ ስለነበሩበት ነው። የሙት ባሕር ጥቅልሎች እንደሚያመለክቱት፣ የመላእክት አለቃ የሆነው ሚካኤል በመሲሑ መንግሥት ትልቅ ስፍራ ይኖረዋል። የዕብራውያን መልእክት ተደራሲዎች ከክርስቶስ (ከመሲሑ) ይልቅ ለመላእክት ከፍ ያለ ስፍራ ይሰጡ ወይም አይሰጡ የሚታወቅ ነገር የለም። *ስም*፤ በአይሁድ ግንዛቤ ሰብ ዘንድ ስም የአንድን ሰው ባሕርይና ተግባር የሚወክል ነው (የዘፍ 17፥5 ማብ ይመ)። ከዚህ ቀጥሉ ያለው ክፍል እንደሚያመለክተው ይህ ስም "ልጅ" የሚለው ነው፤ አንድም መልአክ ይህን ስም ለራሱ ሊጠቀም አይችልም።

1፥5-14፤ ክርስቶስ ከመላእክት በላይ ነው የሚለው ጽኑ ሐሳብ፣ ከብሉይ ኪዳን በተወሰዱ ሰባት ጥቅሶች ተደግፎአል (መዝ2፥7፤2ሳሙ7፥14፤1ዜና17፥13፤ዘዳ32፥43፤መዝ104፥4፤ መዝ45፥6፡7፤መዝ102፥25-27፤መዝ110፥1 ይመ)፤ እነዚህም ጥቅሶች ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ፣ መላእክት የሚሰግዱለትና እንደ አብ እርሱም አምላክ ቢሆንም፣ ከአብ ግን የተለየ መሆኑን ያሳያሉ።

1፥5 *አንተ ልጄ ነህ፣ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ*፤ ይህ ጥቅስ (መዝ 2፥7) ክርስቶስ ከሙታን በተነሣ ጊዜ መፈጸሙን ለማሳየት በሐሥ 13፥33 ላይ ተጠቅሶአል (ከሮሜ 1፥4 *ጋር ያነጻጽሩ*)። *እኔ አባት እሆነዋለሁ፣ እርሱም ልጅ ይሆነኛል*፤ አይሁድ 2ሳሙ 7፥14 (ይህ ጥቅስ የተወሰደው ከዚህ ክፍል ነው) እና መዝ 2 የሚመጣውን መሲሕ የሚያመለክቱ ናቸው ብለው ያምናሉ (ሉቃ 1፥32-33 ይመ)። ይህ ከዳዊት ቤት የሚወጣው ንጉሥ፣ መልአክ ወይም የመላእክት አለቃ አይደለም፤ ነገር ግን እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው።

1፥6 *በኵሩን*፡ የቈላ 1፥15 ማብ ይመ። *የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ ይሰገዱለት*፤ ይህ ጥቅስ የተወሰደው ከመዝ 97፥7 ሳይሆን አይቀርም። በብሉይ ኪዳን ጌታ እግዚአብሔርን የሚያመለክተው ይህ ዐረፍተ ነገር እዚህ ላይ ክርስቶስን አመል ክቷል። ይህም ክርስቶስ ፍጹም አምላክ እንደሆነ በግልጽ ያሳያል። ከክርስቶስ ጋር የተነጻጸሩት እነዚህ መላእክት ለእርሱ በመስገድ ልዕልናውን እንዲያውቁ ታዘዋል።

1፥7 *መላእክቱን ነፋሳት፣ አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል ያደርጋል*፤ መዝ 104፥14፤ ጎይለኛው ነፋስና መብረቅ የእግዚብሔርን ፈቃድ የሚፈጽሙ መልእክተኞች እንደሆኑ ይናገራል። የዕብራውያን መልእክት ጸሓፊ ጥቅሶቹን የወሰደው ተደራሲዎቹ በሚገባ ከሚያውቁት ከሰብዓ ሊቃናት ትርጕም (ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ቋንቋ የተመለሰው) ሲሆን፣ በብሉይ ኪዳ ንና በአዲስ ኪዳን መካከል ባሉት ዘመናት ስለ መላእክት የሚ ሰጠው አስተምህሮ እያደገ እንደመጣ ያመለክታል።

1፥8 *ስለ ልጁ ግን እንዲህ ይላል፤ አምላክ ሆይ፣ ዙፋንህ ከዘላለም እስከ ዘላለም ጸንቶ ይኖራል*፤ የመልእክቱ ጸሓፊ መሲሐዊው (ከዳዊት ወገን) የሆነው ንጉሥ አምላክ እንደሆነ የሚያሳዩ ክፍሎችን እየመረጠ ጠቅሷል፤ ይህም ልጁ ከመላእክት በላይ መሆኑን ይበልጥ የሚገልፅ ነው።

1፥10 *ጌታ ሆይ፣ አንተ በመጀመሪያ የምድርን መሠረት አኖርህ*፤ በቍጥር 6 እንደ ተመለከተው ሁሉ እዚህም ላይ ያህዌን የሚያመለክተው "ጌታ ሆይ" የሚለው ሐረግ ለልጁ መጠሪያ ሆኖአል።

ሰማያትም የእጆችህ ሥራ ናቸው።
11እነርሱ ይጠፋሉ፥ አንተ ግን ጸንተህ ትኖ
ራለህ፤
ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ፥
12እንደ መጐናጸፊያ ትጠቀልላቸዋለህ፥
እንደ ልብስም ይለወጣሉ።
አንተ ግን ያው አንተ ነህ፤
ዘመንህም ፍጻሜ የለውም።"
13ከመላእክቱ፣
"ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስከማድረግ
ልህ ድረስ፣
በቀኜ ተቀመጥ" ያለው ከመላእክት ከቶ ለማን
ነው?
14መላእክት ሁሉ መዳንን የሚወርሱትን ለማ
ገልገል የሚላኩ አገልጋይ መናፍስት አይ
ደሉምን?

ትኵረት የሚያስፈልጋቸው ነገሮች

2 ስለዚህ ከሰማነው ነገር ስተን እንዳንወ
ድቅ፣ ለሰማነው ነገር አብልጠን ልንጠ
ነቀቅ ይገባናል። 2ምክንያቱም በመላእክት
በኩል የተነገረው ቃል ጽኑ ከሆነና ማንኛ
ውም መተላለፍና አለመታዘዝ ተገቢውን
ቅጣት ከተቀበለ፣ 3እኛስ እንዲህ ያለውን
ታላቅ ድኅነት ቸል ብንል እንዴት ልናመልጥ
እንችላለን? ይህ ድኅነት በመጀመሪያ በጌታ
ተነገረ፣ ከእርሱ የሰሙትም ለእኛ አረጋገጡልን።
4እግዚአብሔርም በምልክት፣ በድንቅና በልዩ
ልዩ ታምራት እንዲሁም እንደ ፈቃዱ
በታደሉት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች
ስለዚሁ ነገር መስክሮአል።

ኢየሱስ ወንድሞቹን መሰለ

5ይሆን የምንናገርለትን መጪውን ዓለም
ለመላእክት አላስገዛም፤ 6ነገር ግን አንዱ
በሌላ ስፍራ እንዲህ ብሎ መስክሮአል፥
"ታስቧታውሰው ዘንድ ሰው ምንድን ነው?
ታስብለትስ ዘንድ የሰው ልጅ ምንድን ነው"
7ከመላእክት ጥቂት አሳነስኸው፤
የክብርና የምስጋና ዘውድ ጫንህለት፥
8ሁሉንም ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት።
እግዚአብሔር ሁሉን ከበታቹ ሲያስገዛለት፣ ያላ
ስገዛለት ምንም ነገር የለም፤ ይሁን እንጂ
በአሁኑ ጊዜ ሁሉም ነገር ተገዝቶለት አና
ይም። 9ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ስለ ሰው
ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ ከመላእክት ጥቂት
እንዲያንስ ተደርጎ የነበረው ኢየሱስ፣ የሞ
ትን መከራ በመቀበሉ አሁን የክብርና
የምስጋና ዘውድ ተጭኖለት እናየዋለን።
10ሁሉ ነገር ለእርሱና በእርሱ የሚኖር
እግዚአብሔር፣ ብዙ ልጆችን ወደ ክብር ለማ
ምጣት፣ የድኅነታቸውን መሥራች በመከራ
ፍጹም ሊያደርገው የተገባ ነበር።
11ወይም ለተቂት ጊዜ

1፥11 ኢሳ34፥4፤ 51፥6፤ዕብ12፥27
1፥12 መዝ102፥25-27፤ ዕብ13፥8
1፥13 ቀ3ሁሉ፤ዕብ10፥24፤ መዝ110፥1፤ ማቴ22፥44፤ ማር16፥19፤ሐዋ10፥13
1፥14 ዳን7፥10፤ መዝ91፥11፤103፥20፤ ማቴ25፥34፤ ማር10፥17፤ ሐሥ20፥32 ሮሜ11፥14፤ ዕብ2፥3፤5፥9፤9፥28
2፥1 ሮሜ11፥22
2፥2 ዘጸ33፥2፤ ሐሥ7፥53፤ገላ3፥19፤ ዕብ1፥1
2፥3 ሉቃ1፥2፤ ዕብ1፥2፤10፥29
2፥4 ማር16፥20፤ ዮሐ4፡48፤ሐዋ12፥4፤ ኤፌ1፥5
2፥6 ኢዮ7፥17፤ መዝ144፥3፤ዕብ1፥4
2፥8 መዝ8፥4-6፤ ማቴ22፥44
2፥9 ቀ7ፍሐሥ3፥13፤ 2ቆሮ5፥15፤ፊሊ2፥7-9
2፥10 ሉቃ24፥26፤ ሮሜ11፥16፤ዕብ5፥8፤ 9፥7፣28

1፥13 *በቀኜ ተቀመጥ* የቍ 2-3 ማብ ይመ። በዕብራ ውያን መልእክት ውስጥ መዝ 110 ከኢየሱስ ጋር ተያይዞ ብዙ ጊዜ ተጠ ቅሷል (ቍ3፥1፤5፥6፤10፥6፥20፤7፥3፤11፤17፤21፤8፥1፤10፥12-13፤ 12፥2)።

1፥14 *አገልጋይ መናፍስት* ክርስቶስ ነገሥአል፣ መላእክት ግን ለማገልገል የሚላኩ ናቸው።

2፥1-4 በመልዕክቱ ውስጥ ቍልፍ ቦታ ከያዙት አምስት የማስጠንቀቂያ ክፍሎች መካከል የመጀመሪያው ነው (3፥7-4፥13፤5፥11-6፥12፤10፥19-39፤12፥14-29 ይመ)።

2፥1 *ከሰማነው ነገር* ክርስቶስ አምላክና ሰው መሆኑን እንዲሁም በመስቀል ላይ የፈጸመውን ቤዛነት ጨምሮ የወንጌን መልእክት የሚያሳይ ነው። *እንዳንወድቅ* በልጽ አማካይነት ከተሰጠው ታላቅ መገለጥ እንዳንጐድል ነው።

2፥2 *በመላእክት በኩል የተነገረው ቃል* በሲና ተራራ ላይ ለሙሴ የተሰጠው ሕግ ነው። ሕጉ በተሰጠበት ጊዜ፣ መላ እክት ንቁ ተሳትፎ አድርገው እንደ ነበር በዘዳ32፥2 ላይ ተጠቅሶ አል። "እልፍ አእላፍ" መዝ 68፥17፤የሐሥ7፥38፤ 53፤ገላ 3፥19።

2፥3 *እንዲህ ያለውን ታላቅ ድኅነት* እዚህ ላይ የመከራ ከፈያው ነጥብ ከትንሹ ወደ ትልቁ የሚያመራ ሲሆን፣ ወንጌል ከሕግ በላይ ነው የሚለው ትልቅ ስፍራ ተሰጥቶታል። በመሆ ኑም ሕጉን አለመታዘዝ ቅጣት የሚያመጣ ከሆነ፣ ወንጌሉን አለመታዘዝ ደግሞ የበለጠ ቅጣት ያመጣል። *ያሰሙትም ለእኛ አረጋገጡልን፤* የዐይን ምስክር የነበሩት ሐዋርያት (2ጴጥ 1፥16፤ 1ዮሐ 1፥1 ይመ)፣ በመጀመሪያ በክርስቶስ የተሰበከውን መልእ ክት አረጋግጠዋል።

2፥4 *በምልክት፣ በድንቅና በልዩ ልዩ ታምራት* እግዚ አብሔር የወንጌልን መልእክት ያጸና የነበረው ልዕለ ተፈጥሮአዊ ነገሮችን በመፈጸም ለምሳሌ በሽተኞችን በመፈወስ ነው (የሐሥ 3፥7-9፡11-12፡16ይመ) *የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች፤* በልሳን መናገር፣ የመሳሰሉትን ነው (የሐሥ 2፥4-12 ይመ)፤ *እንደ ፈቃዱ በታደሉት*ም 1ቆሮ 12፥4-11 ይመ።

2፥5-18 የመዝ8፥4-6 ማብራሪያ ሲሆን፣ ክርስቶስ ከመላእክት በላይ መሆኑን ለማሳየት ጸሓፊው የጀመረውን ገለጻ የሚቀጥል ነው፤ ክርስቶስ የሰው ልጆች በምድር ላይ ገዢ በመሆን እንዲያከናውኑት የተሰጣቸውን ተግባር በመፈጸምና የወደቁትን መላእክት ሳይሆን በጎጒኦት የወደቁ ሰዎችን በመዋ ጀት ለእነርሱ የተሰጠውን ተልእኮ ፈጸመ። ይህን ሁሉ ለማድ ረግ ክርስቶስ ሰው መሆን ነበረበት (ቁ 11፤14 ይመ)።

2፥5 *መጪውን ዓለም ለመላእክት አላስገዛም* አንዳንድ ሰዎች፣ የዚህ መልእክት ተደራሲዎች የሚመጣው ዓለም በመላ እክት አገዛዝ ሥር ይውላል የሚለው አመለካከት ሳይማርካቸው አልቀረም ይላሉ (የ1፥4 ማብ ይመ)። ሌሎች ደግሞ ጸሓፊው የሚጥረው ተደራሲዎቹ ወደ ቀድሞው የይሁዲ እምነታቸው እን ዳይመለሱ ነው ይላሉ። ያም ሆነ ይህ የመልእክቱ ጸሓፊ፣ አዲ ሱን መገለጥ ያመጣው ክርስቶስ፣ በሲና ተራራ ላይ ሕግ ሲሰጥ ተሳትፎ ካደረጉት መላእክት እንደሚበልጥ በተጨባጭ አሳይ ቷል።

2፥6 (ሀ)*አንዱ በሌላ ስፍራ እንዲህ ብሎ መስክሮአል* እንደ መዝ 8፥4-6 ያለ በሚገባ የሚታወቅ ጥቅስ ቦታው የት እንደሆነ ለይቶ ማመልከት አስፈላጊ አይደለም።

2፥6 (ለ)-8 መዝሙረኛው ዕቡብ ድንቅ በሆነው የፍጥረት ሥርዐትና ፍጥረተ ዓለም ውስጥ በሚታዩት ልዩ ልዩ የእግዚ አብሔር እጅ ሥራዎች በመገረም፣ እንደ ሉምንት የሚቈጠ ረውን ሰው እግዚአብሔር በሌሎች ፍጥረታት ላይ ገዥ አድርጎ በመሾም፣ ያጐናጸፈውን ታላቅ ክብር እያሰበ ይደነቃል (ዘፍ 1፥26-28፤ እና ማብ ይመ)።

2፥7 *ከመላእክት* የመዝ 8፥5 ማብ ይመ።

2፥8 *ሁሉንም* እግዚአብሔር በመጀመሪያ የነበረው ዐላማ ሰው በሥነ ፍጥረት ላይ ገዥ እንዲሆንና ለእግዚአብሔር ብቻ እንዲገዛ ነው። በጎጒኦት ምክንያት ግን የእግዚአብሔር ዐላማ ሙሉ በሙሉ ገና እውን አልሆነም። እንዲያውም ሰው ራሱ "በባርነት ውስጥ" ነው ያለው (ቍ 15)።

2፥9 *ኢየሱስ ...አሁን የክብር ዘውድ ተጭኖለት* መዝ 8፣ እዚህ ላይ በተለይ ኢየሱስን ለማመልከት ገብቶአል። ሰው በምድር ላይ ገዥ እንዲሆን ለተሰጠው አዲስ ኀላፊነት ቀዳሚ እንደ መሆኑ መጠን፣ ለእጭር ጊዜ ከመላእክት ቢያንስም አሁን ግን በእግዚአብሔር ቀኝ የክብርና የምስጋና ዘውድ ተጭኖለታል። ፍጹም በሆነው ሕይወቱ፣ በመስቀል ሞት የተዋጀው ሰው በሚመጣው መንግሥት፣ በመዝ 8 ላይ የተነገረው ቃል እንዲፈጸምለት አድርጎአል። ያን ጊዜ ሰው በሥነ ፍጥረት ላይ ይሠለጥናል።

2፥10 *ብዙ ልጆችን ወደ ክብር* በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ አንድ ልጅ በሆነው በክርስቶስ አማካይነት የእግዚአብሔር ልጆች ሆነዋል (ከዮሐ 1፥12-13 ጋር ያነጻጽሩ)። *መሥራች* የግሪኩ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኘው አራት ጊዜ ብቻ ነው፤ እዚህ ላይ፤ 12፥2፤ የሐሥ 3፥15፤5፥31፤ ("ራስ")። *በመከራ ፍጹም ሊያደርገው* ክርስቶስ በምግባሩም ሆነ በመንፈሱ ፍጹም

[11]ሰዎችን የሚቀድሰውና የሚቀደሱት ሰዎች ከአንድ ቤተ ሰብ ናቸው፤ ስለዚህ ኢየሱስ ወንድሞች ብሎ ሊጠራቸው ዐያፍርም፤ [12]እንዲህም ይላል፤

"ስምህን ለወንድሞቼ እነግራቸዋለሁ፤
በጉባኤም መካከል ምስጋናህን እዘምራለሁ።"

[13]እንዲሁም፤

"እኔ በእርሱ እታመናለሁ።"

ደግሞም እንዲህ ይላል፤

"እነሆ፤ እኔና እግዚአብሔር የሰጠኝ ልጆች።"

[14]ልጆቹ በሥጋና በደም እንደሚካፈሉ እርሱ ራሱ ደግሞ ያነኑ ተካፈለ፤ ይኸውም በሞት ላይ ጎይል ያለውን ዲያቢሎስን በሞቱ ጎይል እንዲደመስስ ነው፤ [15]እንዲሁም በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ በሞት ፍርሀት ባርነት የታሰሩትን ነጻ እንዲያወጣ ነው። [16]እርሱ የመጣው መላእክትን ለመርዳት ሳይሆን፤ የአብርሃምን ዘር ለመርዳት እንደ ሆነ ግልጽ ነው። [17]ስለዚህ በሁሉም ነገር ወንድሞቹን መምሰል ተገባው፤ ይህንም ያደረገው መሓሪና ታማኝ ሊቀ ካህናት ሆኖ እግዚአብሔርን ለማገልገልና ለሕዝቡ የኀጢአትን ስረየት ለማስገኘት ነው። [18]እርሱ ራሱ በተፈተነ ጊዜ መከራን ስለ ተቀበለ፤ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና።

2፡11 ማቴ28፡10፤ ኤፌ5፡26፤ዕብ13፡12
2፡12 መዝ22፡22፤ 68፡26
2፡13 ኢሳ8፡17፡18፤ ዮሐ10፡29
2፡14 ዘፍ3፡15፤ ዮሐ1፡14፤1ቆሮ15፡50፡54-57፤ ኤፌ6፡12፤ 2ጢሞ1፡10፤1ዮሐ3፡8
2፡15 2ጢሞ1፡7
2፡16 ሉቃ3፡8
2፡17 ቀሌ14፤ ሮሜ3፡25፤ኤፌ2፡7፤ ዕብ3፡1፤4፡14፡15፤ 5፡1፡2፡5፡10፤7፡26፡ 28፡1፡3፡9፡11
2፡18 ዕብ4፡15

3፡1 ሮሜ 8፡28፤2ቆሮ9፡13፤ 1ጢሞ6፡12፤ ዕብ2፡11፡17፤4፡14፤ 10፡23
3፡2 ቁ፡5፤ዘኍ12፡7
3፡3 ዘፍ34፡12
3፡4 ዘፍ1፡1
3፡5 ቁ፡2፤ዘፀ14፡31፤ ዘኍ12፡7

ኢየሱስ ከሙሴ በላይ ነው

3 እንግዲህ የሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ፤ የእምነታችን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት የሆነውን ኢየሱስን አስቡ። [2]ሙሴ በእግዚአብሔር ቤት ሁሉ ላይ ታማኝ እንደ ነበር፤ እርሱም ለሾመው ታማኝ ነበር። [3]ቤትን የሚሠራ ከቤቱ ይልቅ የከበረ ክብር እንዳለው፤ ኢየሱስም ከሙሴ የሚበልጥ ክብር የተገባው ሆኖ ተገኝቶአል፤ [4]እያንዳንዱ ቤት የራሱ ሠሪ አለው፤ ነገር ግን ሁሉን የሠራ እግዚአብሔር ነው። [5]ሙሴ ወደፊት ስለሚነገረው ነገር እየመሰከረ፤ በእግዚአብሔር ቤት ሁሉ ላይ እንደ አንድ ታማኝ አገልጋይ ነበር፤ [6]ክርስቶስ ግን በእግዚአብሔር ቤት ላይ እንደ ታማኝ ልጅ ነው። እኛም የምንተማመን በትንና የምንመካበትን ተስፋ አጥብቀን ብንይዝ ቤቱ ነን።

ስለ አለማመን የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

[7]ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል፤
"ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ፤

3፡6 ቁ፡14፤ሮሜ5፡2፤11፡22፤1ቆሮ3፡16፤ 1ጢሞ3፡15፤ ዕብ1፡2፤ 4፡14፤6፡11፤ 8፡1፡9፡7፤19፡11፡1 3፡7 ሐሥ28፡25፤ዕብ9፡8፤10፡15

[17] ወይም ቁጣ ለመመለስ

ያልነበረበት ጊዜ የለም፤ ሆኖም መከራ በተቀበለ ጊዜ የለበሰው ሥጋ (ትስብእቱ) ፍጽምናን አገኘ። ራሱን ከእኛ ጋር አንድ በማድረግ እኛ የሆነውን ሁሉ እርሱም ሆነ፤ ከዚህም የተነሣ ለኀጢአታችን የሚገባውን ዋጋ ሊከፍልልንና ሊራራልን የሚችል ሊቀ ካህናት ሆነልን።

2፡11 *ሰዎችን የሚቀድሰውና የሚቀደሱት*፡ ክርስቶስ ራሱን ከሰዎች ጋር አንድ ለማድረግ ሲል ሰው ሆነ፤ ስለ ሰው በመስቀል ላይ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረቡም የሰዎችን ሕይወት ዐደሰ። *ወድሞች ብሎ ሊጠራቸው*፡ ከኢየሱስ ጋር ያለን ወንድማማችነት፤ በቤገር በተቤገር መካከል ያለ ወንድማማችነት ሲሆን፤ በዚህም ፍጹም አንድነት አግኝተናል።

2፡12 *ስምህን ለወንድሞቼ እነግራቸዋለሁ*፤ ከመዝ 22፡22 ላይ የተወሰደ ጥቅስ ሲሆን፤ ይህም ጻድቁ የእግዚአብሔር ባሪያ መከራ መቀበሉንና ድል አድራጊ መሆኑን የሚገልጽ መዝሙር ነው። (የመዝ 22ን መግቢያን ይመ)። እዚህ ላይ ቍልፉ ቃል "ወንድሞቼ" የሚለው ሲሆን፤ ቃሉ ከድል አድራጊው መሲሕ አንደበት የወጣ መሆኑን እናያለን።

2፡13 *በእርሱ እታመናለሁ*፤ በእግዚአብሔር ላይ እውነተኛ መታመንን የሚገልጽ አባባል ሲሆን፤ ይህም ፍጹም ሆኖ የታየው በክርስቶስ ነው። ደግሞም ሰው ሊሆነው የሚገባው ነገር በትክክል የታየው በእርሱ ነው። *እነሆ፤ እኔና እግዚአብሔር የሰጠኝ ልጆች*፤ ይህን ሥጉውም ልጅ ሲናገረው ይታያል። የአብ ልጆች የልጁ ወድሞች እንዲሆኑ ተሰጥተውታል (ቍ 11 ይመ)።

2፡14 *በሞት ላይ ጎይል ያለውን*፤ ሰይጣን የሞትን ጎይል የሚይዘው ሰዎች ኀጢአት እንዲሠሩ ማሳትና ሞትን በሚያስከትለው የኀጢአት ቅጣት ሥር እንዲወድቁ ማድረግ እስከ ፫ሺ ድረስ ብቻ ነው (ሕዝ 18፡14፤ሮሜ5፡12-፤ 6፡23 ይመ)።

2፡15 ኑ፡ 1ቆሮ 15፡54-57፤ ራእ 1፡18 ይመ።

2፡16 *የአብርሃምን ዘር*፡ ክርስቶስ የለበሰው የመላእክትን ተፈጥሮና ባሕርይ ሳይሆን፤ የአብርሃም ልጆች ተለይተው የሚታወቁበትን የሰዎችን ተፈጥሮና ባሕርይ ነው።

2፡17 *መሓሪና ታማኝ ሊቀ ካህናት*፡ ክርስቶስ ሰዎችን በእግዚአብሔር ፊት ወክሎ መቆም የሚችለው ከእነርሱ እንደ አንዱ ሲሆን ብቻ ነው። *ዮጠኢትን ስርዮት ... ለማስገኘት*፡ አማራጭ ትርጉሙን ይመ፤ እንዲሁም የዘሌ 16፡20-22፤ 17፡11፤ ግብ ይመ። ክርስቶስ ኀጢአተኞች ላይ የሚነደውን የእግዚአብሔርን ቍጣ ለመመለስ ከእነርሱ እንደ አንዱ መሆንና በእነርሱ ምትክ መሞት አለበት።

2፡18 *በተፈተነ ጊዜ*፤ የዓ፡15 ግብ ይመ።

3፡4-4፡13፤ የመዝሙር 95፡7-11 ግብ ነው። ክርስቶስ ከሙሴ በላይ መሆኑን በተጨባጭ የሚገልጽና አለመታዘዝና አለ ማመን የሚያስከትለውን ጥፋት የሚያስጠነቅቅ ክፍል ነው።

3፡1 *ተካፋዮች*፡ የቍ 14 ግብ ይመ። *የሰማያዊው ጥሪ*፤ ከሰማይ የመጣና ወደ ሰማይ የሚመራ ግብዣ ነው። *ሐዋርያና "ዋተላከ" ማለት* ነው (የማር 6፡30 እና የ1ቆሮ 1፡1 ግብ ይመ)። ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ከአብ ተልኮ እንደሆነ ራሱ ተናግሮአል። ለምሳሌ (ማቴ 10፡40፡15፡24፤ ማር 9፡36፤ ሉቃ 9፡48፤ ዮሐ 4፡34፡5፡24፡30፡36-38፡6፡38 ይመ)። እርሱም ለሌሎቹ ሐዋርያትን የሚሰጥ ታላቅ ሐዋርያ ነው።

3፡2፤ እዚህ ላይ የሚነጻጸሩት ክርስቶስና ሙሴ ሲሆኑ፤ ሁለቱም ሕዝቡን እንዲመሩ ከአብ የተላኩ ቸው፤ አንደኛው ከፈርዖን ባርነት ነጻ አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር የሚመራቸው ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ የሚያምኑብትን ከዲያብሎስ ባርነት ነጻ አውጥቶ (2፡14-15) ተስፋ ወደ ተሰጣቸው የሰንበት ዕረፍት የሚመራቸው ነው (4፡3-9)። የሰንበት ዕረፍት የተባለው መንግሥተ ሰማይ ሲሆን፤ ይችላል፤ ብዙዎች ግን ቃሉ የሚያመለክተው በክርስቶስ ቤዛነት የተገኘውን የደኅንነት ዕረፍት ነው ይላሉ። የቀረቡት ምሳሌዎች የሚያተኩሩት ታማኝ መጋቢ ሆኖ በመገኘት ላይ ነው።

3፡3 *ቤትን የሚሠራ ከቤቱ ይልቅ የሚበልጥ ክብር እንዳለው*፤ ኢየሱስ የቤቱ (የቤተ ሰቡ) ሠሪ ሲሆን፤ ሙሴ ግን ከቤተ ሰቡ እንደ አንዱ አባል የሚቈጠር ብቻ ነው።

3፡4 *ሁሉን የሠራ እግዚአብሔር ነው*፤ እዚህ ላይ ኢየሱስ ከአብ ጋር እኩል ሆኖ ቀርቦአል፤ ይህም ክርስቶስ ከሙሴ የሚበልጥ መሆኑን በግልጽ ያሳያል።

3፡5-6 *በእግዚአብሔር ቤት ሁሉ ላይ እንደ አንድ ታማኝ አገልጋይ ...በእግዚአብሔር ቤት ላይ እንደ ታማኝ ልጅ*፤ ክርስቶስ ከሙሴ እንደሚበልጥ በሁለት መንገድ ለማሳየት ተሞክሮአል፤ (1) ሙሴ አገልጋይ ሲሆን ክርስቶስ ግን ልጅ ነው፤ (2) ሙሴ የእግዚአብሔር ቤት አባል ማለትም ከቤተሰቡ አንዱ ሲሆን ክርስቶስ ግን የእግዚአብሔር ቤት ገዥ ነው።

3፡6 *እኛም ...ቤቱ ነን*፤ ቤቱ የተሠራው ቤተሰብ ከሆነው ከእግዚአብሔር ሕዝብ ነው፤ (ኤፌ 2፡19፤ 1ጴጥ 2፡5 ይመ)። *የምንተማመንበትንና የምንመካበትን ተስፋ አጥብቀን ብንይዝ*፤ እስከ መጨረሻው ጸንቶ እስመጨቃው የእግዚአብሔር ልጅ አለመሆንን ሲያሳይ፤ እስከ መጨረሻው ጸንቶ መቆም ደግሞ የእርሱ ልጅ መሆንን የሚያሳይ ልዩ ምልክት ነው።

3፡7-11፤ ይህ ከመዝ 95፡7-11 ላይ የተወሰደው ጥቅስ በሙሴ አመራር ሥር ሆነው በምድረ በዳ ይዓዙ የነበሩትን የእስራኤላውያንን አሳፋሪ ታሪክ ባጭሩ የሚያቀርብ ነው። እዚህ ላይ

8በምድረ በዳ በፈተና ቀን፣
በዐመፅ እንዳደረጋችሁት፣
ልባችሁን አታደንድኑ።
9አባቶቻችሁ በዚያ ተፈታተኑኝ፤
መረመሩኝ፤ ያደረግሁትንም ሁሉ ለአርባ
ዓመት አዩ።
10በዚያም ትውልድ ላይ የተቈጣሁት ለዚህ ነበር፤
እንዲህም አልሁ፣ ‘ልባቸው ሁልጊዜ ይስ
ታል፤
መንገዴንም አላወቁም፤’
11ስለዚህ በቍጣዬ እንዲህ ብዬ ማልሁ፤
“ወደ ዕረፍቴ ከቶ አይገቡም።”

12ወንድሞች ሆይ፤ ከእናንተ ማንም ከሕ
ያው እግዚአብሔር የሚያስኰበልል፣ ኀጢአተ
ኛና የማያምን ልብ እንዳይኖረው ተጠን
ቀቁ። 13ነገር ግን ከመካከላችሁ ማንም
በኀጢአት ተታሎ ልቡ እንዳይደነድን፣
“ዛሬ” እየተባለ ሳለ በየቀኑ እርስ በርሳችሁ
ተጽናኑ። 14በመጀመሪያ የነበረንን እምነት
እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንይዝ ከክርስ
ቶስ ጋር ተካፋዮች እንሆናለን፤ 15ይኸውም፣
“ዛሬ ድምጹን ብትሰሙ፣
በዐመፅ እንዳደረጋችሁት፣
አሁንም ልባችሁን አታደንድኑ” እንደተባ
ለው ነው።
16ሰምተው ያመፁት እነማን ነበሩ?
ሙሴ ከግብፅ መርቶ ያወጣቸው ሁሉ አይ
ደሉምን? 17አርባ ዓመት የተቈጣውስ እነ
ማንን ነበር? ኀጢአት ሠርተው ሬሳቸው
በምድረ በዳ ወድቆ የቀረውን አይደለምን?
18ያልታዘዙትንም ካልሆነ በቀር ወደ ዕረፍቱ
እንዳይገቡ የማለባቸው እነማን ነበሩ? 19እን

3፥8 ቍ15፤ዕብ4፥7
3፥9 ዘጸ14፥33፤
ዘጸ1፥31ሐሥ7፥36
3፥11 ዘጸ1፥34፤
35፤መዝ95፥7-11፤
ዕብ4፥3፤5
3፥12 ማቴ16፥16
3፥13 ኤር17፥9፤
ኤፌ4፥22፤
ዕብ10፥24፤25
3፥14 ቍ6፤ኤፌ3፥12
3፥15 ቍ7፡8፤
መዝ95፥7፡8፤ዕብ4፥7
3፥16 ዘጸ14፥2
3፥17 ዘጸ14፥29፤
መዝ106፥26፤
1ቆሮ10፥5
3፥18 ዘጸ14፥20-23፤
ዘጸ1፥34፡35፤ዕብ4፥6

3፥19 መዝ78፥22፤
106፥24፤ ዮሐ3፥36
4፥1 ዕብ12፥15
4፥2 1ተሰ2፥13
4፥3 ዘጸ1፥34፡35፤
መዝ95፥11፤ዕብ3፥11
4፥4 ዘፍ2፥2፡31
ዘፀ20፥11
4፥5 ቍ3፤መዝ95፥11
4፥6 ቍ11፤ዕብ3፥18
4፥7 መዝ95፥7፡8፤
ዕብ3፥7፡8፡15
4፥8 ኢሱ22፥4፤
ዕብ1፥1

ግዲህ ሊገቡ ያልቻሉት ካለማመናቸው የተ
ነሣ እንደ ሆነ እንረዳለን።

የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ

4እንግዲህ ወደ ዕረፍቱ ለመግባት የተ
ሰጠው ተስፋ አሁንም የተጠበቀ ስለ
ሆነ፣ ከእናንተ ማንም ለዚያ ሳይበቃ እንዳ
ይቀር እንጠንቀቅ፤ 2ለእኛዚያ እንደ ተሰበሰ
ለእኛም ደግሞ የምሥራቹ ቃል ተሰብኮ
ልናልና። ነገር ግን ሰሚዎቹ ቃሉን ከእም
ነት ጋር ስላላዋሐዱት አልጠቀማቸውም።
3እኛ ያመነው ግን ወደዚያ ዕረፍት እንገባ
ለን፤ እግዚአብሔርም፣
“ስለዚህ በቍጣዬ እንዲህ ብዬ ማልሁ፤
‘ወደ ዕረፍቴ ከቶ አይገቡም’ ” ብሎአል።
ይሁን እንጂ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የእ
ርሱ ሥራ ተከናውኖአል። 4ስለ ሰባተኛውም
ቀን በአንድ ስፍራ፣ “በሰባተኛውም ቀን እግ
ዚአብሔር ከሥራው ሁሉ ዐረፈ” ብሎአልና።
5ቀደም ባለው ክፍል ደግሞ፣
“ወደ ዕረፍቴ ከቶ አይገቡም” ይላል።
6ወደ ዕረፍቱ ገና የሚገቡ አንዳንዶች
አሉ፤ ቀድሞ የምሥራቹ ቃል የተሰበከላ
ቸው ባለመታዘዛቸው ምክንያት ወደ ዕረ
ፍት አልገቡም። 7ስለዚህ እግዚአብሔር፣
“ዛሬ” ብሎ እንደ ገና አንድን ቀን ወሰነ፤
ይህም ከብዙ ዘመን በኋላ በዳዊት በኩል፣
“ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ፣
ልባችሁን አታደንድኑ”
ተብሎ ቀደም ሲል እንደተነገረው ነው።
8ኢያሱ ዕረፍትን ሰጥቶአቸው ቢሆን ኖሮ፣
ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ስለ ሌላ ቀን ባለተ

ሥስት ዘመኖች ወይም ጊዜዎች ተጠቅሰዋል፤ እዝዚም ከጕዞ መውጣት የተፈጸመበት፣ መዝሙረኛው የነበረበትና የዕብራውያን መልእክት የተጻፈበት ናቸው። መዝሙረኛው በሙሴ አመራር ሥር የነበሩ እስራኤላውያንን ምሳሌ አድርጎ በመውሰድ፣ በእርሱ ዘመን ለሚኖሩ እስራኤላውያን አለመታዘዝ የሚያስከትለውን ቅጣት ለማስጠንቀቅ ተጠቅሞበታል። ልክ እንዲሁ የዕብራውያን መልእክት ጸሓፊም የመዝሙረኛው ማስጠ ቀቂያ ለተደራሲያኑና በዚህም ዘመን የሚገኙ የእግዚአብሔር ሰዎችን የሚመለከት መሆኑን ይገልጻል።

3፥12 *ከእናንተ ማንም ከሕያው እግዚአብሔር የሚያስኰ በልል*፤ ከግብጽ የወጡት አንዳንድ እስራኤላውያን እንዳደረ ጉት፣ ዐመፀኛ ሆኖ ከእግዚአብሔር መኰበል (ቃል በቃል ሲተ ረጎም “ከሓዲ መሆን” ማለት ነው) ከሕይወት ኩብልሎ ሞትን መምረጥ ማለት ነው።

3፥13 *“ዛሬ”* እየተባለ ሳለ፤ 4፥7 ይመ። ይህ ቀን አሁንም የእግዚአብሔር የጸጋ ቀንና በእርሱም ለማመን የተመረጠ ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ ገደብ የለሽ አይደለም።

3፥14 *ከክርስቶስ ጋር ተካፋዮች*፤ የእርሱና የበረከቱ ተካፋይ መሆን ነው (ከቍ1 ጋር ያነጻጽሩ)። *በመጀመሪያ የነበረንን እምነት እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንይዝ*፤ አንድ ሰው ድኑት እንደተቀበለ ማረጋገጥ የሚችለው፣ በእምነቱ እስከ መጨረሻው ድረስ መዝለቅ የቻለ እንደሆነ ነው። በዚህ ዐይነት አንቶ ከክርስቶስ ጋር ተካፋይ የሚሆኑት ሰዎች እነማን እንደ ሆኑ የሚታወቁት በእንዲህ ያለው ጽናት ነው (የቍ 6 ማብ ይመ)።

3፥16-19፤ የመልእክቱ ጸሓፊ የጀመረውን ገለጻ የሚቀጥለው እርስ በርስ የቁያያዙ ጥያቄዎችን በማንሣት ነው። እዚህ ላይ እንዲታይ የተፈለገው እውነት ወደ ከነዓን ለመግባት ያልቻሉት እስራኤላውያን፣ እግዚአብሔር ስለ ተስፋዱቱ ምድር የገባውን ቃል በጆሮአቸው የሰሙና እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ (ቍ 19)፣ *ያላመኑ* መሆናቸውን ነው፤ ይህም ድርጊት እንደ ዐመፅ (ቍ 6)፣ ኀጢአትና (ቍ 17) አለመታዘዝ (ቍ 18) ተቈጥሮባቸዋል። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ከቍጣው የተነሣ በወቅቱ በነበሩት በእስራኤላውያን ትውልድ ፊት የከነዓ ንን በሮች ዘጋ (ዘኍ 14፥21-35)። በመጀመሪያው ምእተ ዓመት የነበሩ የዕብራውያን መልእክት ተደራሲዎችም ተመሳሳይ የሆነ መንፈሳዊ ችግር ገጥሞአቸው ነበር።

4፥1 *እንግዲህ ወደ ዕረፍቱ ለመግባት የተሰጠው ተስፋ አሁንም የተጠበቀ ስለሆነ*፤ ድኑትን አሁንም፣ ማግኘት ይቻላል። ወደ ዕረፍቱ የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው እስራኤላውያን ከነዓን ሲገቡ የሚያገኙትን ዕረፍት አይደለም። ይህ በኢያሱ መሪነት ያገኙት ዕረፍት ጊዜአዊና ምድራዊ (ቍ8 ይመ እንዲ ሁም የኢያሱን 1፥13 ማብ ይመ) ሲሆን የሚያመለክተውም ወደፊት የሚመጣውን ዘላለማዊና ሰማያዊ ዕረፍት ነው።

4፥3 *እኛ ያመነው ... ወደዚያ ዕረፍት እንገባለን*፤ ወደ ምድራዊቷ ከነዓን ለመግባት እግዚአብሔር የተሰጠውን ተስፋ ማመን እንደሚያስፈልግ ሁሉ፣ ወደ ድኑቱ ዕረፍት መግባት የሚቻለውም ኢየሱስ ክርስቶስንና የፈጸመውን የማዳን ሥራ በማ መን ብቻ ነው። *ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የእርሱ ሥራ ተከናውኖአል*፤ እግዚአብሔር የመፍጠር ሥራውን ፈጽሞ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ (ቍ 4፤ ዘፍ 2፥2 ይመ)፤ በመሆኑም ዕረ ፍቱ ቀድሞውኑ የተረጋገጠ ነው። እግዚአብሔር እንድንገባበት የጠራን ዕረፍት (ቍ 10-11)፣ የእኛ ዕረፍት ሳይሆን የእርሱ ዕረ ፍት ነው፤ እርሱም ይህን ዕረፍት እንድንካፈል ጋበዘን።

4፥6-8 እስራኤላውያን በኢያሱ መሪነት ወደ ከነዓን ምድር ቢገቡም፣ የገቡት ግን ከፊልና ጊዜአዊ ወደ ሆነው የእግዚአብሔር ዕረፍት ነው። በመዝ 95፥7-8 ላይ እንደተመ ለከተው ግብዣው የሚቀጥል በመሆኑ፣ ወደዚያ ዕረፍት መግ ባቱ የመጨረሻ አይደለም።

4፥7 *“ዛሬ” ብሎ፣* የ3፥13 ማብ ይመ።

ናገረ ነበር። [9]ስለዚህ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ገና ቀርቶለታል፤ [10]ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት የሚገባ ሁሉ፣ እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ፣ እር ሱም ደግሞ ከሥራው ያርፋል። [11]እንግዲህ ማንም የእነዚያን አለመታዘዝ ምሳሌ ተከ ትሎ እንዳይወድቅ ወደዚያ ዕረፍት ለመግ ባት እንትጋ።

[12]የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና የሚሠራ ነውና፤ በሁለት በኩል ስለት ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ ስለታም ነው፤ ነፍስንና መንፈ ስን፣ ጅማትንና ቅልጥምን እስኪለያይ ድረስ ዘልቆ ይወጋል፤ የልብንም ሐሳብና ምኞት ይመረምራል። [13]ከእግዚአብሔር ዐይን የተሰ ወረ ምንም ፍጥረት የለም፤ ስለ ራሳችን መልስ መስጠት በሚገባን በእርሱ ፊት ሁሉም ነገር የተራቈተና የተገለጠ ነው።

ታላቁ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ

[14]እንግዲህ ወደ ሰማያት ያረገ[ሠ] ታላቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፣ እምነታችንን አጥብቀን እንያዝ። [15]በድካማችን የማይራራልን ሊቀ ካህናት የለንምና፤ ነገር ግን እንደ እኛ በማንኛ ውም ነገር የተፈተነ ሊቀ ካህናት አለን፤ ይሁን እንጂ ምንም ኀጢአት አልሠራም። [16]እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበልና በሚ

4፥10 ቊ፬፡፭፣፳፫፥፴፤ ራእ፲፬፥፲፫
4፥11 ቊ፳፩፡፴፭፥፲፰
4፥12 ኢሳ፶፭፥፲፩፤ ኢር፳፫፥፳፱፤ ማር፬፥፲፬፡፩፦፭፥፩፤ ፲፩፥፳፰፡ሐ፲፥፴፭፤ ሐሥ፯፥፴፰፤፪፥፵፤ ፩ቆር፲፬፥፳፬፡፳፭፤ኢሬ ፮፥፲፯፤፡ተሰ፪፥፲፫፤ ፪ጢሞ፬፥፱፤ ፩ጴጥ፤፳፫፤፪ሮሐ፪፥፲፬፤ ራእ፩፥፪፡፱፡፲፮
4፥13 መዝ፴፫፥፲፫-፲፭፤ ምሳ፭፥፳፩፤ኢር፲፮፥፲፯፤ ፳፫፥፳፬፤ዳን፯፥፳፪
4፥14 ማቴ፬፥፳፤ ዕብ፭፥፲፯፥፲፮፥፳፡፰፥፲፱፥፳፬
4፥15 ፪ቆር፭፥፳፩፤ ዕብ፪፥፲፰
4፥16 ኤፌ፮፥፲፪፤ ዕብ፯፥፲፱

5፥1 ዕብ፰፥፲፯፥፳፯፤ ፰፥፲፱፥፱
5፥2 ኢሳ፵፱፥፳፬፤ ዕብ፲፪፥፲፭፥፲፯፥፳፰
5፥3 ዘሌ፱፯፥፲፮፥፩፤ ዕብ፯፥፳፯፥፯
5፥4 ዘፀ፳፰፥፲፤ ዘኍ፲፮፥፵፡፲፰፥፯
5፥5 መዝ፪፥፯፤ ማቴ፫፥፲፯፡ዮሐ፰፥፶፬፤ ዕብ፲፥፲፪፥፲፯

ያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድና ገኝ፣ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅ ረብ።

5 እያንዳንዱ ሊቀ ካህናት ከሰዎች መካ ከል ይመረጣል፤ የእግዚአብሔርም በሆነው ነገር ላይ ሰዎችን በመወከል ለኀጢአት የሚሆነ ውን መባንና መሥዋዕትን ለማቅረብ ይሾ ማል። [2]እርሱ ራሱ ድካም ያለበት በመ ሆኑ፣ አላዋቂ ለሆኑትና ለሚባዝኑት ሊራ ራላቸው ይችላል። [3]ስለራሱ ኀጢአትና ስለ ሌሎች ሰዎች ኀጢአት መሥዋዕት ማቅረብ የተገባው በዚሁ ምክንያት ነው።

[4]አሮን እንደ ተጠራ በእግዚአብሔር መጠራት አለበት እንጂ፣ ይህን ክብር ለራሱ የሚወ ስድ ማንም የለም። [5]እንዲሁም ክርስቶስ ሊቀ ካህናት የመሆንን ክብር ለራሱ አልወ ሰደም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር፣

"አንተ ልጄ ነህ፤
እኔ ዛሬ አባት ሆንሁህ"[ሸ] አለው።

[6]እንዲሁም በሌላ ስፍራ፣

"እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት፣
አንተ ለዘላለም ካህን ነህ" ይላል።

[7]ኢየሱስ በዚህ ምድር በኖረበት ዘመን

5፥6 ቊ፲0፡፮፣፲፱፡መዝ110፥4፤ዕብ6፥2017፥1-22 5፥7 መዝ22፥24፤ማቴ27፥46፡50፤ማር14፥36፡ሉቃ22፥41-44፤23፥46

[ሠ]14 ወይም ወደ ሰማይ የዞረ
[ሸ]5 ወይም መልጀሃለሁ።

4፥9 *ስለዚህ የሰንበት ዕረፍት ... ኛ ቀርቶለታል፤* ወደ እግዚ አብሔር ዕረፍት መግባት የሚቻለው በልጁ በማመን ብቻ ነው።

4፥10 *ከሥራው ያርፋል፤* እግዚአብሔር የሥነ ፍጥረት ሥራውን ጨርሶ እንዳረፈ፣ አማኞችም ድኑትን በገዛ ሥራቸው ለማግኘት የሚያደርጉት ጥረት አቁመው ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሠርቶ በፈጸመው ሥራ ይርፋሉ። አንዳንድ ሊቃውንት እንደሚናገሩት እዚህ ላይ ጸሓፈው የሚናገረው አማኞች ስለሚያገኙት የመጨረሻው ዕረፍት ነው (ራእ 14፥13 ይመ)።

4፥11 *እንትጋ፤* ድኑትን በሥራ እንድናገኝ የቀረበ ጥሪ ሳይሆን፣ ወደ ድኑት ዕረፍት በእምነት እንድንገባ እንጂ እስራ ኤላውያን በምድረ በዳ የፈጸሙትን አሳዛኝ ምሳሌ እንዳንከተል የተሰጠ ምክር ነው።

4፥12-13፤ በቊ 11 ላይ የተሰጠው ምክር በሚገባ ማጤን ያስፈለገበትን ምክንያት የሚገልጽ ነው።

4፥12 *የእግዚአብሔር ቃል፤* የእግዚአብሔር እውነት የተገለጠው በኢየሱስ ነው (እርሱም *ሥጋ የለበሰው ቃል* ነው፤ ዮሐ 1፥1፤14 ይመ)፤ እዚህ ላይ የተነገረው "ቃል" የተገለጠው በቃል ማለት በእንደበት ነው። ይህ ብርቱ ኀይል ያለው የእግዚ አብሔር ቃል ሕያው በመሆኑ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሲፈጽም እንደሚችል በብሉይና በአዲስ ኪዳን ተገልጦአል (መዝ 107፥20፤147፥18፤ኢሳ40፥8፤55፥11፤ዘፍ3፥8፤ኤፌ5፥26፤ያዕ1፥18፤ 1ጴጥ1፥23 ይመ)። የዕብራውያን መልእክት ጸሓፊም ሲናገር፣ ይህ ቃል ሁሉን በሚያይ ዐይን ስውር በሆነው ውስጣዊ አካላችን ዘልቆ በመግባት መመርመር የሚችል ሕያው ኀይል ነው። *ነፍስንና መንፈስን፣ ጅማትንና ቅልጥምን፤* የሰውን ሁለንተናና ጥልቅ የሆነውን ውስጣዊ ማንነቱን የሚገልጽ ነው።

4፥13 *ከእግዚአብሔር ዐይን የተሰወረ ምንም ፍጥረት የለም፤* የመልእክቱ ጸሓፊ ቃሉ የሚሠራው ሥራና እግዚአብሔር የሚሠራው ሥራ አንድና ተመሳሳይ እንደ ሆኑ አድርጎ አቅርቦአቸዋል፤ በእርግጥም ደግሞ አንድና ተመሳሳይ ናቸው።

4፥14-7፥28፤ የመዝ 110፥4 ግብራሪያ ሲሆን፣ ክርስቶስ የሚሻል ክህነት ስላለው ከአሮን በላይ መሆኑን በአጽንዖት የሚገ ልጽ ክፍል ነው።

4፥14 *ታላቅ ሊቀ ካህናት፤* 2፥17፤3፥1 ይመ። የመልእክቱ ጸሓፊ የክርስቶስ ክህነት ከአሮን ክህነት የሚበልጥ መሆኑን ለመግለጽ፣ ረጅም ማብራሪያውን እዚህ ላይ ይጀምራል። *ወደ ሰማ ያት፥* ከአሮን ወገን የሆኑት ሊቀ ካህናት በስርየት ቀን በሕዝቡ ፊት አልፈው ወደ ቅድስት ቅዱሳን እንደሚገቡ ሁሉ (ዘሌ 16፥14፤17 ይመ)፣ ኢየሱስም ቆመው በሚያዩት ደቀ መዛሙ ርቱ ፊት ወደ ሰማይ ማለትም ወደ ሰማያዊቷ ቤተ መቅደስ ዐረገ፤ ይህም የቤዛት ሥራውን እንደ ፈጸመ ያሳያል። (ሐሥ 1፥9-11)። *እምነታችንን አጥብቀን እንያዝ፤* የመልእክቱ ተደራሲዎች ከያዙት እምነት ለማፈግፈግ የዳዳቸው ይመስላል፡ (ተመሳሳይ ምክር መስጠቱን ቊ2፡፲፫፥፮፲፬ ላይ ይመ)።

4፥15 *ነገር ግን እንደ እኛ በማንኛውም ነገር የተፈተነ፤* 2፥18 ይመ። የመልእክቱ ጸሓፊ በክርስቶስና በእኛ ላይ የደረሰውን ፈተና ጎን ለጎን አስቀምጦ ያነጻጽራል፤ ክርስቶስ፣ በእኛ ላይ የደረሰውን ፈተና ሁሉ ባይቀበልም፣ እንደ እኛ በሁሉም ረገድ ተፈትኖአል። *ይሁን እንጂ ምንም ኀጢአት አል ሠራም፤* የክርስቶስ መፈተን ከእኛ የሚለይበት ነገር ቢኖር በውጤቱ ብቻ ነው፤ ይኸውም እርሱ እንደ እኛ በተፈተነ ጊዜ በፈተናው አልወደቀም (ማቴ 4፥1-11 ይመ)።

5፥1-4፤ ሊቀ ካህናት ሆኖ ለማገልገል ሁለት መመዘኛ ዎችን ማሟላት ያስፈልጋል፤ (1) የሚመረጠው ሰው "ከሰዎች መካከል" መሆን አለበት፤ እንዲህ ከሆነ ሰዎችን ወክሎ በእግዚአብሔር ፊት መቆም ይችላል። (2) "በእግዚአብሔር መጠራት አለበት" (ቊ 4)።

5፥1 *መባንና መሥዋዕትን፤* 8፥3፤9፥9 ተመልከት፤ እንዲ ሁም የዘሌ 1፥2፤2፥1 ማብ ይመ።

5፥2 *አላዋቂ ለሆኑትና ለሚባዝኑት፤* ኢሳ 53 6 የመ። ባለማወቅ የሚፈጸመውን ኀጢአት (በዘሌ 4፤ዘኍ፲፭፥27-29 እንደ ተጠቀሰው ዐይነት)፣ እግዚአብሔርን በመናቅ ሆን ብሎ ከሚሠ ራው ኀጢአት ጋር ያነጻጽሩ (ዘኍ 15፥30-31 ይመ፤ እንዲሁም ከዕብ 6፥4-6፤10፥26-31 *ጋር ያነጻጽሩ*)።

5፥4 *ይህን ክብር ለራሱ የሚወስድ ማንም የለም፤* ክርስቶስ በነበረበት ዘመን የሊቀ ካህናት ቢሮ በአንድ ቤተሰብ ቊጥጥር ሥር ነበር።

5፥5 *ክርስቶስ ሊቀ ካህናት የመሆንን ክብር ለራሱ ለልወሰደም፤* እዚህ ላይ የተጠቀሱት ሁለት ትንቢታዊ ምንባቦች እንደሚያመለክቱት፣ ልጅ የተሾመው በእብ ነው (መዝ 2፥7፤110፥4)፤ ደግሞም ሊቀ ክህነቱ እንደ አሮን ሹመት ሳይሆን "እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት" (ቊ 6) ነው። *እኔ ዛሬ አባት ሆንሁህ* የ1፥5፤ እና መዝ 2፥7-9 ማብ ይመ፤ ከሮሜ 1፥4 *ጋር ያነጻጽሩ*።

5፥7 *ኢየሱስ በዚህ ምድር በኖረበት ዘመን፤* እዚህ ላይ ለማ መልከት የተፈለገው ዋናው ነገር ክርስቶስ በጌቴሴማኒ የአት

ከሞት ሊያድነው ወደሚችለው ጸሎትንና ልመናን ከታላቅ ጩኸትና ከእንባ ጋር አቀረበ፤ ፍጹም ትሑት ሆኖ በመታዘዙም ጸሎቱ ተሰማለት። 8የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም እንኳ፣ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፤ 9በዚህም ፍጹም ሆኖ ከተገኘ በኋላ፣ እርሱን ለሚታዘዙ ሁሉ የዘላለም ድኅነት ምክንያት ሆነላቸው፤ 10እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመትም ሊቀ ካህናት ተብሎ በእግዚአብሔር ተሾመ።

5፥8 ፊል2፥8፤ ዕብ1፥2
5፥9 ዕብ2፥10
5፥10 ቁ•5፡6፤ ዕብ2፥17
5፥12 1ቆሮ3፥2፤ ዕብ6፥11፤ ጴጥ2፥2
5፥13 1ቆሮ14፥20

በእምነት ስላለመጽናት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

11ስለዚህ ጉዳይ የምንናገረው ብዙ ነገር አለን፤ ነገር ግን ለመማር ዳተኛ ስለ ሆናችሁ ለማስረዳት አስቸጋሪ ነው። 12በዚህ ጊዜ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፣ ገና የእግዚአብሔርን ቃል የመጀመሪያ ትምህርት የሚያስተምራችሁ ሰው ያስፈልጋች ኋል፤ የሚያስፈልጋችሁም ጠንካራ ምግብ ሳይሆን ወተት ነው። 13ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለሆነ፣ ከጽድቅ ትምህርት ጋር ገና አልተዋወቀም። 14ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙን ከክፉው ለመለየት ራሳቸውን

5፥14 ኢሳ7፥15፤ 1ቆሮ2፥6
6፥1 ፊል3፥12-14፤ ዕብ5፥12፤9፥14
6፥2 ዮሐ3፥25፤ ሐሥ2፥24፤6፤ 17፥18፡32
6፥3 ሐሥ18፥21
6፥4 ዕዝ9፥2፤ኢሌ2፥8፤ ዕብ10፥32
6፥5 መዝ34፥8፤ ዕብ4፥12
6፥6 ማቴ4፥3፤ 2ጴጥ2፥21፤1ዮሐ5፥16

ሳስለመዱ፣ ለበሰሉ ሰዎች ነው።

6ስለዚህ ስለ ክርስቶስ የተሰጠውን የመጀመሪያ ትምህርት ትተን ወደ ብስለት እንሂድ፤ ከሞተ ሥራ ንስሓ ስለ መግባትና+ በእግዚአብሔር ስለ ማመን እንደ ገና መሠረትን አንጣል፤ 2እንዲሁም ስለ ጥምቀቶች፣ እጅ ችን ስለ መጫን፣ ስለ ሙታን ትንሣኤና ስለ ዘላለም ፍርድ ትምህርት እንደ ገና አንመሥርት። 3እግዚአብሔር ቢፈቅድ ይህን እናደርጋለን።

4አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን፣ ሰማ ያዊውን ስጦታ የቀመሱትን፣ ከመንፈስ ቅዱስ ተካፋዮች የሆኑትን፣ 5መልካሙን የእግዚአብሔር ቃልና የሚመጣውን ዓለም ኀይል የቀመሱ ትን፣ 6በኋላ ግን የካዱትን እንደ ገና ወደ ንስሓ መመለስ አይቻልም፤ ምክንያቱም እነርሱ ለገዛ ጥፋታቸው የእግዚአብሔርን ልጅ እንደገና ይሰቅሉታል፤ ያዋርዱታልም።

7ዘወትር በእርሷ ላይ የሚወርደውን ዝናብ የምትጠጣና ለሚያርሷትም ፍሬ የምትሰጥ መሬት ከእግዚአብሔር በረከትን ትቀበላለች።

+1 ወይም ከከንቱ ሥርዐት

ክልት ስፍራ የደረሰበትን ሥቃይ ነው። *ከሞት ሊያድነው ወደሚችለው* ወደ አባቱ ነው። ኢየሱስ ከእርሱ እንዲያልፍ የፈለገው በሥጋው የሚቀበለውን መከራና ሞት ሳይሆን የሰዎችን ኀጢአት በመሸከሙ የሚደርስበትን እንደበት ሊገልጸው የማ ይቻለውን ሥቃይ ነው (ማቴ 27፥46 ይመ)። ምንም እንኳ የመከራው ጽዋ ከእርሱ እንዲወገድ ቢለምንም፣ የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም ካለው ቁርጥ አቋም ግን ከቶ አላመነታም (ማቴ 26፥36-46 ይመ)። *ተሰማለት*፡ አብ ትንሣኤ በመስጠት ጸሎቱ መልስ እንዲያገኝ አድርጎአል።

5፥8 *ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ*፤ "ፍጹም" (ቁ• 9) ሊሆን የቻለው በተቀበለው መከራ (የ2፥10 ማብ ይመ)፤ ማለትም በምድረ በዳ በተቀበለው ፈተናና በመስቀል ላይ በተሸከመው መከራ ነው። ምንም እንኳ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅ ቢሆንም፣ *ሥጋ* የለበሰ ልጅ እንደ መሆኑ፣ *መታዘዝን* መማር ያስፈልገዋል፤ ይህ የሆነው ያልታዘዘበት ጊዜ ስለ ነበር ሳይሆን፣ ከዚህ በፊት ያላሳየውን *መታዘዝ* እንዲያሳይ በመጠራቱ ነው። የደረሰበት ፈተና እውነተኛ ከመሆኑም በላይ ውጊያውን በአሸናፊነት ለመወጣት እጅግ አስቸጋሪ ነበር፤ ይሁን እንጂ አዳም የሳተበትንና የወደቀበትን ነገር ኢየሱስ ተቋቁሞ ድል አደረገ። በዚህ ዐይነት ሰብእዊ ማለትም ሰው መሆኑ "ፍጹም ሆነ" (ቁ• 9)፤ ፍጹም በመሆኑም "ዘላለማዊ ቤዛነትን ሊያ ስገኝ" (9፥12 ይመ) ቻለ።

5፥11 *ስለዚህ ጒዳይ የምንናገረው ብዙ ነገር አለን*፤ "እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት" (ቁ•10) ስላለው፣ ስለ ክርስቶስ ዘላለማዊ ክህነት ነው። *ለመማር ዳተኛ ስለ ሆናችሁ*፤ በክርስትና ሕይወታቸው እያደጉ መሄድ ሲገባቸው ለመንፈሳዊ ነገር ልበ ሙትና ዳተኞች ሆነዋል (6፥12)።

5፥12 *በዚህ ጊዜ*፤ አዲስ አማኞች አይደሉም። *የእግዚ አብሔርን ቃል የመጀመሪያ ትምህርት*፤ እዚህ ትምህርቶች በ6፥1-2 ላይ ተዘርዝረዋል (የዚህን ማብ ይመ)። በክርስትና ሕይ ወታቸው እየበሰሉ ለመሄድ ጒዞ ከጀመሩ በኋላ እየተንሸራተቱ ቀድሞ ወደነበሩበት ስፍራ ይመለሳሉ። *ጠንካራ ምግብ* በምዕ 7 ላይ እንደሚገኘው ከባድ ትምህርት ነው።

5፥14 *ለበሰሉ ሰዎች*፤ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያደጉና የጠራ ማስተዋልና የማመዛዘን ችሎታ ያላቸው ክርስቲያኖች ናቸው። *ያላቸው መልካሙን ከክፉው ለመለየት*፤ በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሕፃናት የሆኑ ሰዎች እንዲህ ማድረግ አይችሉም።

6፥1-2 *እንደ ገና መሠረትን አንጣል*፤ እዚህ ላይ ስድስት መሠረታዊ አስተምህሮች ተወሠተዋል፤ እነዚህም (1) *ንስሓ* አንድ ሰው ከኀጢአቱና ከጉቱ ከሆነ ሥርዐት (አማራጭ ትርጒሙን ይመ) እንዲመለስ የሚያደርግ ፍጹም ለውጥ ነው። (2) *በእግዚአብሔር ስለ ማመን*፤ የንስሐ ሌላው ገጽታ ነው። ንስሓ ከኀጢአት ጨለማ መመለስ እንደ ሆነ ሁሉ፣ እምነት ደግሞ ወደ እግዚአብሔር ብርሃን መመለስ ነው። (3) *ስለ ጥምቀቶች*፤ የመልእክቱ ተደራሲዎች የሚያውቁአቸው ልዩ ልዩ ጥምቀቶች ሳይሆኑ አይቀሩም፤ እነርሱም አሕዛብ የአይሁድ እምነት ሲቀበሉ የሚጠመቁት ጥምቀት፣ መጥምቁ ዮሐንስ ያጠ መቀው ጥምቀትና ኢየሱስ ያዘዘው ጥምቀት ናቸው (ማቴ28፥19)። (4) *እጆችን ስለ መጫን*፤ አንዳንድ ጊዜ ከጥምቀት በኋላ የሚፈ ጸም ሥርዐት ነው (ሐሥ 8፥16-17፤19፥5-6)። አለበለዚያ እጅ የሚጫነው ሰዎችን ለተለየ አገልግሎት ለመሾም ወይም ለመሳክ (ሐዋ 6፥6፤13፥3፤ 1ጢሞ 5፥22፤ 2ጢሞ 1፥6 ይመ)፣ ወይም ሕመ ማዊን ለመፈወስና (ማር 6፥5፤ 16፥18፤ ሉቃ 4፥40፤ ሐሥ 28፥8 ይመ) ቡራኬ ለመስጠት (ማቴ 19፥13-15 ይመ) ነው። (5) *ስለ ሙታን ትንሣኤና*፤ በመጨረሻው ቀን ሰዎች ሁሉ የሚያገኙትን ትንሣኤ ነው (ዮሐ 5፥25-29፤11፥25፤ 2ቆሮ 4፥14 ይመ)። (6) *ስለ ዘላለም ፍርድ*፤ የእግዚአብሔርን የማዳን ጸጋ በመናቅ በክፋ መንገዳቸው የቀጠሉትን ነው።

6፥1 *ስለ ክርስቶስ የተሰጠውን የመጀመሪያ ትምህርት*፤ የ5፥12 ማብ ይመ።

፩፥3፤ በእግዚአብሔር ላይ መታመንን የሚገልፅ የተለመደ አባባል ነው (1ቆሮ 16፥17 ጋር ያነጻጽሩ)። የሰዎችን አእምሮና ልብ መክፈትና መንፈሳዊ ብስለትን ማምጣት የሚችል ጌታ ብቻ ነው።

፩፥4-፮፤ ይህን ክፍል አስመልክቶ የሚሰጡት የታወቁት ትርጓሜዎች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፤ (1) ክፍሉ የሚናገረው በእርግጥ ድነታቸውን ስላጡ ሰዎች ነው። (2) በመንፈሳዊ ሕይ ወታቸው ብስለት ያላሳዩትን የክብረ-ወሰን ክርስቲያኖች (5፥11-14)፤ በነገር ሁሉ እያደጉና እየበሰሉ መሄድ እንዳለባቸው የሚያሳስብ ሲሆን (በቁ•1 ይመ)፣ ይህ ሳይሆን ቢቀር እግዚአብ ሔር እንደሚቀጣቸውና እንደሚፈርድባቸው (ቁ•7-8 ይመ) የሚገልጽ ግምታዊ ሐሳብ ነው። (3) ክርስቲያኖች ነን ሲሉ የነበሩ ትንና በኋላ ግን ከሀደታቸው፣ እምነታቸው ቀድሞውኑ እውነ ተኛ እንዳልሆነ ያሳየውን የሚያመለክት ነው (ከ1ዮሐ2፥19 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ አመለካከት ከም3-4 ያለውን ክፍል የሚያየው እንደ ማስጠንቀቂያ ሲሆን፣ ለዚህም መሠረት ያደረገው እስራ ኤላውያን በምድረ በዳ ሳሉ የፈጸሙትን ዐመፅ ነው። እስራኤል የተስፋይቱን ምድር ከሰለችና ፍሬዋንም ከቀመሰች በኋላ ወደ ምድሪቱ መግባት እንዳልቻሉት ሁሉ፣ እኛም አማኞች ነን የሚሉት የዕብራውያን ክርስቲያኖች ከበራላቸው "ብርሃን" በልበ ደንዳናነት ዘወር ካሉ ንስሓ መግባት አይችሉም።

6፥5 *የሚመጣውን ዓለም*፤ ማር 10፥30 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም 1ጢሞ 6፥19 ይመ።

፩፥7-፰፤ ከፍ ብሉ የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ በአጭሩ የሚገልጽ ሥዕላዊ ምሳሌ ነው (ዮሐ 15፥5-6፤ 2ጴጥ 2፥20-21፤

[8]ነገር ግን እሾህና አሜከላ የምታበቅል መሬት ዋጋ ቢስ ትሆናለች፤ መረገሚያ ዋም ተቃርቦአል፤ መጨረሻዋም በእሳት መቃጠል ነው።

[9]ወዳጆች ሆይ፥ ምንም እንኪ እንደዚህ ብንናገርም፣ ከድነታችሁ ጋር የተያያዘ ታላቅ ነገር እንዳላችሁ እርግጠኞች ነን። [10]እግዚአብሔር ዐመፀኛ አይደለም፤ እርሱ ሥራችሁን እንዲሁም በፊትም ሆነ አሁን ቅዱሳንን በመርዳት ስለ ስሙ ያሳያችሁትን ፍቅር አይረሳም። [11]የተሰጠው ተስፋ እስኪ ፈጸም ድረስ እያንዳንዳችሁ እንዲህ ያለውን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመ ኛለን። [12]በእምነትና በትዕግሥት የተስፋ ውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንድትሆኑ አንፈልግም።

የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል እርግጠኝነት

[13]እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ በሰጠው ጊዜ፣ የሚምልበት ከእርሱ የሚበልጥ ሌላ ባለ መኖሩ፣ በራሱ ማለ፤ [14]እንዲህም አለ፤ "በእርግጥ አባርክህለሁ፤ ዘርህንም አበዛዋለሁ።" [15]አብርሃምም በትዕግሥት ከጠበቀ በኋላ የተ ሰጠውን ተስፋ አገኘ።

[16]ሰዎች ከእነርሱ በሚበልጥ ይምላሉ፤ መሐላውም የተባለውን ነገር ስለሚያጸና፣ በመካከላቸው የተነሣው ክርክር ሁሉ ይወ ገዳል። [17]እግዚአብሔር የማይለወጥ ዐላማውን ለተስፋው ቃል ወራሾች ግልጽ ለማድረግ ስለፈለገ፣ በመሐላ አጸናው፤ [18]እግዚአብሔር ከቶ ሊዋሽ አይችልም፤ እርሱ በሁለት በማ ይለወጡ ነገሮች በፊታችን ያለውን ተስፋ ለመያዝ ወደ እርሱ ለሸሸን ለእኛ ብርቱ መጽናናት እንድናገኝ አድርጎአል። [19]እኛም የኋስ መልሕቅ የሆነ ጽኑና አስተማማኝ ተስፋ አለን፤ ይህም ተስፋ ከመጋረጃው በስተጀርባ ወዳለው ውስጠኛ መቅደስ ይገባል። [20]ይህም ስፍራ ኢየሱስ ስለ እኛ ቀድሞ የገባበት ነው። እርሱም እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ሊቀ ካህናት ሆኖአል።

ካህኑ መልከ ጼዴቅ

7 ይህ መልከ ጼዴቅ የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር፤ እርሱም አብርሃም ነሥታትን ድል አድርጎ ሲመለስ አግኝቶት ባረከው፤ [2]አብርሃምም ከሁሉ ነገር ዓሥራት አውጥቶ ሰጠው። በመጀመ ሪያ ስሙ "የጽድቅ ንጉሥ" ማለት ነው፤ ኋላም ደግሞ "የሳሌም ንጉሥ" ማለትም "የሰላም ንጉሥ ማለት" ነው። [3]አባትና እናት ወይም የትውልድ ሐረግ የለውም፤ ለዘመኑ መጀ መሪያ፣ ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም፤ ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ልጅ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል።

[4]እስቲ እርሱ የቱን ያህል ታላቅ እንደ ሆነ ዐስቡ፤ ርእሰ አበው የሆነው አብር ሃም እንኪ ካገኘው ምርኮ ዓሥራት አው ጥቶ ሰጠው። [5]ክህነት የተሰጣቸው የሌዊ ልጆች ምንም እንኪ ወንድሞቻቸው የአብ ርሃም ዘሮች ቢሆኑም፣ ከሕዝቡ ማለት

6፥8 ዘፍ3፥17፣18፤ ኢሳ5፥6፤27፥4
6፥9 1ቆሮ10፥14
6፥10 ማቴ10፥40፣42፤ 1ተሰ1፥3
6፥11 ዕብ3፥6
6፥12 2ተሰ1፥4፤ ዕብ10፥36፤13፥7፤ ያዕ1፥3፣6፤13፥10፤ 14፥12
6፥13 ዘፍ22፥16፤ ሉቃ1፥73
6፥14 ዘፍ22፥17
6፥15 ዘፍ21፥5
6፥16 ዘፀ22፥1
6፥17 ቊ፡18፤ መዝ110፥4፤ሮሜ 4፥16፤ዕብ11፥9
6፥18 ዘኍ23፥19፤ ቲቶ1፥2፤ዕብ3፥6
6፥19 ዘሌ16፥2፤ ዕብ9፥2፡3፡7
6፥20 ዕብ2፥17፤ 4፥14፤5፥6
7፥1 ቊ፡61 ዘፍ14፥18-20፤ መዝ76፥2፤ሚር5፥7
7፥3 ቊ፡61ማቴ4፥3
7፥4 ዘፍ14፥20፤ ሐሥ2፥29
7፥5 ዘኍ18፥21፡26

1ዮሐ 5፥16 ይመ)።

6፥9፤ *ከድነታችሁ ጋር የተያያዘ ታላቅ ነገር እንዳላችሁ እርግጠኞች ነን*፤ ምንም እንኪ የመልእክቱ ጸሐፊ፣ ከተደራሲ ዎቹ መካከል አንዳንዶቹ ገና ድነት ያልተከበሉ መሆንቸውን ቢናገርም፣ እግዚአብሔር በመካከላቸው እንደሚሠራ እርግጠኛ ነው። የተለወጠው ሕይወታቸውና የፍቅር ሥራቸው(ቊ. 10) በእርግጥም ብዚዎቹ ዳግም ልደት ያገኙ መሆናቸውን ይመሰክራል።

6፥11 *እስከ መጨረሻ* በእምነታቸው እስከ መጨረሻ ጸንተው እንዲገኙ የቀረበ ጥሪ ነው፤ ምክንያቱም ድነት እንደ ተቀበሉ የሚያረጋጡት ጸንተው ሲገኙ ነው። *የተሰጠው ተስፋ*፤ 11፥1፤ 2ጴጥ 1፥10 ይመ።

6፥12 *በእምነትና በትዕግሥት የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን*፤ እነማን እንደሆኑ ምዕ11 ይመ።

6፥13 *እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ በሰጠው ጊዜ*፤ ዘሩን እንደሚያበዛለት የሰጠውን ተስፋ ያጸናለት በመሐላ ነው፤ ይህም ተስፋው የማይለወጥ መሆኑን ያረጋግጣል (ዘፍ 22፥16-18 ይመ)። በመሠረቱ መሐላ በጎጢያት የወደቁ ሰዎች መለያ ነው፤ ምክንያቱም የሰዎች ቃል ሁልጊዜ የሚታመን አይደለም። እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል በመሐላ ሲያጸና ራሱን በወደቁ ሰዎች ደረጃ ዝቅ አድርጎአል፤ በዚህ ዐይነት ፍጹም ታማኝ የሆነውን ቃሉን ይበልጥ ታማኝ አደረገ (ቊ. 18 ይመ)።

6፥15 *በትዕግሥት ከጠበቀ በኋላ*፤ ሐ25 ዓመት ጠብቋል (ዘፍ 12፥3-4፤ 21፥5 ይመ)። *የተሰጠውን ተስፋ አገኘ*፤ ልጁ ይስሐቅ ተወለደ ነው (ዘፍ 17፥2፤18፥10፤21፥5)።

6፥18 *በሁለት በማይለወጡ ነገሮች*፤ ፍጹም ታማኝ የሆነውን የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃልና ተስፋውን የሚያጸና ውን የእግዚአብሔርን መሐላ ነው። *ብርቱ መጽናናት እንድ ናገኝ አድርጎአል*፤ የምንጽናናው አብርሃም በተስፋ ብቻ ያየውን (11፥13፤ ዮሐ 8፥56) የተስፋውን ቃል ፍጻሜ ወይኋላ ተመልሰን መመልከት ስለምንችል ነው።

6፥19 *የኋስ መልሕቅ የሆነ ጽኑና አስተማማኝ*፤ መልሕቅ አንድ መርከብ ስፍራዋን ጠብቃ እንድትቆም እንደሚያደርግ ሁሉ፣ በክርስቶስ ያለን ተስፋም የድኅነታችን ዋስትና ነው። *ከመጋረጃው በስተጀርባ ወዳለው ውስጠኛ መቅደስ*፤ የመርከቦች መልሕቅ የሚጣለው ወደ ታች ወደ ባሕሩ ወለል ሲሆን፣ የክር ስቲያኖች መልሕቅ ግን ወደ ላይ ወደ እውነተኛዪቱ ሰማያዊት መቅደስ በመሄድ በራሱ በእግዚአብሔር ላይ ይታሰራል።

6፥20 *እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ሊቀ ካህናት*፤ የመልእክቱ ጸሐፊ በሰፊው የሚያብራራው ዐቢይ ጭብጥ ነው (ምዕ 7)።

7፥1 *መልከ ጼዴቅ*፤ ዘፍ 14፥18-20 እና ማብ ይመ። *ንጉሥና...ካህን*፤ መልከ ጼዴቅ ንጉሥም ካህንም መሆኑ ልዩ ትኵረት ተሰጥቶታል፤ ይህም የክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ ከቀረበባቸው መንገዶች አንዱ ነው። *የሳሌም*፤ ኢየሩሳሌም ማለት ነው (የዘፍ 14፥18 ማብ ይመ)።

7፥2 *የጽድቅ ንጉሥ...የሰላም ንጉሥ*፤ ለመሲሑ የተሰጡ መጻሪጋት ናቸው (ኢሳ 9፥6-7፤ ኤር 23፥5-6፤ 33፥15-16 ይመ)።

7፥3 *አባትና...የለውም...ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም*፤ በመጀመሪያዎቹ የዘፍጥረት ምዕራፎች ውስጥ ከምናየው ነገር የተለየ ሲሆን፣ በዘፍ 14፥18-20 ላይ ስለ መልከ ጼዴቅ የትውልድ ሐረግም ሆነ የልጅነት ዘመን ወይም ሥራ፣ ስደቱም ሆነ ሞቱ ምንም የጠቀሰ ነገር የለም። በአንዳንድ ወቅት ይኖር የነበረ ሠሙ ስለመሆኑ ግን ግልጽ ነው፤ የዕብራውያን መልእክት ጸሓፊ (የአይሁድን ትርጓሜ በመከተል) ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መልከ ጼዴቅ የትውልድ ሐረግ ሳይናገሩ በዝምታ ቢያልፉም፣ ያን ዝምታ መሠረት በማድረግ መልከ ጼዴቅ የክርስቶስ ምሳሌ መሆኑን ይናገራል። የመልከ ጼዴቅ ክህነት፣ ክርስቶስ ዘላለ ማዊና ክህነቱም ፍጻሜ እንደሌለው ያሳያል። አንዳንድ ሰዎች መልከ ጼዴቅ ለአብርሃም መታየቱን፣ ክርስቶስ ሥጋ ከመልበሱ በፊት ለሰዎች ይገለጥ ነበር ከሚለው ጋር በማያያዝ፣ ለአብርሃም የተገለጠለት ክርስቶስ ነው የሚል እምነት አላቸው፤ ሆኖም "እንደ እግዚአብሔር ልጅ" የሚለው ማነጻጸሪያ ይህ አባባል ትክክል እንዳልሆነ ያመለክታል።

7፥4 *እስቲ እርሱ የቱን ያህል ታላቅ እንደ ሆነ ዐስቡ*፤ ዓሥራት የሚቀበል ዓሥራት ከሚሰጥ ይልቅ እንደሚበልጥ የታወቀ ነው፤ ደግሞም "ትንሹ በትልቁ እንደሚባረክ ግልጽ ነው" (ቊ. 7)። በሁለቱም መንገድ ሲሆን መልከ ጼዴቅ ከአብርሃም ይበልጣል።

ከገዛ ወንድሞቻቸው ዓሥራት እንዲቀበሉ ሕጉ ያዛል። [6]ይህ ግን ትውልዱ ከሌዊ ወገን አይደለም፤ ይሁን እንጂ ከአብርሃም ዓሥራት ተቀበለ፤ የተስፋ ቃል የተቀበለው ንም ባረከው። [7]ትንሹ በትልቁ እንደሚባረክ ጥርጥር የለውም። [8]በአንድ በኩል ዓሥራት የሚቀበሉት ሟች ሰዎች ናቸው፤ በሌላ በኩል ግን ሕያው ሆኖ እንደሚኖር የተመ ሰከረለት ይቀበላል። [9]እንዲያውም ዓሥ ራት የሚቀበለው ሌዊ፤ ራሱ በአብርሃም በኩል ዓሥራት ከፍሎአል ማለት ይቻላል፤ [10]ምክንያቱም መልከ ጼዴቅ አብርሃምን ባገኘው ጊዜ፣ ሌዊ ገና በአባቱ በአብርሃም አብራክ ነበር።

ኢየሱስ እንደ መልከ ጼዴቅ

[11]ፍጹምነት የተገኘውና ሕጉ ለሕዝቡ የተሰጠው በሌዊ ክህነት መሠረት ቢሆን ኖሮ፣ እንደ አሮን ሳይሆን እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ያለው ሌላ ካህን መምጣቱ ለምን አስፈለገ? [12]ክህነት ለውጥ ካለ ሕጉም ሊለወጥ ግድ ነውና። [13]ይህ ሁሉ የተነገረ ለት እርሱ ከሌላ ነገድ ነው፤ ከዚያም ነገድ በመሠዊያ ያገለገለ ማንም የለም። [14]ጌታ ችን ከይሁዳ ነገድ እንደመጣ ግልጽ ነውና፤ ሙሴ ስለ ካህናት ሲናገር ይህን ነገድ አስመ ልክቶ የተናገረው ምንም ነገር የለም። [15]እንደ መልከ ጼዴቅ ያለ ሌላ ካህን ቢነሣ ግን እኛ የተናገርነው ይበልጥ ግልጽ ይሆናል፤ [16]እርሱ ካህን የሆነው በማይጠፋ የሕይወት ኀይል መሠረት እንጂ፣ እንደ ትውልዱ የሕግ ሥር ዐት አይደለም፤ [17]እንዲህ ተብሎ ተመስክ ሮለታል፤

"እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት፣
አንተ ለዘላለም ካህን ነህ።"

[18]የቀድሞው ትእዛዝ ደካማና የማይጠ ቅም በመሆኑ ተሽሮአል፤ [19]ሕጉ ማንንም ፍጹም ሊያደርግ ስለማይችል ወደ እግዚ አብሔር የምንቀርብበት የተሻለ ተስፋ መጥ ቶአል።

[20]ይህ ያለ መሐላ አልሆነም፤ ሌሎች ካህ ናት የሆኑት ያለ መሐላ ነው፤ [21]እርሱ ግን ካህን የሆነው በመሐላ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ተናግሮለታል፤

"ጌታ ማለ፤
ዐሳቡንም አይለውጥም፤
'አንተ ለዘላለም ካህን ነህ።' "

[22]ከዚህ መሐላ የተሥግ፣ ኢየሱስ ለተሻለ ኪዳን ዋስ ሆኖአል።

[23]በአገልግሎታቸው እንዳይቀጥሉ ሞት ስለ ከለከላቸው፣ የቀድሞዎቹ ካህናት ቍጥ ራቸው ብዙ ነበር፤ [24]ኢየሱስ ግን ለዘላለም የሚኖር በመሆኑ፣ ክህነቱ የማይሻር ነው። [25]ስለዚህ ስለ እነርሱ እየማለደ ሁልጊዜ በሕይወት ስለሚኖር፣ በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያ ድናቸው ይችላል።

[26]እንግዲህ ለእኛ የሚያስፈልገን፣ ቅዱስ፣ ነቀፋ የሌለበት፣ ንጹሕ፣ ከኀጢአተኞች የተ ለየና ከሰማያት በላይ የከበረ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ነው። [27]እርሱም እንደ ሌሎቹ ሊቃነ ካህናት፣ መጀመሪያ ስለራሱ ኀጢ አት ከዚያም ስለ ሕዝቡ ኀጢአት በየቀኑ መሥዋዕት ማቅረብ አያስፈልገውም፤ ራሱን በሰጠ ጊዜ፣ ስለ ኀጢአታቸው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መሥዋዕት አቅርቦአልና። [28]ሕጉ ደካማ የሆኑትን ሰዎች ሊቃነ ካህ ናት አድርጎ ይሾማልና፤ ከሕግ በኋላ

7፥6 ዘፍ14፥19፡20፤ ሮሜ4፥13
7፥8 ዕብ5፥6፤6፥20
7፥11 ቍ.17፡8፥19፤ ዕብ5፥6፡8፥7፡10፥1
7፥13 ቍ.11፡14
7፥14 ኢሳ11፥1፤ ማቴ1፥3፡2፥6፤ ሉቃ3፥33፤ራእ5፥5
7፥17 ቍ.21፤ መዝ110፥4፤ዕብ5፥6
7፥18 ሮሜ8፥3
7፥19 ቍ.11፡25፤ ሮሜ3፥20፤
7፥7፡3፣ገላ3፥21፤ ዕብ3፥6፡4፥16፤ 9፥9፡10፥1፣22፤ያዕ4፥8
7፥21 ዘኍ23፥19፤ 1ሳሙ15፥29፤መዝ110፥4፤ሚል3፥6፤ ሮሜ11፥29፤ዕብ5፥6
7፥22 ሉቃ22፥20
7፥24 ቍ.28
7፥25 ቍ.19፤ ሮሜ8፥34፡11፥14
7፥26 2ቆሮ5፥21፤ ዕብ2፥17፡4፥14
7፥27 ሮሜ6፥10፤ ኤፌ5፥2፤ዕብ5፥1፡ 3፥9፡12፡14፡ 26፡28፡10፥10፤ 1ጴጥ3፥18
7፥28 ዕብ1፥2፤ 2፥10፡5፥2

[0]25 ወይም ለዘላለም

7፥11 *መሠረት ቢሆን* በሌዋውያን ክህነት መሠረት ነው። ሕጉ ... *የተሰጠውን* የሙሴ ሕግና ክህነት አብረው የሚ ሄዱ ናቸው። ሰዎች ሁሉ ኀጢአተኞች በመሆናቸው ከሕግ ኮነኔ ሥር ናቸው፤ ስለዚህ በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል ሆኖ የሚ ማልድ ሥርዐተ ክህነት የግድ ያስፈልጋቸዋል። *እንደ አሮን ሳይሆን እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት*፣ የአሮን (የሌዋውያኑ) ክህ ነት ፍጹም አለመሆኑን፣ ባንጻሩም የመልከ ጼዴቅ ግን ፍጹም እንደሆነ ያመለክታል። ለዘላለም ካህን የሚሆነው እንደሚመጣ የተነገረው (መዝ 110፥10) የሌዋውያኑ ክህነት አገልግሎት በመ ስጠት ሳይ እያለ ነው፤ ይህም አሁን ያለው ሥርዐተ ክህነት ወደ ፊት በሚመጣው የተሻለ ክህነት እንደሚተካ ያሳያል።

7፥16 *ካህን የሆነው*...*እንደ ትውልዱ የሕግ ሥርዐት አይደለም*፤ በሙሴ ሕግ መሠረት በክህነት ማገልገል የሚችሉት ከሌዊ ወገን የሆኑ ብቻ ናቸው (ዘፃ 18፥1)፤ ኢየሱስ ግን የመጣው የክህነት አገልግሎት ካልተሰጠው ከይሁዳ ነገድ ነው (ቍ. 14-15)። *በማይጠፋ የሕይወት ኀይል*፤ በመዝ 110፥4 መሠረት በመልከ ጼዴቅ ሹመት ሥርዐት የሚመጣ ካህን "የዘላለም ካህን" ነው።

7፥18 *የቀድሞው ትእዛዝ ደካማና የማይጠቅም በመሆኑ*፤ ሕጉ ቅዱስና መልካም ነው (ሮሜ 7፥12)፤ ይሁን እንጂ ሕጉን በመተላለፍ ኀጢአት የሚሠሩትን ሊያጸድቃቸው ወይም ሕጉ የሚጠይቀውን ሁሉ ለመፈጸም የሚያስችል ኀይል ሊሰጣቸው አይችልም (ሥ. 19)።

1፥19፤ ሕጉ ወደ ፊት ለሚመጣው የሚያዘጋጅ ብቻ እንጂ (ገላ 3፥23-25 ይመ) ፍጹም ሊያደርግ አይችልም (ማቴ 5፥17 ይመ)። *የተሻለ ተስፋ*፤ አዲሱ ኪዳን የተሻለ ነው፤ ምክንያቱም ያገኘነው ቤዛነት ፍጹምና ወደ እግዚአብሔርም ፊት ሊያቀርበን የሚችል መሆኑን ያረጋግጥልናል። የቍላ 1፥5 ማብ ይመ።

7፥20፤ የሌዋውያኑ ክህነት ሲመሠረት እግዚአብሔር አል ማለም። በመዝ110 ላይ ቃል የተገባው ክህነት በመሐላ የጸና በመሆኑ እጅግ የላቀ ነው።

7፥22 *ለተሻለ ኪዳን*፤ ምዕ8-10 ይመ።

7፥23 *በአገልግሎታቸው እንዳይቀጥሉ ሞት ስለ ከለከላ ቸው*፤ የሌዋውያኑ ሥርዐተ ክህነት ፍጹም እንዳልሆነ የሚያሳይ ተጨማሪ ማስረጃ ነው።

7፥25 *ፈጽሞ* ፍጹምነትና ሙሉነት የሚለውን ሐሳብ ሊይዝ ይችላል፤ አማራጭ ትርጒሙን ይመ። ኢየሱስ ለዘላለም ፍጹም ሊቀ ካህናት ነው፤ በመሆኑም ሁልጊዜ ሊያድነን ይችላል። *እየማለደ ሁልጊዜ በሕይወት ስለሚኖር*፤ ሕዝቡ ያለ ካህን የሚሆንበት ጊዜ አይኖርም (ዮሐ 17፤ 1ዮሐ 2፥1 ይመ)።

7፥26 *የሚያስፈልገን*፤ ከኀጢአትና ኀጢአት ከሚያስ ከትለውም ቅጣት ሊታደገን የሚችል ነው።

7፥27 *በየቀኑ*፤ ዓመቱን በሙሉ ያለማቋረጥ የሚቀርበውን *መሥዋዕት* የሚያመለክት ሲሆን (ዘፀ 29፥36-42)፤ ይህም *መሥዋዕቱ* በማያዳግም ሁኔታ ለኀጢአት መፍትሔ ሊሰጥ እንደማይችል አንዱ ማስረጃ ነው። *መጀመሪያ ስለ ራሱ ኀጢአት*፤ ኀጢአት የሌለ በት ስለ ሆነ፣ ስለ ራሱ መሥዋዕት ማቅረብ አያስፈልገውም፤ ስለ ዚህም የክርስቶስ ክህነት የላቀ ነው። *ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ*፤ በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ቍልፍ ሐረግ ነው (9፥12፤26፤ 10፥2፤10 ይመ)። ሊቀውያን ካህናት በየዕለቱ ለእግዚአብሔር መሥ ዋዕት ማቅረብ ነበረባቸው፤ ኢየሱስ ግን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ራሱን *መሥዋዕት* አድርጎ አቀረበ። *ራሱን በሰጠ ጊዜ*፤ ሌዋው ያን ካህናት መሥዋዕት አድርገው የሚያቀርቡት እንስሳትን ብቻ ሲሆን፣ የእኛ ሊቀ ካህን ግን ራሱን መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ፤ በዚህ ዐይነት ፍጹም ምትክ ሆነን።

7፥28 *ደካማ የሆኑትን ሰዎች*፤ ደካማ የሆኑት (1) ሟችና ከዚህም የተነሣ ዘላለማዊነት የሌላቸው በመሆኑ ቍ. 23፤ (2)

የመጣው መሐላ ግን ለዘላለም ፍጹም የሆነ ውን ልጅ ሾሞአል።

የአዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት

8 እንግዲህ የምንናገረው ዋናው ነገር ይህ ነው፤ በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት አለን፤ 2እርሱም በሰው ሳይሆን በጌታ በተተከለ ችው፣ እውነተኛ ድንኳን በሆነችው ቤተ መቅደስ አገልጋይ ነው።

3እያንዳንዱ ሊቀ ካህናት የሚሾመው መባንና መሥዋዕትን ለማቅረብ ነው፤ ስለ ዚህ ይሸኟውም ካህን የሚያቀርበው ነገር ያስፈልገዋል። 4እርሱ በምድር ቢኖር ኖሮ ካህን ባልሆነም ነበር፤ ምክንያቱም በሕግ በታዘዘው መሠረት መባን የሚያቀርቡ ሰዎች አሉ። 5እነርሱ ያገለገሉት በሰማይ ላለችው መቅደስ ምሳሌና ጥላ በሆነችው ውስጥ ነው፤ ሙሴ ድንኳኒቱን ለመሥራት በተ ነሣ ጊዜ፣ "በተራራው ላይ በተገለጠልህ ምሳሌ መሠረት ሁሉን ነገር እንድታደርግ ተጠንቀቅ" የሚል ትእዛዝ የተሰጠው በዚህ ምክንያት ነበር። 6ነገር ግን ኢየሱስ መካከ ለኛ የሆነበት ኪዳን ከቀድሞው እንደሚበ ልጥ ሁሉ፣ የተቀበለውም አገልግሎት ከእነ ርሱ አገልግሎት ይበልጣል፤ ይህም የተመ ሠረተው በተሻለ የተሰፋ ቃል ላይ ነው።

7የመጀመሪያው ኪዳን ምንም ጒድለት ባይኖበት ኖሮ፣ ለሁለተኛው ስፍራ ባለተፈ ለገም ነበር። 8ነገር ግን እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ጒድለት በማግኘቱ እንዲህ ይላቸዋል፤

"ከእስራኤል ቤት ጋር፣
ከይሁዳም ቤት ጋር፣
አዲስ ኪዳን የምገባበት፣
ጊዜ ይመጣል፤
ይላል ጌታ።
9ይህም እነርሱን ከግብፅ ምድር ለማውጣት
እጃቸውን በያዝሁ ጊዜ፣
ከቀድሞ አባቶቻቸው ጋር እንደ ገባሁት ኪዳን
አይደለም፤
ምክንያቱም እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑም፤
እኔም ከእነርሱ ዘወር አልሁ፤
ይላል ጌታ።
10ከዚያን ጊዜ በኋላ፣
ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ኪዳን
ይህ ነው፤
ይላል ጌታ፤
ሕጌን በአእምሮአችው አኖራለሁ፤
በልባቸውም እጽፈዋለሁ።
እኔ አምላካቸው እሆናለሁ፤
እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ።
11ከእንግዲህ ማንም ሰው ጐረቤቱን ወይም
ወንድሙን፣
'ጌታን ዕወቅ' ብሎ አያስተምርም፤
ምክንያቱም ከታናሹ ጀምሮ እስከ
ታላቁ ድረስ፣
ሁሉም ያውቁኛል።
12በደላቸውን ይቅር እላለሁ፤ ኀጢአታቸውን
ከእንግዲህ አላስብም፤
13ይህን ኪዳን፣ "አዲስ" በማለቱ የፊተ
ኛውን ኪዳን አርጌ አድርጎታል፤ ስለዚህ
ያረጀ ያፈጀው የሚጠፋበት ጊዜ ተቃርቦአል።

8፥1 ግር16፥19፤ ዕብ2፥17፤4፥14
8፥2 ዕብ9፥11፡24
8፥3 ዕብ2፥17፤5፥1፡9፥9፡14
8፥4 ዕብ5፥1፡9፡9
8፥5 ዘፀ25፥40፤ ቈላ2፥17፤ዕብ9፥23፤10፥1፡11፥7፡12፥25
8፥6 ቍ8፡13፤ ሉቃ22፥20፤ገላ3፥20
8፥7 ዕብ7፥11፡18፤10፥1
8፥8 ቍ6፡13፤ ሉቃ22፥20
8፥9 ዘፀ19፥5፡6፤ 20፥1-17
8፥10 ሕዝ11፥20፤ ዘካ8፥8፤ሮሜ 11፥27፤2ቆሮ3፥3፤ ዕብ10፥16
8፥11 ኢሳ54፥13፤ ዮሐ6፥45
8፥12 ኤር31፥31-34፤ ዕብ10፥17
8፥13 ቍ6፡8፤ ሉቃ22፥20፤2ቆሮ5፥17

ኀጢአተኞች በመሆናቸውና ቍ. 27፤ (3) ማቅረብ የሚችሉት መሥዋዕት እንስሳትን ብቻ በመሆኑና እንሳሳት ደግሞ በእግዚ አብሔር አምሳል ለተፈጠረ ሰው፣ ትክክለኛ ምትክ መሆን ስለ ማይችሉ ነው (ዘፍ 1፥26-28 እና ማብ ይመ)። *ለዘላለም ፍጹም የሆነውን* ክርስቶስ ፍጹም ሊሆን የቻለው በኀጢአት ሳይሸነፍ ፈተናን በመቀበሉ ነው (ዕ2፥10፤5፥8 ማብ ይመ)። ይልቁንም አባቱን ፍጹም በመታዘዙ፣ ዘላለማዊ ፍጽምናን መውረሱ።

8፥1-10፥39፤ የዚህ ክፍል ዐቢይ ሀሳብ የሠረገው በኤር 31፥31-34 ከተሰጠው ትንታኔ ሲሆን፣ ክርስቶስ "ለተሻለ ኪዳን" መካከለኛ መሆኑን አጉልቶ የሚያሳይ ነው (7፥22)።

8፥1፤ የ1፥2-3 ማብ ይመ። *በሰማያት በግርማው፤* አይ ሁድ እግዚአብሔርን ለማመልከት የሚጠቀመበት አባባል ነው (1፥3 ይመ)።

8፥2 *እውነተኛ ድንኳን*፣ ሙሴ ከተከላት ፍጹምና ዘላለ ማዊ ካልሆነችው እንዲሁም ለሰማያዊቷ ድንኳን ምሳሌ ከሆነ ችው ጋር ሲነጻጸር ነው። *በሰው ሳይሆን በጌታ በተተከለችው፤* እግዚአብሔር የሠራት ሰማያዊቷ ድንኳን ሙሴ ከሠራትና ሊቀ ካህኑ በዓመት አንድ ጊዜ የማስተስረያውን ደም ይዞ ከሚገባበት ቅድስትና ቅድስተ ቅዱሳን ጋር ትመሳሰላለች (ዘሌ 16፥13-15፤ 34)። ታላቁ ሊቀ ካህናችን ግን አማላጃችን ሆኖ በሰማያዊቷ መቅደስ ውስጥ ለዘላለም ይኖራል (7፥25)።

8፥3 *መባንና መሥዋዕትን*፣ የ5፥1 ማብ ይመ።

8፥4 *ካህን ባልሆነም ነበር*፣ ክርስቶስ በሥጋ የተወለደው ከይሁዳ ነገድ ነው፤ የይሁዳ ነገድ ደግሞ ከካህናት ወገን አይደለም (7፥12-14 ይመ)። *መባን የሚያቀርቡ ሰዎች*፣ ከሌሎ ነገድ የሆኑ ናቸው እዚህም ላይ ሆነ በመልእክቱ ውስጥ በሌላ ስፍራ የሚያቀርቡ የሚለው የአሁን ጊዜ ግስ የሚያመለክተው በኢየሩሳሌም የሚገኘው ቤተ መቅደስ እንደቆመ ነው። እንግዲህ ይህ መልእክት የተጻፈው ቤተ መቅደሱ በ70 ዓ.ም. ላይ ከመፍረሱ በፊት ነው ማለት ነው (በመልእክት "መግቢያ" ላይ "መልእክቱ የተጻፈበት ጊዜና ቦታ" የሚለውን ይመ)።

8፥5 *በሰማይ ላለችው መቅደስ ምሳሌና ጥላ*፣ ሊቀ ካህናችን ክርስቶስ የራሱን ደም ይዞ የገባው ወደ እውነተኛዪቱና እግዚአብሔር ወደሚኖርባት መቅደስ ነው (9፥11-12 ይመ)። *በተገለጠልህ ምሳሌ መሠረት ሁሉን ነገር እንድታደርግ* ድንኳኒቱም ሆነች የእገልግሎቱ ሥርዐት የቀረቡት ኀጢአተኞች ቅዱስ ወደሆነው አምላክ በመቅረብ የሚችሉት በዚህ መንገድ ብቻ መሆኑን በምሳሌ ለመግለጽ ነው።

8፥6 *ሊየሱስ መካከለኛ የሆነበት ኪዳን ከቀድሞው እንደሚበልጥ ሁሉ፤* 9፥15፤ 12፥24፤ 1ጢሞ 2፥5 ይመ። ኢየሱስ መካከለኛ የሆነበት አዲሱ ኪዳን (ቍ. 8-12፤ ኤር 31፥31-34 ይመ) እግዚአብሔር፣ በሊና ተራራ ላይ በሙሴ አማካይነት ከሰጠው ኪዳን ይበልጣል (ዘፀ 24፥7-8 ይመ)። *የተመሠረተው በተሻለ የተሰፋ ቃል ላይ ነው*፤ ቍ. 10-12 ይመ።

8፥7 *የመጀመሪያው ኪዳን ምንም ጒድለት ባይገኝበት ኖሮ*፣ እዚህ ላይ የቀረበው ሐሳብ በ7፥11 ላይ ካለው ጋር ተመሳሳይነት አለው፤ ይኸውም የሌዋውያኑን ሥርዐተ ክህነት እንደሚያንስ በግልጽ ታይቶአል። ምክንያቱም በመልከ ጼዴቅ ሥርዐት በመገው ክህነት ተተክቶአል። በተመሳሳይ ሁኔታ ለሙሴ የተሰጠው ኪዳን ጒድለት ባይኖረው ኖሮ፣ በአዲስ ኪዳን መተካት ባላስፈለገም ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን በሙሴ በኩል የመጣው ኪዳን "ጒድለት" የለበትም። የ7፥17 ይመ።

8፥8-12፤ ከኤርምያስ 31፥31-34 ላይ የተወሰደ ትንቢ ታዊ ዐዋጅና የአዲሱ ኪዳን ትርጓሜ ነው፤ ይህም ኪዳን በሙሴ በኩል ከመጣው ኪዳን ፍጹም ልዩ ነው (ቍ. 9)። ከዚህ ኪዳን የሚገኙት ዐበይት ጥቅሞች፦ (1) የእግዚአብሔር ሕግ የጎሊና መርሕ በመሆን (ቍ. 10)፣ ሕዝቡ ፈቃዱን በመፈጸም ደስ እን ዲላቸው ያደርጋል (ከአዝ 36፥26-27፤ ዘሮሜ 8፥2-4 ጋር ያነጻጽሩ፤ (2) በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ጥብቅ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል (ቍ. 10)፤ (3) እግዚአብሔርን ያለማወቅ ኀጢአት ለዘላለም ይወገዳል (ቍ. 11)፤ እንዲሁም (4) የኀጢአት ይቅርታ ከዘላለም እስከ ዘላለም የሚኖር እውነት ይሆናል (ቍ. 12)።

8፥13 *ያረጀ ያፈጀው*፣ የአዲሱ ኪዳን መታወጅ የቀድሞው ኪዳን ጊዜያዊ መሆኑን ያረጋግጣል። በመሆኑም ወደ

በምድራዊው ድንኳን የሚደረግ አምልኮ

9 የመጀመሪያው ኪዳን የአምልኮ ሥርዐትና ምድራዊ መቅደስ ነበረው። ²ድንኳን ተተክሎ ነበር፤ በመጀመሪያው ክፍል መቅረዙ፣ ጠረጴዛውና የመሥዋዕቱ ኅብስት ነበረበት፤ ይህም ስፍራ ቅድስት ይባላል። ³ከሁለተኛው መጋረጃ በስተኋላ ቅድስተ ቅዱሳን የተባለ ክፍል ነበር፤ ⁴በዚያም ውስጥ የወርቅ ማዕጠንትና በወርቅ የተለበጠው የኪዳኑ ታቦት ነበሩ፤ ይህም ታቦት መና ያለበትን የወርቅ መሶብ፣ የለመለመችውን የአሮንን በትርና ኪዳኑ የተጻፈበትን ጽላት ይዞአል። ⁵በታቦቱም ላይ የስርየት መክደኛውን የሚጋርዱ የክብር ኪሩቤል ነበሩ፤ አሁን ግን ስለ እነዚህ ነገሮች በዝርዝር መናገር አንችልም።

⁶ሁሉም በዚህ መልክ ከተዘጋጀ በኋላ፣ ካህናት አገልግሎታቸውን ለመፈጸም ዘወትር ወደ ድንኳኒቱ መጀመሪያ ክፍል ይገባሉ። ⁷ነገር ግን ወደ ውስጠኛው ክፍል የሚገባው ሊቀ ካህናቱ ብቻ ነበር፤ የሚገባውም በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን፣ ስለ ራሱ ጎጢአትና ሕዝቡ ባለማወቅ ስላደረገው ጎጢአት የሚያቀርበውን ደም ሳይዝ ከቶ አይገባም ነበር። ⁸የመጀመሪያይቱ ድንኳን ቆማ እስካለች ድረስ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚወስደው መንገድ ገና እንዳልተገለጠ መንፈስ ቅዱስ ያሳያል። ⁹ይህም ለአሁኑ ዘመን ምሳሌ ሲሆን፣ የሚቀርቡት መባና መሥዋዕት የሚያመልከውን ሰው ጎሊና ፍጹም ሊያደርጉ አልቻሉም። ¹⁰እነዚህ ሁሉ አዲሱ ሥርዐት እስኪመጣ ድረስ የሚደረጉ የም ግብና የመጠጥ እንዲሁም የተለያዩ የመጠ ንጻት ሥርዐቶች ብቻ ናቸው።

የክርስቶስ ደም

¹¹ክርስቶስ አሁን ስላሉት መልካም ነገ ሮች ሊቀ ካህናት ሆኖ በመጣ ጊዜ በሰው እጅ ወዳልተሠራችው፣ ከዚህ ፍጥረት ወዳ ልሆነችው ታላቅና ፍጹም ድንኳን ገባ። ¹²የገ ባውም የፍየልንና የጥጃዎችን ደም ይዞ አይ ደለም፤ ነገር ግን የዘላለም ቤዛነት ሊያ ስገኝ የራሱን ደም ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱ ሳን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ገባ። ¹³የውጭ አካላቸው ይነጻ ዘንድ በረከሱ ሰዎች ላይ የሚረጨው የፍየሎችና የኮርማዎች ደም እንዲሁም የፍየሎችና የጊደር ዐመድ የሚቀድሳቸው ከሆነ፣ ¹⁴በዘላለም መንፈስ አማካይነት ራሱን ነውር አልባ መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ያቀረበው የክርስቶስ ደም ሕያው እግዚአብሔርን እንድናመልክ ጎሊናችንን ከምውት ሥራ እንዴት ይበ ልጥ ያነጻ ይሆን!

¹⁵ስለዚህም የተጠሩት ተስፋ የተሰጠ ውን የዘላለም ርስት እንዲቀበሉ ክርስቶስ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው፤ በመጀመሪ ያው ኪዳን ሥር በነበሩበት ጊዜ ከሠሩት

9፡1 ዘፀ25፡8
9፡2 ዘፀ25፡8፡9፡ 23-29፡30፡31-39፡ 26፡33፡34፡ዘሌ24፡5-8
9፡3 ዘፀ26፡31-33
9፡4 ዘፀ16፡32፡ 33125፡10-22፡ 30፡1-5፡31፡18፡ 32፡15፡ዘኍ17፡10
9፡5 ዘፀ25፡17-19፡ 20-22፡26፡34
9፡6 ዘኍ28፡3
9፡7 ቀኍ2፡3፡ ዘሌ16፡11-19፡34፡ ዕብ5፡2፡3
9፡8 ዮሐ14፡6፡ ዕብ3፡7፡10፡19፡20
9፡9 ዕብ5፡1፡7፡19፡ 8፡3፡10፡1
9፡10 ዘሌ11፡2-23፡ 25፡28፡40፡ዘኍ6፡31፡ ቁላ2፡16፡
ዕብ2፡17፡8፡2፡10፡1
9፡11 ቀኍ24፡ ዮሐ2፡19፡24፡26፡28፡ ዘሌ16፡6፡15፡ ሮሜ3፡25፡ ዕብ7፡27፡10፡4
9፡13 ዘኍ19፡9፡ 17፡18፡ዕብ10፡4
9፡14 መዝ51፡2፡ 65፡31፤ኢሮ33፡8፡ ዘካ13፡1፡ሮሜ6፡16፡ ኤፌ5፡2፡ ቲቶ2፡14፡ 1ጴጥ3፡18፡ዕብ6፡1፡ 10፡2፡22
9፡15 ሉቃ22፡20፡ ሐሥ20፡32፡ሮሜ 8፡28፡11፡29፡ዊሣ3፡20፡ ዕብ6፡15፡17፡22፡ 10፡36

ᵗ5 ወይም የማስተሰረያውን መክደኛ
ᶜ11 አንዳንድ የጥንት ጽሑፍ ሊመጡ ስላሉት ይላሉ።
ᵇ14 ወይም ከክንቱ የዘመትሮ ሥርዐቶች

ቀደመው ሥርዐት መመለስ ማለት ወዳረጀው ወይም ከጥቅም ውጭ ወደ ሆነው መመለስ ማለት ነው።

9፡2 *ድንኳን ተተክሎ ነበር*፤ በመሴ የተሠራውን ድንኳን ነው። *መቅረዙ* ከቅጥቅም ወርቅ የተሠራና በቅድስት ውስጥ በተቀደሰው ቦታ በስተደቡብ የሚቀመጥና (ዘጸ 40፡24)፣ በየምሽቱ ያለ ማቋረጥ የሚበሩ ሰባት መብራቶች ያሉት ነው (ዘጸ 25፡31-40)። *ጠረጴዛውና የመሥዋዕቱ ኅብስት*፤ ከግራር እንጨት የተሠራና በወርቅ የተለበጠ፣ በቅድስት ውስጥ በስተ ሰሜን የሚቀመጥ ነው (ዘጸ 40፡22)። በኅብስት ማስቀመጫው ጠረጴዛ ላይ በሁለት ረድፍ የተደረደሩ ስድስት ስድስት ኅብስቶች ይገኛሉ (ዘሌ 24፡5-6)።

9፡4 *የወርቅ ማዕጠንትና ...* *ነበሩ*፤ ማዕጠንቱ የተቀ መጠው በቅድስት ውስጥ ቢሆንም፣ የመጨረሻው ጽሑፉ ግን በቅ ድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ እንደሚገኝ አድርጎ ይገልጻል። እንዲህ ያደ ረገው ቅድስተ ቅዱሳኑ ከኪዳኑ ታቦት ጋር ያለውን የቅርብ ግን ኙነት ለማሳየት ነው (ከዘጸ 40፡5፤ ፲ነ 6፡22 *ጋር* ያንጻጽሩ)። ሊቀ ካህኑ በስርየት ቀን ከማዕጠንቱ ላይ ዕጣን በመውሰድና ለጎጢአት ማስተስረያ የሚሆነውን ደም በመያዝ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባል (ዘሌ 16፡12-14)። *የኪዳኑ ታቦት*፤ ከውስጥም ከግ ራር እንጨት ተሠርቶ ከውስጥና ከውጭ በወርቅ የተለበጠ ሣጥን ነው (ዘጸ 25፡10-16)። *መና ... በትሮና ... ጽላት* የዘፀ 16፡33-34 ማብ ይመ፤ እንዲሁም ዘኁ 17፡8-10 ይመ።

9፡5 *የክብር ኪሩቤል*፤ ከንጹሕ ወርቅ የሚሠሩ እያን ጻንጻቸው ሁለት ክንፍ ያላቸው ምስሌችና በስርየት መክደኛው ላይ ከጻርና ጻር ትይዩ የሚቆሙ ናቸው። የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጠው በሁለቱ መካከል ነበር (ዘጸ 25፡17-22፤ ዘሌ 16፡2፤ ዘኁ 7፡89)። *የስርየት መክደኛውን*፤ ከንጹሕ ወርቅ የተሠራና፣ የኪዳኑን ታቦት ሙሉ በሙሉ የሚሸፍን ዝርግ ግጣም ነው፤ ሊቀ ካህኑ በስርየት ቀን የጎጢአት ማስተስረያው ደም የሚረጨው በዚህ ግጣም ላይ ነው (ዘሌ 16፡14-15)።

9፡7 *በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ* በስርየት ቀን (ዮም ኪፑር) በሰባተኛው ወር በዐሥረኛው ቀን ማለት ነው (ዘሌ 16፡29፤34)። በዚህ ቀን ስለሚፈጸመው ሥርዐት ዘሌ 16 እና ማብራሪያዎቹን ይመ።

9፡8 *የመጀመሪያይቱ ድንኳን ቆማ እስካለች ድረስ* የመሴ ሥርዐት ይሽመም፣ ፍጹም ያልሆነው ክህነትና መሥዋዕት እስካለ ድረስ ማለት ነው (8፡7-8፤13)።

9፡9 *ለአሁኑ ዘመን ምሳሌ*፤ ምንም እንኳ የመሴ ድንኳን በሌላ የተተካ ቢሆንም፣ በሥርዐቱ ውስጥ የሚገኙት ትእምርቶች (ምሳሌዎች) ግን፣ አሁንም ትምህርት የሚሰጡና ወደ አርኄው ሥርዐት መመለስ ከንቱ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው፤ አር ኄው ሥርዐት ኅሊናችን ፈጽሞ ሊያስወግድ አይችልምና። *መባና መሥዋዕት*ን የ5፡1 ማብ ይመ።

9፡10 *አዲሱ ሥርዐት*፤ አዲሱን ኪዳንና ከእርሱም ጋር የመጡትን አዲሱን ክህነት፣ አዲሱን ቤተ መቅደስና አዲሱን ሥርዐት ነው፤ ይህ ሁሉ የተገኘው በክርስቶስ ነው።

9፡11 *ከዚህ ፍጥረት ወዳልሆነችው* ምድራዊ ድንኳን ሳትሆን፣ እግዚአብሔር የሚኖርባት ሰማያዊቷ መቅደስ ናት (ቊ 24፡8፡2)።

9፡12 *ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ገባ* ሊዋውያን ሊቀ ካህናት በየዓመቱ በመደጋገም እንደሚያደርጉት አይደለም፤ የክ ርስቶስ መሥዋዕትነት ፍጹም ነው፤ ምክንያቱም የሚሠራና በመደ ጋገም ሊቀርብ የማያስፈልገው ነው። ዘላለማዊ ቤዛነት ከተቀዳጀ በኋላ፣ ክርስቶስ ወደ እውነተኛዪቱ ሰማያዊ ቤተ መቅደስ ዐረገ።

9፡13 *የፍየሎችና የኮርማዎች ደም*፤ በስርየት ቀን የሚቀርብ የእነዚህ እንስሳት ደም ነው። *የጊደር ዐመድ*፤ በዘኍ 19 ላይ እንደተጠቀሰው የሞተ ሰው የነኩ ሰዎች በሥርዐቱ መሠ ረት ስለሚረከሱ የጊደር ዐመድ ይረጫሉ። *የውጭ አካላቸውን* የሚረጩት ውጫዊ አካላቸውን ብቻ ስለ ሆነ፣ እንዲህ ዐይነቱ ሥርዐት ሰውን ከጎጢአቱ አያነጻውም።

9፡14 *ራሱን ... መሥዋዕት አድርጎ ... ያቀረበው* መሥዋዕ ቱን ያቀረበውም ሆነ መሥዋዕቱ እርሱ ራሱ ነው። *ነውር አልባ* ላይ ላዩን ብቻ ሳይሆን፣ መላ እሱነቱ እንከን የሌለበት መሆኑን ለመግለጽ ነው። *ጎሊናችንን ... ያነጻ ይሆን*፣ የጎጢአትን ርኵሰት፣ ከእኝነታችን ውስጥ ጨርሶ ያስወግዳል።

9፡15 *መካከለኛ*፣ 8፡6 እና ማብራሪያውን ይመ፤ ማስታ ወሻውን፤ እንዲሁም 12፡24፤ 1ጢሞ 2፡5 ይመ። *የአዲስ ኪዳን* 7፡22፤8፡6፡13 ይመ። *ተስፋ የተሰጠውን የዘላለም ርስት*፤ ከኢርምያስ ትንቢት (31፡31-34) ላይ ተወስዶ በ8፡8-21 ላይ

ጎጢአት ነጻ ለማውጣት ቤዛ ሆኖ ሞቶ አልፍ።

16ኑዛዜ[7] በሚኖርበት ጊዜ የተናዛዡን ሞት ማረጋገጥ ግድ ነው፤ 17ምክንያቱም ኑዛዜው የሚጸናው ሰውዬው ሲሞት ብቻ ነው፤ ነገር ግን ተናዛዡ በሕይወት እስካለ ድረስ ኑዛዜው ዋጋ አይኖረውም። 18ስለዚህ የመጀመሪያው ኪዳን እንኳ ያለ ደም የጸና አልነበረም። 19ሙሴ እያንዳንዱን የሕግ ትእዛዝ ለሕዝቡ ሁሉ ከተናገረ በኋላ የጥጆችን ደም ከውሃ፣ ከቀይ የበግ ጠጕርና ከሂሶጵ ጋር ወስዶ፣ በመጽሐፉና በሕዝቡ ላይ ረጨው፤ 20እንዲህም አለ፤ “እንድትጠብቁት እግዚአብሔር ያዘዛችሁ የኪዳኑ ደም ይህ ነው።” 21እንዲሁም ድንኳኒቱንና ማገልገያ ዕቃውን ሁሉ በደም ረጨው። 22በእርግጥ ከጥቂት ነገሮች በስተቀር ሁሉም ነገር በደም መንጻት እንዳለበት ሕጉ ያዛል፤ ደም ሳይፈስ ስርየት የለምና።

23እንግዲህ የሰማያዊው ነገሮች ምሳሌ የሆኑት በእነዚህ ነገሮች ሊነጹ ግድ ነበር፤ በሰማይ ያሉት ነገሮች ግን ከዚህ በማይበልጥ መሥዋዕት ይነጻሉ። 24ክርስቶስ የእውነተኛዪቱ ድንኳን ምሳሌ ወደ ሆነችውና በእው ጅ ወደ ተሠራችው መቅደስ አልገባም፤ ነገር ግን አሁን ስለ እኛ በእግዚአብሔር ፊት ለመታየት፣ ወደ እርሷ ወደ ሰማይ ገባ። 25ሊቀ ካህናት የራሱ ያለሆነውን ደም ይዞ በየዓመቱ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን እንደሚገባ፣ ክርስቶስ ራሱን ብዙ ጊዜ መሥዋዕት ለማድረግ ወደ ሰማይ አልገባም። 26እንዲህ ቢሆን ኖሮ፣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ክርስቶስ ብዙ ጊዜ መከራን መቀበል ባስፈለገው ነበር። አሁን ግን በዘመናት መጨረሻ ራሱን መሥ

9፥18 ዘ02፬፥6-8
9፥19 ቊ፡12፤ዘ02 24፥6-8፤ዕብ11፥1
9፥20 ዘ02፬፥8፤ ማቴ26፥28
9፥22 ዘ03፱፥21፤ ዘሌ8፥15፤17፥11
9፥23 ዕብ8፥5
9፥24 ቊ፡12፤ ሮሜ8፥34፤ ዕብ14፥14፤ዕብ8፥2
9፥25 ቊ7፡8፤ ዕብ10፥19
9፥26 ቊ፡12፡28፤ ዕብ14፥3፤7፥27፤ 1ዮሐ3፥5

9፥27 ዘፍ3፥19፤ 2ቆሮ5፥10
9፥28 ቊ፡12፡26፤ ማቴ16፥27፤ 1ቆሮ1፥7፤ ዕብ5፥9፤7፥27፤ 1ጴጥ2፥24
10፥1 ቊ4፡11፤ ቈላ2፥17፤ዕብ7፥19፤ 8፥5፤9፥11፡23
10፥2 ዕብ9፥9
10፥3 ዘሌ16፥34፤ ዕብ9፥7
10፥4 ቊ1፡11፤ ዕብ9፥12፡13
10፥5 ዕብ16፥2፤14፤ 1ጴጥ2፥24

ዋዕት በማድረግ ጎጢአትን ለማስወገድ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተገልጧል። 27ሰው አንድ ጊዜ ሊሞት ከዚያም በኋላ በፍርድ ፊት ሊቆም ተወስኖበታል። 28ክርስቶስ የብዙ ሰዎችን ጎጢአት ለመሸከም፣ እንዲሁ አንድ ጊዜ መሥዋዕት ሆኖአል፤ ሁለተኛ ጊዜም ይገለጣል፤ ይህም ለሚጠባበቁት ድኅንን ለማምጣት እንጂ ጎጢአትን ለመሸከም አይደለም።

ክርስቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያቀረበው መሥዋዕት

10 ሕጉ ወደ ፊት ለሚመጡት መልካም ነገሮች ጥላ ነው እንጂ፣ እውነተኛው አካል አይደለም፤ ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር ያለማቋረጥ የሚቀርበው ተደጋጋሚ መሥዋዕት፣ ለአምልኮ የሚቀርቡትን ሰዎች ፍጹም ሊያደርጋቸው ከቶ አይችልም። 2ፍጹም ሊያደርጋቸው ቢችል ኖሮ፣ መሥዋዕት ማቅረቡን ይተዉት አልነበረምን? ደግሞም ለአምልኮ የሚቀርቡት ሰዎች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስለሚነጹ፣ በኀሊናቸው ጎጢአተኝነት ባልተሰማቸውም ነበር። 3ነገር ግን እነዚህ መሥዋዕቶች በየዓመቱ ጎጢአትን የሚያስታውሱ ናቸው፤ 4ምክንያቱም የኮር ማዎችና የፍየሎች ደም ጎጢአትን ማስወገድ አይችልምና።

5ስለዚህ ክርስቶስ ወደ ዓለም በመጣ ጊዜ እንዲህ ብሎአል፤

“መሥዋዕትንና መባን አልፈለግህም፤
ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ፤
6በሚቃጠል መሥዋዕትና ለኀጢአት በሚቀ

7፡16 ይህንን ትርጕም የሚለጠው የግሪክ ቃል ኪዳን ተብሎም ሊተረጎም ይችላል፤ እንዲሁም ቊ፡17

የተብራራ ሐሳብ ነው። ከክርስቶስ ቤዛዊ ሞት የተነሣ፣ ይህ ርስት በእግዚአብሔር ለተጠሩት ሁሉ ተዘጋጅቶላቸዋል (ከሮሜ 8፥28 ጋር ያነጻጽሩ)። ቤዛ ሆኖ ማር 10፥45 እና ግብ ይመ። ደመን በማፍሰስ በመጀመሪያው ኪዳን ሥር ሳሉ ከፈጸሙት ኀጢአት ነጻ ለማውጣት ተገቢውን ዋጋ ከፈለ።

9፥16 ኑዛዜ፤ ይሄንኑ ቃል ለመግለጽ የገባው የግሪኩ ቃል ላይ “ኪዳን” (ቊ፡15) ተብሎ ተተርጉሞአል፤ በዚህ ቊጥርና በቊ. 17 ላይ ግን ቃሉ የገባው የመጨረሻ ኑዛዜና ቃል ኪዳንን ለማመልከት ነው (ቊ፡18 ደግሞ “ኪዳን” ወደሚለው እሳቤ ይመለሳል)። ኑዛዜ የተገባላቸው ሰዎች ተናዛዡ እስኪሞት ድረስ ይገኛል ማለት አይችሉም ቊ፡ 17። የክርስቶስ መሞት ፍጹም የተረጋገጠ በመሆኑ ኑዛዜ ያላቸው ሁሉ ተስፋ የተሰጠውን የዘላለም ርስት (ቊ፡ 15) ለማግኘት ይችላሉ።

9፥18 ያለ ደም ያለ ሞት ማለት ሲሆን ሙሴ ብሉይ ኪዳንን ለማጽናት ደም ይወስድ የነበረው ከጥጃዎች ነበር።

9፥19-20፤ እዚህ ላይ ስለ ተገለጸው ሥርዐት ዘጸ 24፥4-8 ይመ።

9፥21፤ ዘሌ 8፥10፡30 ይመ።

9፥23 *የሰማያዊው ነገሮች ምሳሌ፤* 8፥5 ይመ። ምድራዊው ቤተ መቅደስ የሚነጻው በእንስሳት መሥዋዕት እንደ ሆነ ሁሉ፣ ሰማያዊው ቤተ መቅደስ የሚነጻውም የተሻለ መሥዋዕት በሆነው በክርስቶስ ነው።

9፥24 *አሁን ስለ እኛ በእግዚአብሔር ፊት ለመታየት፤* 7፥25፤ 1ዮሐ 2፥1 ይመ። ታሪክ ሁሉ ፍጻሜውን ለማግኘት የሚገሠግሠው ወደዚሁ ነው።

9፥26 *በዘመናት መጨረሻ* መሲሑ ወደዚህ ምድር ሲመጣ የዘመኑ መጨረሻ ሆነ፤ ደግሞም ታሪክ ሁሉ ፍጻሜውን ለማግኘት የሚገሠግሠው ወደዚሁ ነው።

9፥27 *ሰው አንድ ጊዜ ሊሞት ከዚያም በኋላ በፍርድ ፊት ሊቆም ተወሥኖበታል፤* የተፈጥሮ ሕግ በመሆኑ ሰው አንድ ጊዜ ይሞታል (በጎጢአቱ ምክንያት፣ ሮሜ 5፥12)፤ ክርስቶስም የጎጢአት ፍጹም መሥዋዕት በመሆን አንድ ጊዜ ሞተ (ቊ. 28)። ከሞት በኋላ ሰው በፍርድ ፊት እንደሚቆም ሁሉ ክርስቶስም ከሞተ በኋላ የጎጢአትና ከፍርድ ሰዎችን ለማዳን እንደ ገና ይገለጣል። (አማራጭ ትርጕሙን ይመ)።

9፥28 *ድኑትን ለማምጣት፤* በመስቀል ላይ በመሞት የገዛውን (የተቤዠውን) ድኑት ከሙሉ ክብሩ ጋር ያመጣዋል (ሮሜ 8፥29-30፤ ፊል 3፥20-21፤ 1ዮሐ 3፥2-3 ይመ)። *ለሚጠባበቁት፤* በነርዮት ቀን አስራኤላውያን ሊቀ ካህኑ ከቅድስተ ቅዱሳን እስኪወጣ ድረስ እንደሚጠብቁት ሁሉ ነው። (2ጢሞ 4፥8፤ቲቶ 2፥13 ይመ)

10፥1 *ሕጉ፤* ከሙሴ ሥርዐት ጋር ጥብቅ ቊርኝት ያለውን የሌዋውያኑን ክህነት ጨምሮ ነው (ዖ7፥11 ማብ ይመ)። *ጥላ ነው እንጂ፤* በሕጉ ላይ የተዘረዘሩት መሥዋዕቶች በሙሉ የሚያመለክቱት ክርስቶስ በመጣ ጊዜ የሚያቀርበውን መሥዋዕት ነው። ስለዚህም በየዓመቱ መልሰው መላልሰው መሥዋዕት ማቅረብ ነበረባቸው፤ ይህም ፍጹም የሆነውና ጎጢአትን ማስወገድ የሚችለው መሥዋዕት ገና ያልቀረበ መሆኑን ይመለክታል።

10፥4 *የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ጎጢአትን ማስወገድ አይችልም።* የእንስሳት መሥዋዕት በእግዚአብሔር አምላክ ለተፈጠረው ሰው ብቁና ፍጹም መሆን አይችልም።

10፥5 *ክርስቶስ ወደ ዓለም በመጣ ጊዜ እንዲህ ብሎ አለ፤* ከዳዊት መዝሙር ላይ የተወሰዱት እነዚህ የዳዊት ቃላት (መዝ 40፥6-8)፣ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ሲመጣ ለአብ ያለውን ፍጹም ታዛዥነት ይገልጻሉ። በመሲሑ ሥርዐት የሚቀር ቡት መሥዋዕቶች፣ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ፍጹም ታዛዥ በሆነው ተተክተዋል (ቊ፡ 17)።

10፥6 *ደስ አልተሰኘህም፤* እነዚህ መሥዋዕቶች ሥጋ የለበሰው የእግዚአብሔር ልጅ በመጣ ጊዜ የሚያቀርበውን ፍጹምና የመጨረሻ መሥዋዕት የሚያመለክቱ ጊዜያዊና መንገድ

ርብ መሥዋዕት ደስ አልተሰኘህም።
7በዚያን ጊዜ እንዲህ አልሁ፥ ‘ስለ እኔ በመ
ጽሐፍ እንደ ተጻፈ፣
አምላክ ሆይ፥ እነሆኝ፥ ፈቃድህን ለማ
ድረግ መጥቻለሁ።’ ”
8ሕጉ ይህ እንዲደረግ ቢያዝም፣ እርሱ ግን
በመጀመሪያ፣ “መሥዋዕትንና መባን፣ የሚቃጠል
መሥዋዕትንና ስለ ኀጢአት የሚቀርበውን
መሥዋዕት አልፈለግህም፣ ደስም አልተሰ
ኘህበትም” ይላል። 9ቀጥሎም፣ “እነሆኝ፣
ፈቃድህን ለማድረግ መጥቻለሁ” አለ፤ ሁለ
ተኛውን ለመመሥረት የመጀመሪያውን
ሻረ። 10በዚህ ፈቃድ በኢየሱስ ክርስቶስ
ሥጋ አማካይነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ
በቀረበው መሥዋዕት ተቀድሰናል።

11ካህን ሁሉ በየዕለቱ ቆሞ አገልግሎ
ቱን ያከናውናል፣ ኀጢአትን ማስወገድ ከቶ
የማይችሉትን እነዚያኑ መሥዋዕቶች ዘወ
ትር ያቀርባል። 12ይህኛው ካህን ግን አን
ዱን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ፣ በእግዚ
አብሔር ቀኝ ተቀምጦአል፤ 13ከዚያን ጊዜ
ጀምሮ ጠላቶቹ የእግሩ መረገጫ እስኪሆኑ
ድረስ ይጠብቃል፤ 14ምክንያቱም በአንዱ
መሥዋዕት እነዚያን የሚቀደሱትን ለዘላለም
ፍጹማን አድርጎአቸዋል።

15መንፈስ ቅዱስም ስለዚህ ነገር ይመሰ
ክርልናል፤ በመጀመሪያ እንዲህ ይላል፤
16“ከዚያም በኋላ ከእነርሱ ጋር የምገባው

10፥7 ዕዝ6፥21
መዝ40፥6-8፤
ኤር36፥2፤ቁ26፥39
10፥8 ቁ5፥6፤
ማር12፥33
10፥9 ቁ7
10፥10 ቁ14፤1
ኤፌ5፥26፤ዕብ2፥14፤
7፥27፤ 1ጴጥ2፥24
10፥11 ቁ1፡4፤
ዕብ5፥1
10፥12 ማር16፥19፤
ዕብ5፥1
10፥13 ኢሳ10፥24፤
ዕብ1፥13
10፥14 ቁ1፡10፤
ኤፌ5፥26
10፥15 ዕብ3፥7
10፥16 ኤር31፥33፤
ዕብ8፥10
10፥17 ኤር31፥34፤
ዕብ8፥12
10፥19 ዘሌ16፥2፤
ኤፌ2፥18፤3፥12፤
ዕብ9፥8፤12፡25
10፥20 ዕብ6፥19፤
9፥3፡8
10፥21 ዕዝ2፥17፤ 3፥6
ሕዝ36፥25፤
ሐመ22፥16፤ኢሬ3፥12፤
ዕብ7፥19፤9፥14፤
12፥24፤1ጴጥ1፥2
10፥23 1ቆሮ1፥9፤
ዕብ3፥1፡6
10፥24 ቲቶ2፥14
10፥25 ሐመ2፥42፤
1ቆሮ3፥13፤ዕብ3፥13

ኪዳን ይህ ነው፤
ይላል ጌታ፤
ሕጌን በልባቸው አኖራለሁ፤
በአእምሮአቸውም እጽፈዋለሁ።”
17ደግሞም፣
“ኀጢአታቸውንና ዐመፃቸውን፣
ከእንግዲህ አላስብም” ይላል።
18እነዚህ ይቅር ከተባሉ በኋላ ከእንግዲህ
ስለ ኀጢአት የሚቀርብ መሥዋዕት አይኖርም።

እስከ መጨረሻው ጸንቶ ስለ መገኘት የቀረበ ጥሪ

19እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፥ በኢየሱስ
ደም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት ድፍ
ረት አግኝተናል፤ 20ይኸውም በመጋረጃው
ማለት በሥጋው በኩል በከፈተልን አዲስና
ሕያው መንገድ ነው። 21በእግዚአብሔር ቤት
ላይ የተሾመ ታላቅ ሊቀ ካህናት ስላለን
22ከክፉ ኅሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭ
ተን፣ ሰውነታችንንም በንጹሕ ውሃ ታጥበን፣
በእውነተኛ ልብና በሙሉ እምነት ወደ
እግዚአብሔር እንቅረብ። 23የተስፋን ቃል
የሰጠን ታማኝ ስለሆነ፣ እምነን የምንና
ገርለትን ተስፋ አጥብቀን እንያዝ። 24እርስ
በርሳችንም ለፍቅርና ለመልካም ሥራ
እንዴት እንደምንነቃቃቃ እናስብ። 25አንዳንዶች
ማድረጉን እንደተዉት መሰብሰባችንን
አንተው፤ ይልቁንም ቀኑ እየተቃረበ መም

ኣ7 ሰብዓ ሊቃናት ይመ።

የሚያዘጋጁ ብቻ ናቸው።

10፥7 *ፈቃድህን ለማድረግ* የልኞ ምኞት የአብን ፈቃድ መፈጸም ነው (ሉቃ 22፥42፤ ዮሐ 4፥34 ይመ)።

10፥9 *ሁለተኛውን ለመመሥረት የመጀመሪያውን ሻረ* በፍጹም መታዘዝ ያቀረበው መሥዋዕት ከዚህ በፊት ይቀርቡ የነበሩ መሥዋዕቶችን በሙሉ ይተካል።

10፥10 *ተቀድሰናል* ጸድቀናል ደግሞም ለእግዚአብሔር ተለይተን ተሰጥተናል፤ አሁን የሚቀረው በየዕለቱ እየተቀደስን መሄድ ብቻ ነው (ቁ. 14 ላይ “የሚቀደሱትን” የሚለውን ይመ፤ እንዲሁም የ1ቆሮ 1፥2 ማብ ይመ)።

10፥11-14፤ “ቆመው” በሚያገለግሉትና ሥራውን ሁሉ ጨርሶ “ባተቀመጠው” መካከል ያለውን ንጽጽር የሚያሳይ ክፍል ነው። በሌዋውያኑ ሥርዐት የሚያገለግሉት ካህናት ሥራ ቸውን ገና ስላልጨረሱ ሁልጊዜ ቆመው ያገለግሉ ነበር።

10፥11 *እነዚያኑ መሥዋዕቶች ዘወትር ያቀርባል፤* ዘወ ትር እነዚያን መሥዋዕቶች የሚያቀርበው የተደነገገውን ነገር ሊፈ ጽሙ ስላልቻሉ ነው። ኀጢአትንም ፈጽመው ማስወገድ ስለማይ ችሉ፣ በየጊዜው መቅረብ አለባቸው።

10፥12 *በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦአል፤* በሌዋውያኑ ሥርዐት መሠረት ከሚያገለግሉት ካህናት ጋር ሲነጻጸር ነው፤ እነርሱ ሥራቸውን አልጨረሱም (ቁ. 11፤የ1፥3፤13 ማብ ይመ)፤ ክርስቶስ ግን ሥራውን ጨርሷል። እርሱ አንድ ጊዜ ያቀረበው መሥዋዕት፣ ማንኛውም ሰውና በማንኛውም ዘመን የተፈጸመን ኀጢአት ማስተስረይ ይችላል፤ ይህም ከእንዲህ በኋላ ምንም ዐይ ነት መሥዋዕት እንዳይኖር አድርጎአል (ቁ. 14)።

10፥15-18፤ በእነዚህ ሦስቱም ላይ የተካተቱት ሁሉ ጥቅ ሶች የተወሰዱት ከኤር 31፥31-34 (ቀደም ሲል በ8፥8-12 ላይ ተጠ ቅሰዋል) ላይ ነው። አዲሱ ኪዳን ኀጢአት ሙሉ በሙሉ ይቅርታ እንደሚያገኘና (ቁ. 17) ከዚህም የተነሣ ለኀጢአት የሚቀርብ መሥዋዕት ከዚህ በኋላ እንደማያስፈልግ ያረጋግጣል (ቁ. 18)።

10፥19፤ ጸሓፊውን የመልእክቱን ተደራሲዎች የሚያበረ ታታቡት ሌላው ክፍል ነው (የ2፥1-4 ማብ ይመ)። *ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት ድፍረት*፣ የእንስሳቱ ደም ኀጢአታቸውን ፈጽሞ ሊያስተሰርይ ስለማይችል፣ በቀድሞው ኪዳን ሥር ለሚ ኖሩት ሕዝቦች ወደ እግዚአብሔር የሚወስደው መንገድ ተዘግቶ ነበር። አሁን ግን ፍጹም የሆነው ካህን፣ ኀጢአትን ለእንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚያስተሰርይ ፍጹም መሥዋዕት ስላቀረበ፣ አማ ኞች ወደ ጸጋው ዙፋን መቅረብ ይችላሉ።

10፥20 *በመጋረጃው፣* ማለት *በሥጋው።* ኢየሱስ በሞተ ጊዜ፣ ቅድስተ ቅዱሳኑን ከቅድስት የሚለውየው መጋረጃ፣ “ከላይ እስከ ታች ተቀዶ ሁለት ቦታ ተከፈለ” (ማር 15፥38)። *መጋረጃው ሥቃ ዩን* የሚገልጽ የክርስቶስ *ሥጋ* ምሳሌ ነው፤ ልክ እንደ መጋረ ጃው ሥጋውም ቡተቁረሰ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር የሚወስደ ውን መንገድ ከፈተልን።

10፥22-25፤ ኢየሱስ ካቀረበው መሥዋዕት የተነሣ ከእባቱ ጋር ለመታረቅ ቻልን፤ ጸሓፊውን ይህን መሠረት በማድረግ ተደ ራሲዎቹን እንዲህ ሲያሰ ያበረታታቸዋል፤ (1) ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ፤ (2) “አምነን የምንናገርለትን ተስፋ አጥብቀን እን ያዝ” (3) “እርስ በርሳችንም ... እንዴት እንደምንነቃቃቃ እናስብ (4) “መሰብሰባችንን አንተው” (5) “እርስ በርሳችን እንበረታታ”።

10፥22፤ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ አራት ነገሮች መሟ ላት እንዳለባቸው ተገልጸአል። (1) *በእውነተኛ ልብ* በውስጥ ሰው ነት ፍጹም ታማኝ ሆኖ መገኘት፤ (2) *በሙሉ እምነት* ክርስቶ ስን አምኖ ለመከተል መወሰን፤ (3) *ከክፉ ኅሊና ለመንጻት ልባ ችንን ተረጭተን*፣ ከበደለኝነት ስሜት ፍጹም ነጻ መሆን፤ ይህም ነጻነት ክርስቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ባቀረበው መሥዋዕት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፤ (4) *ሰውነታችንንም በንጹሕ ውሃ ታጥበን፤* እንደ ጥምቀት ያለውን ውጫዊ ሥርዐት ሳይሆን፣ ውስጣዊ መንጻትን የሚያመለክት ነው፤ ይህም በአርጌው ኪዳን ሥር የነበሩ ካህናት ለመንጻት ያደርጉት የነበረውን ሥርዐት ያመለክታል። (ዘፀ 30፥19-21፤ ዘሌ 8፥6 ይመ፤ እንዲሁም በሕዝ 36፥25 ላይ በአዲሱ ኪዳን የተገኘውን መንጻት ምሳሌያዊ በሆነ መንገድ ለመግለጽ የገባውን አብሳል ይመ)።

10፥23 *የተሰፋን ቃል የሰጠን ታማኝ ስለ ሆነ* ከ2ጢሞ 2፥13 *ጋር ያነጻጽሩ።* *አምነን የምንናገርለትን* 6፥18-20 ይመ። *አጥብቀን* ያለ አንዳች ጥርጥር ወይም ማመንታት ማለት ነው። ከመልእክቱ ተደራሲዎች ውስጥ አንዳንዶቹ ትግሉን ትተው ወደ ቀድሞው የይሁዲ እምነት ለመመለስ ከጅለው ነበር።

10፥25 *መሰብሰባችንን አንተውን* “አንተው” የሚለውን ለመግለጽ የገባው የግሪኩ ቃል ጨርሶ ወይም እርግፍ አድርጎ መተውን ያመለክታል (ማቴ 27፥46፤ 2ቆሮ 4፥9፤ 2ጢሞ 4፥10፤ 16 ይመ)። *ቀኑ* ጌታ ዳግም ተመልሶ የሚመጣበትን ቀን ነው

ጣቱን ስታዩ እርስ ብርሳችን እንበረታታ።

26የእውነትን ዕውቀት ከተቀበልን በኋላ ሆን ብለን በኀጢአት ጸንተን ብንመላለስ፣ ከእንግዲህ ለኀጢአት የሚሆን ሌላ መሥዋዕት አይኖርም፣ 27የሚቀረው ግን የሚያስፈራ ፍርድና የእግዚአብሔርን ጠላቶች የሚበላ ብርቱ እሳት መጠበቅ ብቻ ነው። 28የሙሴን ሕግ የናቀ ማንኛውም ሰው ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ከመሰከሩበት ያለ ምሕረት ይገደል ነበር። 29ታዲያ የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ፣ የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ተራ ነገር የቈጠረ፣ የጸጋንም መንፈስ ያከፋፋ እንደምን ያለ የባሰ ቅጣት ይገባው ይመስላችኋል? 30“ብቀል የእኔ ነው፤ እኔ ብድራትን አመልሳለሁ” ያለውን እና ውቀዋለንና፣ ደግሞም፣ “ጌታ በሕዝቡ ላይ ይፈርዳል” ይላል። 31በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ እጅግ የሚያስፈራ ነው።

32ብርሃን ከበራላችሁ በኋላ፣ በመከራ ውስጥ በብርቱ ተጋድሎ ጸንታችሁ የቆማችሁበትን የቀድሞውን ዘመን ዐስቡ። 33አንዳንድ ጊዜ በአደባባይ ለስድብና ለስደት ተጋልጣችሁ ነበር፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ እንደዚህ ያለ መከራ ከደረሰባቸው ሰዎች ጋር አብራችሁ መከራን ተቀብላችኋል። 34እናንተ ራሳችሁ የተሻለና ለዘወትር የሚኖር ሀብት ያላችሁ መሆናችሁን ስለምታውቁ ለታሰሩት ራራችሁ፤ ንብረታችሁም ሲዘረፍ በደስታ ተቀበላችሁ።

35ስለዚህ ታላቅ ዋጋ ያለውን መታመን አትጣሉ። 36የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጽማችሁ የተስፋ ቃሉን እንድትቀበሉ፣ ጸንታችሁ መቆም ያስፈልጋችኋል፤ 37ምክንያቱም ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣

“የሚመጣው እርሱ ይመጣል፤ አይዘገይም።

10፥26 ዘኍ21፥14፤ ዘኍ15፥30፤ 1ጢሞ2፥4፤ዕብ5፥2፤ 6፥4-8፤ሉቃ2፥20

10፥27 ኢሳ26፥11፤ 2ተሰ1፥7፤ ዕብ9፥27፤12፥29

10፥28 ዘዳ17፥6፤7፤ ማቴ18፥16፤ዕብ2፥2

10፥29 ማቴ4፥3፤ 26፥28፤1ቆሮ6፥11፤ ኤፌ4፥30፤ዕብ12፥3፤ 6፥4፡6፤12፥25፤ ራእ1፥5

10፥30 ዘዳ32፥35፡ 36፤መዝ135፥14፤ ሮሜ12፥19

10፥31 ኢሳ19፥16፤ ማቴ16፥16፤ 2ቆሮ5፥11

10፥32 ፊል1፥29፡ 30፤ዕብ6፥4

10፥33 1ቆሮ4፥9፤ ፊል4፥14፤1ተሰ2፥14

10፥34 ዕብ11፥16፤ 13፥3፤1ጴጥ1፥4፡5

10፥35 ኤፌ3፥12

10፥36 ሮሜ5፥3፤ ዕብ6፥15፡9፤15፤ 12፥1፤ያዕ1፥3፡4፡12፤ 5፥11፤2ጴጥ1፥6

10፥37 ማቴ11፥3፤ ራእ22፥20

10፥38 ሮሜ1፥17፤ ገላ3፥11፤ዕን2፥3፡ 4፤11፥1

2ቆሮ4፥18፤ዕብ3፥6

11፥2 ቁጥ4፡39

11፥3 ዘፍ1ዋሕ1፥3፤ ዕብ11፥2፤2ጴጥ3፥5

11፥4 ቁጥ2፡39፤ ዘፍ4፥4፤ዕብ12፥24፤ 1ዮሐ3፥12

11፥5 ዘፍ5፥21-24

11፥6 ዕብ7፥19

38ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል፤
ወደ ኋላ ቢያፈገፍግ፣
ነፍሴ በእርሱ ደስ አትሰኝም።”

39እኛ ግን አምነው ከሚድኑት ወገን እንጂ፣ ወደ ኋላ አፈግፍገው ከሚጠፉት አይደለንም።

የእምነት ቋሚ ምስክሮች

11 እምነት ተስፋ ያደረግነው ነገር እንደ ሚፈጸም እርግጠኛ የምንሆንበት፣ የማናየውም ነገር እውን መሆኑን የምንረዳበት ነው። 2አባቶችም የተመሰከረላቸው በዚሁ ነው።

3ዓለማት በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተፈጠሩ በእምነት እንረዳለን፤ ስለዚህ የሚታየው ነገር የተፈጠረው ከሚታየው እንዳልሆነ እንገነዘባለን።

4አቤል ከቃየል ይልቅ የበለጠ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር በእምነት አቀረበ። እግዚአብሔር ስለ ስጦታው በተናገረለት ጊዜ፣ እርሱ በእምነት ጻድቅ እንደ ሆነ ተመሰከረለት፤ ቢሞትም እንኳ እስከ አሁን በእምነቱ ይናገራል።

5ሄኖክ ሞትን እንዳያይ ከዚህ ዓለም በእምነት ተወሰደ፤ እግዚአብሔርም ስለ ወሰደው አልተገኘም፤ ከመወሰዱም በፊት እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመስክሮለታልና። 6ደግሞም ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሁሉ እግዚአብሔር መኖሩንና ከልብ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጥ ማመን አለበት።

7ኖኅ ገና ስለማይታየው ነገር እግዚአብሔር ባስጠነቀቀው ጊዜ፣ እግዚአብሔርን ፈርቶ ቤተ ሰውቹን ለማዳን መርከብን በእምነት ሠራ፤ በእምነቱ ዓለምን ኰነነ፤ በእምነትም የሚገ

11፥7 ቁጥ1፤ ዘፍ6፥9፡ 13-22፤ሕዝ14፥14፡ 20፤ሮሜ9፥30፤ዕብ3፥20

ን38 ወይም የእኔ ጽድቅ ግን

(1ተሰ5፥2፤4፤2ተሰ1፥10፤2፥2፤2ጴጥ 3፥10 ይመ)።

10፥26-31፤ እነዚህ ቍጥሮች ከእግዚአብሔር ጉባኤ ተለይተው የሚወጡ ሰዎችን (በቍ. 25 ላይ “አንዳንዶች የተባሉትን) ለማስጠንቀቅ የተጻፉ ናቸው። በዚህ ክፍል ከተነገረው መንፈሳዊ ውድቀት ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለውን የዕብ4-8 ማብ ይመ፤

10፥26 *ሆን ብለን በኀጢአት ጸንተን ብንመላለስ* የክህደት ኀጢአትን ብንፈጽም ማለት ነው (ቍ. 29 ይመ፤ የ5፥2 ማብ ይመ)። ይህ ጥቅስ የተመሠረተው በዘኍ 15፥27-31 ላይ ነው። *ለኀጢአት የሚሆን ሌላ መሥዋዕት አይኖርም፤* ክርስቶስን ለኀጢአት ያቀረበውን መሥዋዕት አለመቀበል ማለት፣ ብቸኛ የሆነውን የኀጢአት መሥዋዕት አለመቀበል ማለት ነው፤ ከዚህ ሌላ መሥዋዕት የለምና።

10፥27 *የሚያስፈራ ፍርድና...ያሚባላ ብርቱ እሳት*፤ 2ተሰ 1፥6-9 ይመ።

10፥28፤ ዘዳ 17፥2-7 ይመ።

10፥29 *የኪዳኑን ደም*፤ 9፥20፤13፥20፤ ዘፀ 24፥8፤ ማቴ 26፥28፤ ማር 14፥24 ይመ።

10፥31፤ 12፥29 ይመ።

10፥32 *የቀድሞውን ዘመን* ምናልባት መጀመሪያ ወንጌልን በተቀበሉ ጊዜ የነበራቸውን ብርቱ አቋምና በዚያ ሁሉ መከራ ውስጥ ሲያልፉ ያሳዩትን ጽናት እንዲሁም እርስ በርስ የነበራቸውን ፍቅር ለመግለጽ ነው።

10፥34 *የተሻለና ለዘወትር የሚኖር ሀብት*፤ በክርስቶስ ያገኙትን ድኅንና ወደፊት የሚጠብቃቸውን ሽልማት ነው (11፥10፤ 13-16፤26፤35፤13፥14፤ ማቴ 5፥11-12፤6፥19-21፤ ሮሜ 8፥18)።

10፥38 *ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል*፤ የዕንባቆም 2፥4 ማብ ይመ።

10፥39 *ወደ ኋላ አፈግፍገው ከሚጠፉት*፤ “አምነው ከሚድኑት ወገን” ለሚለው ተቃራኒ ነው። የመልእክቱ ጸሓፊ ከተደራሲዎቹ መካከል አብዛኞቹ አምነው ከሚድኑት ወገን እንደሆኑ እርግጠኛ ነው (የ6፥9 ማብ ይመ)።

11፥1-12፥29፤ ቀደም ሲል በተብራሩት የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ላይ የተመሠረተ ምክር ነው።

11፥2 *አባቶቻችን* በቅድመ ክርስትና ዘመን የነበሩ የእምነት ዐርበኞች ናቸው፤ ከእነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ በዚህ ምዕራፍ ተጠቅሰዋል።

11፥4፤ ዘፍ 4፥2-5 ይመ። *ጻድቅ እንደ ሆነ ተመሰከረለት*፤ ሁለቱ ወንድማማቾች፣ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረቡ፤ ቃየን ከዕርሻው ፍሬ ሲያቀርብ፣ አቤል ደግሞ ከበጎቹ መካከል በኵር የሆነውን አቀረበ። የአቤል መሥዋዕት ተቀባይነት ሊያገኝ የቻለበት ዋናው ምክንያት፣ መሥዋዕቱን “በእምነት” ስላቀረበ ነው። ይህም የቃየል መሥዋዕት ተቀባይነት ያጣው በእምነት ሳይሆን ለታይታ ብቻ የቀረበ መሆኑን ያስገነዝባል (የዘፍ 4፥3-4 ማብ ይመ)።

11፥5 *ሄኖክ* ዘፍ 5፥18-24 ይመ። *ተወሰደ*፤ እግዚአብሔር ወደ ሚኖርበት ነው (የዘፍ 5፥24 ማብ ይመ፤ ከመዝ 49፥15፤ 73፥24 ጋር ያነጽጽሩ)።

11፥6 *ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም*፤ ሄኖክ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘቱ እምነት ያለው ሰው መሆኑን ያረጋግጣል። *ማመን አለበት*፤ እምነት የሚያርፍበት ወይም የሚቆምበት ነገር ያስፈልገዋል፤ የእውነተኛ እምነት ማረፊያ እግዚአብሔር ነው። *ለሚሹትም*፤ ኤር 29፥13 ይመ።

11፥7 *ኖኅ* ዘፍ 5፥28-9፥29 ይመ። *በእምነቱ*፤ የጥፋት ውሃ በመጣ ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ቃል እውነተኛ መሆኑ

ኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ።

⁸አብርሃም ርስት አድርጎ ወደሚቀበለው ስፍራ እንዲሄድ በተጠራ ጊዜ በእምነት ታዘዘ፤ ወዴት እንደሚሄድ ባያውቅም፤ እሺ ብሎ ሄደ። ⁹በባዕድ አገር እንዳለ መጻተኛ በተስፋውም ቃል አብረውት እንደሚወርሱት እንደ ይስሐቅና እንደ ያዕቆብ በድንኳን ኖረ፤

¹⁰ምክንያቱም መሠረት ያላትን፤ እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠባበቅ ነበርና። ¹¹አብርሃም[ም] ምንም እንኳ ዕድሜው ቢገፋም፤ ሣራም[ም] ራሷ መካን ብት ሆንም፤ ተስፋን የሰጠውን ታማኝ አድርጎ ስለ ቈጠረ[ች] በእምነት የልጅ አባት ለመሆን በቃ። ¹²ስለዚህ እንደ ሞተ ሰው ከሚቈጠር ከዚህ ከአንድ ሰው፤ እንደ ሰማይ ከዋክብት የበዛና እንደ ባሕር ዳር አሸዋ ተቈጥሮ የማያልቅ ዘር ተገኘ።

¹³እነዚህ ሁሉ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል ሳያገኙ እምነታቸውን እንደ ጠበቁ ሞቱ፤ ሆኖም ከሩቅ አይተው ሰላም አሉት፤ በዚህ ምድር ሲኖሩ መጻተኞችና እንግዶች መሆናቸውን ተገንዝበው ነበርና። ¹⁴እንደዚህ የሚሉት ሰዎች የራሳቸው የሆነውን አገር እንደሚጠባበቁ ያሳያሉ። ¹⁵ትተውት የወጡትን አገር ቢያስቡ ኖሮ፤ ወደዚያ የመመለስ ዕድል ነበራቸው። ¹⁶አሁን ግን ከዚህ የሚበልጠውን ሰማያዊ አገር ይናፍቃሉ፤ ስለ ዚህ እግዚአብሔር ለምሳሳቸው ተብሎ ሊጠራ አላፈረም፤ ከተማን አዘጋጅቶላቸዋልና።

¹⁷አብርሃም እግዚአብሔር በፈተነው ጊዜ፤

11፥8 ዘፍ12፥1-4፤ 7፤ሐሥ7፥2-4
11፥9 ዘፍ12፥8፤18፥1፤ 9፤ሐሥ7፥5፤ዕብ6፥17
11፥10 ቈላ1፥16፤ ዕብ12፥22፤13፥14፤ ራእ21፥2፤14
11፥11 ዘፍ17፥17-19፤ 18፥11-14፤ 21፥2፤1ቆሮ1፥9
11፥12 ዘፍ22፥17፤ ሮሜ4፥19
11፥13 ቊ39፤ ዘፍ23፥4፤ዘሌ25፥23፤ ማቴ13፥17፤ሐኤ3፥20፤ 1ጴጥ1፥17፤2፥11
11፥15 ዘፍ24፥6-8
11፥16 ቊ10፤ ዘፍ26፥24፤28፥13፤ ዘፀ3፥6፤15፤ማር8፥38፤ 2ጢሞ4፤18፤ዕብ13፥14
11፥17 ዘፍ22፥1-10፤ ያዕ2፥21

11፥18 ዘፍ21፥12፤ ሮሜ9፥7
11፥19 ሮሜ4፥21፤ ዮሐ5፥21
11፥20 ዘፍ27፥27-29፤ 39፥40
11፥21 ዘፍ48፥1፤ 8-22
11፥22 ዘፍ50፥24፤ 25፤ዘፀ13፥19፤ ኢያ24፥32
11፥23 ዘፀ1፥16፤ 22፤2
11፥24 ዘፀ2፥10፤11
11፥25 ቊ37

ይስሐቅን መሥዋዕት አድርጎ በእምነት አቀረበ፤ የተስፋን ቃል የተቀበለው እርሱ፤ አንድ ልጁን ሊሠዋ ዝግጁ ነበር፤ ¹⁸ይህም እግዚአብሔር፤ "ዘርህ በይስሐቅ ይጠራል" ያለለት ነበር። ¹⁹አብርሃም እግዚአብሔር ሙታንን ሊያስነሣ እንደሚችል ተገንዝቦ ነበር፤ ይስሐቅንም ከሞት የመነሣት አምሳያ ሆኖ አገኘው።

²⁰ይስሐቅ ወደፊት የሚሆነውን ዐስቦ ያዕቆብንና ዔሳውን በእምነት ባረካቸው።

²¹ያዕቆብ በሚሞትበት ጊዜ እያንዳንዳቸውን የዮሴፍን ልጆች በእምነት ባረካቸው፤ በበትሩም ጫፍ ዘንበል ብሎ ሰገደ።

²²ዮሴፍ ሊሞት በተቃረበ ጊዜ፤ ስለ እስራኤል ሕዝብ ከግብፅ መውጣት በእምነት ተናግሮ፤ ስለ ዐጽሙም ትእዛዝ ሰጠ።

²³ሙሴ ከተወለደ በኋላ፤ ወላጆቹ መልከ መልካም ሕፃን መሆኑን ስላዩ በእምነት ሦስት ወር ሸሽጉት፤ የንጉሡንም ዐዋጅ አልፈሩም።

²⁴ሙሴ ካደገ በኋላ፤ የፈርዖን የልጅ ልጅ መባልን በእምነት እምቢ አለ። ²⁵ለጥቂት ጊዜ ቦነኪአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ፤ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራን መቀበል መረጠ። ²⁶ከግብፅ ሀብት ይልቅ ስለ ክርስቶስ መከራን መቀበል እጅግ የሚበልጥ ሀብት መሆኑን ተገንዝቦ፤ ወደ ፊት የሚቀበለውን ብድራት ከሩቅ ተመልክቶ

11፥26 ሉቃ14፥33፤ዕብ10፥35፤13፥13

ዝ11 ወይም ሣራ ... አብርሃምም ... ስለቈጠረች

ተረጋገጠ፤ የኖኅ እምነት ትክክለኛ እንደ ሆነ ተመሰከረ፤ የዓለምም ከሀደት ተኮነነ። *በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ፤* ኖኅ ምንም እንኳ የተነገረው ነገር ይኸውም የጥፋት ውሃ ባይታየው (ቊ 7) በእግዚአብሔርና በቃሉ ላይ ያለውን ሙሉ እምነት ገለጸ። ስለዚህ ኖኅ በእምነት ከሚኖሩ የእግዚአብሔር ጻድቃን መካከል ለመቈጠር በቃ (10፥38)። በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያለው እምነት በደረቅና የሠራውን መርከብ ማንሳፈፍ የሚችል በቂ ውሃ ይኖራል ተብሎ በማይታሰብበት ስፍራ መርከብን እንዲሠራ አነሣሣው።

11፥8 *አብርሃም፤* በአዲስ ኪዳን ውስጥ በ"እምነት" ለሚኖሩና "ለሚያምኑ ሁሉ አባት" ተብሎ ተጠቅሶለል (ሮሜ 4፥11-12፤16፤ገላ3፥7፤29)። *በተጠራ ጊዜ፤* ዘፍ 12፥1-3 ይመ። እምነቱ የታየው በመታዘዙ ነው (የዘፍ 12፥4 ማብ ይመ)። *ርስት አድርጎ ወደሚቀበለው ስፍራ፤* ወደ ከነዓን ነው። *ወዴት እንደሚሄድ ባያውቅም፤* አካሄዱ ባወጣ ያወጣው በሚል ጭፍንነት ሳይሆን የእግዚአብሔርን ታማኝነት በመታመን ነበር።

11፥10 *መሠረት ያላትን ... ከተማ፤* የቀድሞ አባቶች ይኖሩባት ከነበረው ጊዜያዊ ድንኳን ጋር በማነጻጸር ነው (ቊ 9)። ይህች ከተማ "ሰማያዊት ኢየሩሳሌም" (12፥22)፣ "ወደፊት የምትመጣዋ ከተማ" (13፥14) እንዲሁም "አዲሲቱ ኢየሩሳሌም" (ራእ 21፥2-4፤9-27) ናት። *የፈጠራትን፤* ከመዝ 147፥2 ያነጻጽሩ። የኢሳ 62፥5 አማራጭ ትርጕሙን ይመ።

11፥11 *ሣራም ... መካን ብትሆንም፤* ምናልባት ልጅ መውለድ የማትችልበት ዕድሜ ላይ መድረሷን *ያመለከታል* (ዘፍ 18፥11-12፤ የዘፍ 11፥30 ማብ ይመ)።

11፥12 *እንደ ሞተ ሰው፤* ምክንያቱም ዕድሜው መቶ ዓመት ሆኖት ነበር (ዘፍ 21፥5፤ ሮሜ 4፥19 ይመ)። *እንደ ሰማይ ከዋክብት... እንደ ባሕር ዳር አሸዋ፤* ዘፍ 13፥16 እና ማብራሪያውን ይመ፤ እንዲሁም 15፥5፤22፥17፤26፥4፤1ነገ 4፥20 ይመ።

11፥13 *ከሩቅ አይተው ሰላም አሉት፤* በድንግዝግዝ ቢሆንም፤ ይህን ሰማያዊ እውነት በእምነት ተመለከቱ፤ ደግሞም ተስፋ ያደረጉትን ነገር በመጨረሻ እንደሚያገኙ እርግጠኛ ነበሩ (ቊ 1 ይመ)። *በዚህ ምድር ሲኖሩ መጻተኞችና እንግዶች፤* እውነተኛ ቤታቸው በሰማይ ነው።

11፥14 *የራሳቸው የሆነውን፤* የተሻለና ሰማያዊ አገርን *ያመለክታል* (ቊ 16)።

11፥16 *ከተማ አዘጋጅቶላቸዋልና፤* ከተማና (ቊ 10) አገር የሚሉት ቃላት በዚህ መልእክት መደምደሚያ ምዕራፎች ውስጥ በተለዋዋጭነት ገብተዋል (ቊ 9-10፤14-16፤ 13፥14)። በዮሐንስ ራእይ ውስጥ ይህች ከተማ፣ አማኞች የሚኖሩባት አዲ ሲቱ ኢየሩሳሌም ተብላለች (ራእ 21፥2 ይመ)።

11፥17፤ ዘፍ 22 ይመ። *አንድ ልጁን፤* ዘፍ 22፥2፤12፤16፤ ዮሐ 3፥16፤ ሮሜ 8፥32 ይመ።

11፥19 *እግዚአብሔር ሙታንን ሊያስነሣ እንደሚችል፤* የአብርሃም እምነት ጠንካራ ከመሆኑ የተነሣ፣ እግዚአብሔር ከወደደ ይስሐቅን ከሞት እንኳ ሊያስነሣው እንደሚችል አምኖአል፤ ይህም ምትክ የሚሆነው በግ በቀረበ ጊዜ ምሳሌያዊ በሆነ መንገድ ተፈጽሞአል። (ዘፍ 22፥13)።

11፥20፤ ዘፍ 27፥27-40 ይመ።

11፥21፤ ዘፍ 47፥29-31፤ 48፥8-20 ይመ።

11፥22፤ ዘፍ 50፥24-25 ይመ። *ያዕቆብና* (ቊ 21) ዮሴፍ በሕይወት ዘመናቸውም ሆነ በሞታቸው፣ በእምነት ጠንካራ ለነበሩ ሰዎች ተጨማሪ ምሳሌ ሆነው ቀርበዋል (ቊ 13)።

11፥23-29፤ ሐሥ 7፥20-44 ይመ።

11፥23 *ወላጆቹ፤* ዘፀ 6፥20፤ ዘኍ 26፥58-59 ይመ። *መልከ መልካም ሕፃን መሆኑን፤* የዘፀ 2፥2 ማብ ይመ። *የንጉሡን ዐዋጅ* ወንድ ሆነው የሚወለዱ እስራኤላውያንን በሙሉ ለመግደል የወጣ ዐዋጅ ነው (ዘፀ 1፥16፤22)።

11፥25 *በኀጢአት ከሚገኝ ደስታ፤* በግብፅ ቤተ መንግሥት ውስጥ ከሚገኝ ድሎትና ክብር ነው።

11፥26 *ስለ ክርስቶስ፤* ሙሴ ስለ መሲሑ ተስፋ የነበረው ዕውቀት ውሱን ቢሆንም፣ ይህ ተስፋ እውን ከሚሆንበት ሕዝብ ጋር መሆንን መረጠ። *ከግብፅ ሀብት፤* እጅግ ብዙ ሀብት ፈሰበት የተሠራው የንጉሥ ቱታኽሙን መቃብር፣ በብዙ ሺህ ኪሎ ግራም የሚቈጠር ንጹሕ ውርቅ ፈጅቷል።

11፥27 *ግዙፉን ሉቊ በአምላኩ መጥ* ምናልባት የአርባ ዓመት

አልና። [27]የንጉሡን ቊጣ ሳይፈራ ግብፅን ለቆ በእምነት ወጣ፤ የማይታየውንም እንዳየው አድርጎ በመቍጠር በሐሳቡ ጸና። [28]በዙሮች የሆኑትን የሚገድለው ቀሣፊ የእስራኤልን በኵር ልጆች እንዳይገድል ፋሲካን በእምነት አደረገ፤ ደምንም ረጨ።

[29]ሕዝቡ በደረቅ መሬት እንደሚኬድ ቀይ ባሕርን በእምነት ተሻገሩ፤ ግብፃውያን ግን እንደዚሁ ለማድረግ ሲሞክሩ ሰጠሙ።

[30]ሕዝቡ የኢያሪኮን ግንብ ሰባት ቀን ከዙሩት በኋላ፣ በእምነት ወደቀ።

[31]ዝሙት አዳሪዋ ረዓብ፣ ሰላዮቹን በሰላም ስለ ተቀበለቻቸው ከማይታዘዙትም ጋር ያልጠፋችው በእምነት ነው።

[32]እንግዲህ ከዚህ በላይ ምን ልበል? ስለ ጌዴዎን፣ ስለ ባርቅ፣ ስለ ሳምሶን፣ ስለ ዮፍታሔ፣ ስለ ዳዊት፣ ስለ ሳሙኤል፣ እንዲሁም ስለ ነቢያት እንዳልተርክ ጊዜ የለኝም። [33]እነዚህ በእምነት መንግሥታትን ድል ነሡ፤ በቅን ፈረዱ፤ የተሰጠውን የተስፋ ቃል ተቀበሉ፤ የአንበሶችን አፍ ዘጉ፤ [34]የእሳትን ኀይል አጠፉ፤ ከሰይፍ ስለት አመለጡ፤ ከድካማቸው በረቱ፤ በጦርነት ኀያል ሆኑ፤ ባዕዳን ወታደሮችን አባረሩ። [35]ሴቶች ሙታናቸው ተነሡላቸው። ሌሎቹ

11፥27 ዘ፴12፥50፡51
11፥28 ዘ፴12፥21-23፤ 1ቆሮ10፥10
11፥29 ዘ፴14፥21-31
11፥30 ኢያ6፥12-20
11፥31 ኢያ2፥1፱-14፤ 6፥22-25፤ ዕዳ2፥25
11፥32 መሳ4-5፤ 6-8፤11-12፤13-16፤ 1ሳሙ1፥20፤1ሳ16፥1፡13
11፥33 ዳን6፥22፤ 2ሳሙ8፥1-3
11፥34 ዘ፴18፥4፤ መሳ15፥8፤2ዜና20፥7፤ ዳን3፥19-27
11፥35 1ነገ17፥22፡ 23፤2ነገ4፥36፡37

11፥36 ዘፍ39፥20፤ ኤር20፥2፤37፥15
11፥37 1ነገ19፥10፤ 2ነገ1፥8፤2ዜና24፥21፤ ኤር26፥23
11፥38 1ነገ18፥4፤ 19፥9
11፥39 ቊ2፥4፡ 13፤ዕብ10፥36
11፥40 ዕብ2፥10፤ ራእ ፥11
12፥1 1ቆሮ9፥24፤ ዕብ10፥36

ደግሞ የተሻለውን ትንሣኤ ለማግኘት ሲሉ፣ መትረፍን ንቀው ለሞት ለሚዳርግ ሥቃይ ራሳቸውን ሰጡ፤ ከዚህም ነጻ ለመውጣት አልፈለጉም። [36]አንዳንዶቹ መዘባበቻ ሆኑ፤ ተገረፉ። ሌሎቹ ደግሞ ታስረው ወደ ወህኒ ተጣሉ፤ [37]በድንጋይ ተወገሩ፤ በመጋዝ ለሁለት ተሰነጠቁ፤[ዐ] በሰይፍ ተወግተው ሞቱ፤ እየተጐሳቈሉ፣ እየተሰደዱና እየተንገላቱ የበግና የፍየል ቈዳ ለብሰው ዞሩ፤ [38]ዓለም ለእነርሱ አልተገባቻቸውምና። በየበረሓውና በየተራራው፣ በየዋሻውና በየጒድጓዱ ተንከራተቱ ።

[39]እነዚህ ሁሉ ስለ እምነታቸው የተመሰከረላቸው ቢሆኑም ከእነርሱ ማንም የተስፋውን ቃል የተቀበለ የለም። [40]እግዚአብሔር ለኛ የሚበልጥ ነገር ስላዘጋጀ፣ ያለ እኛ ፍጹማን ሊሆኑ አልቻሉም።

እግዚአብሔር ልጆቹን ይቀጣል

12 እንግዲህ እነዚህን የመሰሰሉ ብዙ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፣ ሸክም የሚሆንብንን ሁሉ፣ በቀ ላሉም ተብትቦ የሚይዘንን ኀጢአት አስወግ

[ዐ]31 ወይም ከማያሚት
[ዐ]37 አንዳንድ የጥንት ጽሕፈ በድንጋይ ተወገሩ፣ ለፈተና አልፈው ተሰጡ፤

ሰው በሆነው ጊዜ በሲና ባሕር ስርጥ ወደምትገኘው የምድያም ምድር የከበለለበትን ሁኔታ ያመለክታል (ዘፀ 2፥11-15፤ ሐሥ 7፥23-29)። *ዮንጉሡን ቊጣ ሳይፈራ* በዘፀአት መጽሐፍ ውስጥ ሙሴ ፈርዖ እንደ ነበር ተገልጾአል (ዘፀ 2፥14)፤ ነገር ግን ማንን እንደ ፈራ በግልጽ አልተነገረም። ደግሞም ፈርዖን ሊገድለው ባሰበ ጊዜ ከፈርዖን እንደ ሸሸ ተገልጾአል (ዘጸ2፥15)፤ ነገር ግን የሸሸው ከፍርሀት የተነሣ እንደ ሆነ ግልጽ አይደለም። የዕብራውያን መልእክት ጸሓፊ ይህን ሁኔታ መሠረት በማድረግ፣ ሙሴ ከፈርዖን ሲሸሽ በእግዚአብሔር ታምኖ እንደ ነበር፣ እስራኤልም ነጻ የምትወጣበት ቀን እንደ መጣና እርሱም የበኩሉን ድርሻ ለመፈጸም እንደ ተጠራ ይነግረናል። *በሐሳቡ ጸና* ለአርባ ዓመት በምድያም ቈየ (ሐሥ 7፥30)።

11፥28፤ ዘፀ 12 ይመ።

11፥29፤ ዘፀ 14-15 ይመ። ሙሴ ሦስተኛውንና የመጨረሻውን አርባ ዓመት ያሳለፈው እስራኤላውያንን በምድረ በዳ ሲመራ ነው። ዕድሜው መቶ ሃያ ዓመት ሲሆነው በሞዓብ ሞተ (ዘዳ 34፥1-7)።

11፥30፤ ሙሴ ሲመራው የነበረውን ሕዝብ ኢያሱ ተረከበ፤ እርሱም ሕዝቡን ወደ ተስፋቱቱ ምድር አደረሰ። *ኢያ ሪኮ* የተሰፋዪቱን ምድር ለመውረስ በወጡት ጊዜ የገጠ ማቸውን ትልቁን ጠላት ያለ አንዳች ጦርነት በእምነት ብቻ ድል ነሡ (ኢያ 6)።

11፥31 *ዝሙት አዳሪዋ ረዓብ*፤ አዲስ ወዳገኘችው እምነት ከመቃጥቷ በፊት የነበራትን የቀድሞ ሕይወቷን የሚያመለክት አገላለጽ ነው (ኢሱ 2፥8-11፤ 6፥22-25)፤ ከዚህም በላይ ወሰን የሌለው የእግዚአብሔር ጸጋ፣ ማንኛውንም ኀጢአተኛ ተቤዠቶ ለዘላለም ክብር ማብቃት እንደሚችል የሚያሳይም ነው። *ሰላዮቹን በሰላም ስለ ተቀበለቻቸው*፤ ያዕ 2፥25 ይመ።

11፥32-38፤ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት አያሌ የእም ነት ዐርበኞች ነበሩ፤ ስለ እነርሱም ብዙ መጻፍ ይቻል ነበር። ለእ ብነት ያህል ግን በእምነታቸው የታወቁ ጥቂት ውንዶችና ሴቶች ተወስተዋል። ሁሉንም አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር፣ በእም ነት ድል መንሣታቸው ነው (ቊ 33)።

11፥32 *እንዴልተርክ* ይህን ቃል ለመግለጽ የገባው የግ ሪኩ ቃል ተባዕት ጾታ ሲሆን፣ ይህም የዕብራውያን መልእክት ጸሓፊ በጾታው ወንድ እንደ ሆነ ያሳያል (በመልእክቱ መግቢያ ላይ "ጸሓፊው" የሚለውን ይመ)። *ስለጌዴዎን፤ ስለባርቅ፤ ስለ ሳምሶን፤ ስለ ዮፍታሔ*፤ መሳ 4፥6-5፥1፤16፥11-8፥35፤11፥-12፥7፤ 13፥24-16፥31 ይመ። *ስለ ሳሙኤል፣ እንዲሁም ስለ ነቢያት*፤ መዝ 99፥6፤ ኤር 15፥1፤ ሐሥ 3፥24፤ 13፥20 ይመ።

11፥33 *የእንበሶችን አፍ*፤ በእንበሶች ጉድጓድ ውስጥ ከተጣለው ዳንኤል ጋር ያነጻጽሩ (ዳን 6)።

11፥34 *የእሳትን ኀይል አጠፉ*፤ በእሳት እቶን ውስጥ ተጥለው ከነበሩት ከዳንኤል ባልንጀሮች ከሲድራቅ፣ ከሚሣቅና ከአብድናጎም ጋር ያነጻጽሩ (ዳን 3)። *ከድካማቸው በረቱ*፤ በእግዚአብሔር ርዳታ ነው (ሮሜ 8፥26፤ 2ቆሮ 12፥9 ይመ)።

11፥35 *ሴቶች ሙታናቸው ተነሡላቸው*፤ ከስራጥታዋ መበለት (1ነገ 17፥17-24) እንዲሁም ከሱናሜዊቷ ሴት (2ነገ 4፥8-36) *ጋር ያነጻጽሩ*። *የተሻለውን ትንሣኤ ለማግኘት ሲሉ መትረፍን ንቀው ለሞት ለሚዳርግ ሥቃይ ራሳቸውን ሰጡ፤ ከዚህም ነጻ ለመውጣት አልፈለጉም*፤ ከክርስቶስ ልደት በፊት በሁለተኛው ምእተ ዓመት ላይ በግፍ የተገደሉትን የመቃብያንን አይሁድ ዐርበኞች የሚያስታውስ ነው (2መቃብያን 7 ይመ)። ይሁንና እዚህ ላይ የተባለው ነገር በብርቱ *ሥቃይ* ውስጥ ሲያ ልፉ፣ በእግዚአብሔር ላይ ባላቸው እምነት እንተው የቆሙትን ስፍር ቊጥር የሌላቸውንና በስም የሚታወቁትንም ሆነ የማ ይታወቁትን አማኞች ሊያመለክት ይችላል።

11፥37 *በድንጋይ ተወገሩ*፤ እውነት በመናገራቸው የተገደሉትን እንደ ካህኑ ዮዳሄ ልጅ እንደ ዘካርያስ ያሉትን ነው (2ዜና 24፥20-22፤ ሉቃ 11፥51)። እንዲሁም የእርምያስ መጽሐ ፍን መግቢያ ይመ። *በመጋዝ ለሁለት ተሰነጠቁ*፤ በጨካኙ ንጉሥ በምናሴ እጅ እንደ ሞተ በአፈ ታሪክ የሚነገርለትን ኢሳ ይያስን ሊሆን ይችላል (የትንቢተ ኢሳይያስን መግቢያ ይመ)።

11፥39 *እነዚህ ሁሉ ስለ እምነታቸው የተመሰከረላቸው ቢሆኑምግ* ሁሉም የእምነት ዐርበኞች የገጠማቸውን ፈተና ወዲ ያውኑ በድል ባይወጡም፣ ሁሉም ግን በእግዚአብሔር ተባርከዋል።

11፥40 *እግዚአብሔር ... ሾሟበልጥ ነገር ሰላዘጋጀ*፤ ለእኛም እንደ ሆነው ሁሉ ለእነርሱም የሰጠው ተስፋ የሚፈ ጸመው "ትንሣኤና ሕይወት" በሆነው በክርስቶስ ነው (ዮሐ 11፥25-26)። እነርሱ ያለ እኛ ፍጹማን ሊሆኑ አይችሉም፤ ከዚህ በፊት የነበሩ ሰዎች ሁሉ ትኩር ብለው ይመለከቱ የነበረው እግዚአብሔርንና የተስፋ ቃሉን ነበር። እግዚአብሔር የሰጣቸው ተስፋ አሁን በኢየሱስ ክርስቶስ እውን ሆነ፤ መዳናቸውም እውን የሆነው በእርሱ በኩል ነው።

12፥1 *እነዚህን የመሰሰሉ ብዙ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን* እዚህ ላይ የሚታየው ምስል በአንድ ትልቅ ቤተ ተውኔት ውስጥ የሚደረገውን ውድድር ይመስላል። ምስክ ሮች የተባሉት በምዕራፍ 11 ላይ የተጠቀሱት የእምነት ዐር በኞች ናቸው። እነርሱም ትርኢት ተመልካች ሳይሆኑ እውነተኛ ምሳሌዎች ናቸው። ምስክሮች የሚለውን ቃል ለመግለጽ የገባው የግሪኩ ቃል "ሰማዕታት" የሚል ትርጒም አለው። ሲመሰክሩ የነበረውም ስለ እምነት ኀይልና ስለ የእግዚአብሔር ታማኝነት

ደን በፊታችን ያለውን ሩጫ በጽናት እንሩጥ።
2የእምነታችን ጀማሪና ፍጹም አድራጊ የሆነውን ኢየሱስን እንመልከት፤ እርሱ በፊቱ ስላለው ደስታ መስቀሉን ታግሦ፣ የመስቀሉንም ውርደት ንቆ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአል። 3እንግዲህ ዝላችሁ ተስፋ እንዳትቈርጡ፣ ከኀጢአተኞች የደረሰበትን እንዲህ ያለውን ተቃውሞ የታገሠውን እር ሱን ዐስቡ።

4ከኀጢአት ጋር ስትታገሉ ገና ደማች ሁን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማች ሁም። 5ልጆች እንደመሆናችሁ እንዲህ በማ ለት የተናገራችሁን ማበረታቻ ቃልም ረስ ታችኋል፦

"ልጄ ሆይ፤ የጌታን ቅጣት አታቃል፤
በሚገሥጽህም ጊዜ ተስፋ አትቊረጥ፤
6ምክንያቱም ጌታ የሚወደውን ይገሥጻል፤
እንደ ልጅ የሚቀበለውንም ይቀጣል።"

7እግዚአብሔር እንደ ልጆቹ ይዞአ ችኋልና የተግሣጽን ምክር ታገሡ፤ ለመሆኑ አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን ነው? 8ልጆች ሁሉ በሚቀጠብት ቅጣት ተካፋይ ካልሆ ናችሁ፣ ዲቃሎች እንጂ ልጆች አይደላች ሁም። 9ከዚህም በላይ፣ እኛ ሁላችን የሚ ቀጡን ምድራዊ አባቶች ነበሩን፤ እናከብራ ቸውም ነበር። ታዲያ ለመናፍስት አባት እንዴት አብልጠን በመገዛት በሕይወት አንኖርም? 10አባቶቻችን መልካም መስሎ እንደታያቸው ለጥቂት ጊዜ ይቀጡን ነበር፤

12፥2 መዝ25፥15፤ ማር16፥19፤ፊል2፥8፤ 91፥ዕብ12፥9፡10፤13፥13
12፥3 ዝ66፥9፤ኢሳ2፥3
12፥4 ዕብ10፥32-34፤ 13፥13
12፥5 ቊ3
12፥6 መዝ94፥12፤ 119፥75፤ምሳ3፥11፡12፤ ራእ3፥19
12፥7 ዘዳ8፥5፤ 2ሳሙ-7፥14፤ ምሳ13፥24
12፥8 1ጴጥ5፥9
12፥9 ዘኍ-16፥22፤ 27፥16፤ኢሳ38፥16፤ ራእ22፥6
12፥10 2ጴጥ1፥4
12፥11 ኢሳ32፥17፤ ያዕ3፥17-18
12፥12 ኢሳ35፥3
12፥13 ምሳ4፥26፤ ገላ6፥1
12፥14 ማቴ5፥8፤ ሮሜ6፥22፤14፥19
12፥15 ዘዳ29፥18፤ ዓሥ5፥4፤ዕብ13፥12፡4፥1
12፥16 ዘፍ25፥29-34፤ 1ቆሮ6፥18
12፥17 ዘፍ27፥30-40
12፥18 ዘፀ19፥12-22፤ 20፥18፤ዘዳ4፥11

እግዚአብሔር ግን የቅድስናው ተካፋዮች እንድ ንሆን ለእኛ ጥቅም ሲል ይቀጣናል።

11ቅጣት ሁሉ በወቅቱ የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፤ በኋላ ግን ለለ መዱት ሰዎች የጽድቅና የሰላም ፍሬ ያስገ ኝላቸዋል።

12ስለዚህ የዛለውን ክንዳችሁንና የደከ መውን ጕልበታችሁን አበርቱ። 13ዐንካሳው እንዲፈወስ እንጂ የባሰውኑ እንዳያነክስ "ለእግራችሁ ቀና መንገድ አብጁ።"

እግዚአብሔርን ስላለመታዘዝ የተሰጠ ማስጠ ንቀቂያ

14ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር የሚቻላችሁን ሁሉ አድርጉ፤ ለመቀደስም ፈልጉ፤ ያለ ቅድስና ማንም ጌታን ማየት አይችልም፤ 15ከእናንተ ማንም የእግዚአብሔር ጸጋ እንዳይጐድልበት ደግሞም መራራ ሥር በቅሎ ችግር እንዳያስከትልና ብዙዎችን እንዳ ይበክል ተጠንቀቁ። 16ለአንድ ጊዜ መብል ሲል ብኵርናውን እንደ ሸጠው እንደ ዔሳው ማንም ሴሰኛ ወይም እግዚአብሔርን የማያ ከብር ሆኖ እንዳይገኝ ተጠንቀቁ። 17በኋ ላም ይህንኑ በረከት ሊወርስ በፈለገ ጊዜ፣ እንደ ተከለከለ ታውቃላችሁ፤ በረከቱን በእ ንባ ተግቶ ቢፈልግም መልሶ ሊያገኘው አልቻለም።

18ሊዳሰስ ወደሚችለውና በእሳት ወደ ሚቃጠለው ተራራ፣ ወደ ጨለማው፣ ወደ

ነበር። *በጽናት እንሩጥ!* ሐሥ 20፥24፤ 1ቆሮ 9፥24-26፤ ገላ 2፥2፤ 5፥7፤ ፊል 2፥16፤ 2ጢሞ 4፥7 ይመ። እዚህ ላይ የክርስትና ሕይወት የቀረበው እንደ ረጅም ርቀት ሩጫ እንጂ እንደ አጭር ርቀት ሩጫ አይደለም። አንዳንድ የአይሁድ ክርስቲያኖች ከስደቱ የተነሣ ውድድሩን አቋርጠው ለመውጣት ተፈትነው ነበር።

12፥2 *ኢየሱስን እንመልከት!* ሯጭ መድረሻ መሥመሩን አትኩሮ እንደሚመለከት ሁሉ፣ እኛም የእምነታችን ግብና ማረፊያ የሆነውን ኢየሱስን አትኩረን መመልከት አለብን (ፊል 3፥13-14)። *ጀማሪና!* የ2፥10 ማብ ይመ። *ፍጹም አድራጊ!* እምነታችን የተጀመረው በእርሱ እንደ ሆነ፣ ፍጻሜ የሚያገኘውም በእርሱ ነው፤ የውድድሩ ጀማሪም ሆነ ፈጻሚ እርሱ ነውና እንዲሁም እርሱ ታላቁ ምስክር ነው፤ ምክንያቱም ከእኛ በፊት ሮጦ አሸንፏል። *በፊቱ ስላለው ደስታ!* የእርሱ ደስታ የእኛ ዘላለማዊ ቤዛነት መፈጸምና በአብ "ቀኝ" መክበሩ ነው። (የ1፥3ማብ ይመ፤ እንዲሁም ከኢሳ 53፥10-12 *ጋር* ያነጻ ጽሩ)። *መስቀሉን ታገሠ!* ፊል 2፥5-8 ይመ። *ውርደት ንቆ!* እንደ ክርስቶስ ሁሉ እኛም ስለ ወንጌል የምንቀበለው የአሁኑ ጊዜ ውርደት ወደፊት ከምናገኘው ክብር *ጋር* ሲወዳደር ቦታ የሚሰጠው አይደለም (11፥26፤ ማቴ 5፥10-12፤ ሮሜ፡፡ 8፥18፤ 2ቆሮ 4፥17፤ 1ጴጥ 4፥13፤5፥1፤10 ይመ)።

12፥3 *እርሱን ዐስቡ!* ደቀ መዛሙርቱ እንዲደርስባቸው ከተጠየቁት መከራ ይበልጥ እጅግ ብርቱ መከራ የተቀበለው እርሱ ነው፤ ይህም እኛ ተስፋ እስክንቈርጥ ድረስ ለሚደርስብን ፈተናና ጭንቀት ታላቅ መጽናናት ይሆንልናል። *ተስፋ እንዳትቈርጡ!* ኢሳ 40፥28-31 ይመ።

12፥4 *ገና ደማችሁን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወ ማችሁም!* ምንም እንኳ ቢሰደዱም ንብረታቸውንም ቢዘረፉ (10፥32-34)፣ በእምነታቸው ግን እስከ መሞት አልደረሱም።

12፥5 *የጌታን ቅጣት!* መከራና ስደት መታየት ያለባ ቸው፣ እግዚአብሔር የልጆቹን መንፈሳዊ ሕይወት እያረመና እያነጻ የሚያሠለጥንበት ተደርገው ነው።

12፥6 *ይቀጣል!* ይህን ቃል ለመግለጽ የገባው የግሪኩ ቃል "ይገርፋል" ማለት ነው። እግዚአብሔር ከስህተታችን ሊመ ልሰን ይገርፈናል።

12፥7 *እንደ ልጆቹ ይዞአችኋልና* እግዚአብሔር ሲቀጣን ልጆቹ ልመሆናችን አንዱ ማስረጃ ነው። የሚቀጣን ተስፋ እንድንቈርጥ ሳይሆን፣ ቅጣቱ የመጽናናትና የመጽናት መሠረት እንዲሆንልን ነው (ቊ. 10)።

12፥11 *የጽድቅና የሰላም ፍሬ ያስገኝላቸዋል!* በፍጹም ታዛዥነት ከተቀበሉት (ቊ. 9 ይመ)፣ ቅጣት መልካምና ጠቃሚ ነው።

12፥13 *ቀና መንገድ አብጁ!* በክርስትና እምነታቸው እንደ ገበ ለሚሽመደመዱ ሰዎች ዕንቅፋት ከመሆን ይልቅ በመንፈሳዊና በምግባራዊ ሕይወታቸው ይበልጥ ማደግ እንዲችሉ ቀጥተኛ (ንጹሕንና ቅድስና የተሞላበት) ሕይወት በመኖር እንድንረዳቸው የቀረበ ጥሪ ነው።

12፥14 *ያለ ቅድስና ማንም ጌታን ማየት አይችልም!* ከ1ጴጥ 1፥51-16፤ 1ዮሐ 3፥2-3 *ጋር* ያነጻጽሩ።

12፥15 *የእግዚአብሔር ጸጋ እንዳይጐድልበት!* ከእግዚ አብሔር ጸጋ "እንዳይጎድል" ወይም የእግዚአብሔርን ጸጋ "ላይዝ እንዳይቀር" ማለት ነው። ይህን የመሰለው ሁኔታ ሊከ ሠት እንደሚችል በ2፥1-4፤6፥4-8 ላይ ተገልጾአል። *መራራ ሥር!* ትዕቢት፣ ጥላቻ፣ ቅናት ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ሊያ ደርስ የሚችል ማንኛውም ነገር ነው።

12፥16 *ብኵርናውን እንደ ሸጠው እንደ ዔሳው!* ዘፍ 25፥29-34 ይመ። ዔሳው፣ ለእውነተኛ ፋይዳዎች ትክክለኛ አመ ለካከት ስላልነበረው ሕይወትን የናቀ ሰው ነበር (ከፊል 3፥18-19 *ጋር* ያነጻጽሩ)። ከብኵርናው ይልቅ ሆዱን ለሚሞላ ምግብ ትልቅ ቦታ በመስጠቱ "ብኵርናውን አቃለለ" (ዘፍ 25፥34)።

12፥17 *እንደ ተስለለው!* ብኵርናውን ዐዘነ እንጂ በኀጢአቱ ንስሓ አልገባም (ዘፍ 27 ቊተለይም ቊ. 41)። ሐሰኑም "ወደ ድኅነት ለሚያደርስ ንስሓ" የሚያበቃው "እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሐዘን" ሳይሆን "ለሞት የሚያበቃ ያለማዊ ሐዘን" ነው (2ቆሮ 7፥10)። *በረከቱን!* የበኵር ልጅ መሆን ነው። የዚህ መልእክት ተደራሲዎች ከደረሰባቸው ስደት እፎይ ለማለት እምነታቸውን ለመጣል ያስቡ ይመስላል። በዚህ በዓለም ለሚገኝ ጊዜያዊ ደስታ ብለው መንፈሳዊ ብኵርናቸውን ቢሸጡ፣ በክርስ ቶስ ያላቸውን በረከት ያጣሉ። *በእንባ!* ዘፍ 27፥34-38 ይመ።

12፥18-21! እነዚህ ቅሶች በሲና ተራራ ላይ ሕግ ሲሰጥ የነበረውን አስፈሪ ሁኔታ ይገልጻሉ (ዘፀ 19፥10-25፤ ዘዳ 4፥11-

ጭጋጉና ወደ ዐውሎ ነፋሱ አልደረሳች ሁም፤ 19ወደ መለከት ድምፅ፣ ወይም ቃልን ወደሚያሰማ ድምፅ አልመጣችሁም፤ የሰሙትም ሊሳ ቃል ተጨምሮ እንዳይናገሯቸው ለመኑ። 20ምክንያቱም "እንስሳ እንኳ ተራራውን ቢነካ፣ በድንጋይ ተወግሮ ይሙት" የሚለውን ትእዛዝ መሸከም አልቻሉም። 21በዚያ ይታይ የነበረውም ሁኔታ እጅግ አስፈሪ ነበርና፣ ሙሴ "በፍርሀት ተንቀጠ ቀጥሁ" አለ።

22እናንተ ግን ወደ ጽዮን ተራራ፣ ወደ ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም፣ ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ መጥታችኋል፤ በደስታ ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፣ 23ስማቸው በሰማይ ወደ ተጻፈው ወደ በኵራት ማኅበር ቀርባችኋል፤ የሁሉ ዳኛ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር፣ ፍጹምነትን ወዳገኙት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፣ 24የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ወደ ሆነው ወደ ኢየሱስ፣ እንዲሁም ከአቤል ደም የተሻለ ቃል ወደሚናገረው ወደ ተረጨው ደም ደርሳችኋል።

25የሚናገረውን እርሱን እምቢ እንዳትሉት ተጠንቀቁ። እነዚያ ከምድር ሆኖ ሲያስጠነቅቃቸው የነበረውን እምቢ ባሉ ጊዜ ካላመለጡ፣ እኛ ከሰማይ የመጣው ሲያስጠነቅቀን ከእርሱ ብንርቅ እንዴት ልናመልጥ እንችላለን? 26በዚያን ጊዜ ድምፁ ያና ወጠው ምድርን ነበር፤ አሁን ግን፣ "ምድርን ብቻ ሳይሆን፣ ሰማያትንም አንድ ጊዜ ደግሜ አናውጣለሁ" ብሎ ቃል ገብቶአል። 27"አንድ ጊዜ "ደግሜ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የማይናወጡት ፣ጸንተው ይኖሩ ዘንድ፣ የሚናወጡት ይኸውም የተፈጠሩት የሚወገዱ መሆናቸውን ነው።

28ስለዚህ ከቶ የማይናወጥ መንግሥት ስለ ምንቀበል እግዚአብሔርን እናመስግን፣ ደግሞም ደስ በሚያሰኘው መንገድ በአክብሮትና በፍርሀት እናምልከው፣ 29ስምላካችን የሚያጠፋ እሳት ነውና።

የመጨረሻ ምክር

13 እርስ በርሳችሁ እንደ ወንድማማች ተዋደዱ። 2እንግዶችን መቀበል አትርሱ፣ አንዳንዶች ይህን ሲያደርጉ፣ ሳያውቁ መላእክትን አስተናግደዋልና። 3በእስር ላይ ያሉትን ከእነርሱ ጋር እንደ ታሰራችሁ ሆና ችሁ ዐስቡአቸው፣ እንዲሁም በሰው እጅ የሚ ንገላቱትን ራሳችሁ መከራ እንደምትቀበሉ አድርጋችሁ ዐስቡአቸው።

4ጋብቻ በሁሉም ዘንድ ይከበር፣ መኝታ ውም ንጹሕ ይሁን፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር በአመንዝሮችና በሴሰኞች ሁሉ ላይ ይፈር ዳል። 5ራሳችሁን ከፍቅረ ንዋይ ጠብቁ፣ ባላ ችሁ ነገር ረክታችሁ ኑሩ፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር፣

"ከቶ አልተውህም፣
በፍጹም አልጥልህም" ብሎአል።
6ስለዚህ በሙሉ ልብ፣
"ጌታ ረዳቴ ነው፣ አልፈራም፣

12፥19 ዘፀ20፥18፤ ዘዳ4፥12፤5፥25፤ 18፥16
12፥20 ዘፀ19፥12፤ 13
12፥21 ዘዳ9፥19
12፥22 ኢሳ24፥23፤ 60፥14፤ማቴ16፥16፤ ገላ4፥26፤ ዕብ11፥10፤ 13፥14፤ራእ14፥1
12፥23 ዘፍ18፥25፤ ዘፀ4፥22፤መዝ94፥21 ፊል3፥12፤ራእ20፥12
12፥24 ዘፍ4፥10፤ ገላ3፥20፤ዕብ9፥19፤ 10፥22፤11፥4፤ጴጥ1፥2
12፥25ዘዳ18፥19፤ ዕብ1፥12፤2፡3፤ 3፥12፤8፥5፤10፥29፤ 11፥7
12፥26 ዘፀ9፥18፤ ሐጌ2፥6
12፥27 ኢሳ34፥4፤ 54፥10፤ቆሮ7፥31፤ ዕብ1፥11፤12፤ 2ጴጥ3፥10፤ዮሐ2፥17
12፥28 መዝ15፥5፤ ዳን2፥44፤ሚል2፥5፤ 4፥2፤ዕብ13፥15
12፥29 ዘፀ24፥17፤ ዘዳ4፥24፤9፥3፤ መዝ97፥3፤ ኢሳ33፥14፤12፥ዕብ1፥7
13፥1 ሮሜ12፥10
13፥2 ዘፍ18፥1-33፤ 19፥1-3፤ኢዮ31፥32፤ ማቴ25፥35፤ ሮሜ12፥13
13፥3 ማቴ25፥36፤ ቈል4፥18፤ዕብ10፥34
13፥4 ዘዳ22፥22፤ ሚል2፥15፤1ቆሮ6፥9፤ 7፥38፤1ጢሞ4፥3፤ ራእ22፥15
13፥5 ዘዳ31፥6፡8፤ ኢሱ1፥5፤ፊል4፥11፤ 1ጢሞ3፥3፤6፥8
13፥6 መዝ118፥6፡8

12፤ 5፥22-26 ይመ)። ዝርዝር ሐሳቡ የሚያተኩረው በብሉይ ኪዳን ተራራ ሥርዐት፣ አስፈሪ ማስጠንቀቂያዎችና ከባድ ቅጣቶች ላይ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ግን እንዲህ ዐይነት የሚያስፈራ ኪዳን ስለሌላቸው፣ ወደ ብሉይ ኪዳኑ ሥርዐት ለመመለስ ማሰብ አይገባቸውም።

12፥22 *ጽዮን ተራራ*፤ በኢየሩሳሌም ወይም በደቡብ ምሥራቅ ክፍል የምትገኘውን የጽዮን ተራራ ሳይሆን፣ ሰማያዊቷን የእግዚአብሔር ከተማና ከእርሱም ጋር በዚያ የሚኖሩትን ነው (11፥10፡13-16፤13፥14፤ ፊል 3፥20 ይመ)። ብሉይ ኪዳን የተሰጠ በት ሁኔታና (ቊ. 18-21) የአዲስ ኪዳንን ልዩ ባሕርይ (ቊ. 22-24)፣ በሁለቱ ኪዳኖች መካከል መሠረታዊ ልዩነት ያለ መሆኑን ከማመልከቱም በላይ፣ ወደ አይሁድ እምነት ለመመለስ የሚያ ስቡትን ብርቱ ማስጠንቀቂያና ማሳሰቢያ ይሰጣቸዋል። ወደ ... አእላፋት መላእክት፤ ራእ 5፥11-12 ይመ።

12፥23 *በኵራት ማኅበር*፤ በጥቅሉ የቤተ ክርስቲያን አካል የሆኑትን አማኞች ነው፤ (1) ቀደም ሲል በቊጥር 22 ላይ ስለተጠቀሱ፣ መላእክቱን ሲሆን አይቸልም፤ (2) ምንም እንኳ ክርስቶስ በኵር ተብሎ ቢጠራም (1፥6፤ ሮሜ 8፥29፤ ቈላ 1፥15-18፤ ራእ 1፥5) በዚህ ቁጥር ላይ "በኵራት" የሚለው ቃል እርሱን አያመለክትም፤ ምክንያቱም የገሪኩ ቃል ብዙ ቊጥር ነው፤ (3) ስማቸው በሰማይ ስለተመዘገበ የተቤዠ መሆናቸውን ያመለክታል (ራእ 3፥5፤ 13፥8፤ 17፥8፤ 20፥12፤ 21፥27 ይመ)። በኵራት የሚለው ስያሜ የሚያመለክተው ልሂቁ በኵርና "ሁሉን ወራሽ" (ዕብ 1፥2) ከሆነው ከክርስቶስ ጋር አብረው ወራሾች መሆናቸውን ነው። *የሁሉ ዳኛ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር*፤ 4፥13፤ ሮሜ 14፥10-12፤ 1ቆሮ 3፥10-15፤ 2ቆሮ 5፥10፤ ራእ 20፥11-15 ይመ። *ፍጹምነትን ወዳገኙት ወደ ጻድቃን መንፈሶች*፤ በአብዛኛው ከክርስትና እምነት በፊት የነበሩትን እንደ አቤልና (11፥4) ኖኅ (11፥7) የመሳሰሉ አማ ኞችን ነው። እነዚህ ሰዎች "መንፈሶች" የተባሉት ትንሣኤን ስለሚጠባበቁ ሲሆን፣ ጻድቃን የተባሉት ደግሞ እግዚአብሔር የአብርሃምን እምነት ጽድቅ አድርጎ እንደ ቈጠረለት ሁሉ የእነርሱንም እምነት ጽድቅ አድርጎ ሰለ ቈጠረላቸው ነው(ሮሜ 4፥3 ይመ)። ይሁን እንጂ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቱ ፍጹም እስኪያደርገው ድረስ እውነተኛ ጽድቅ አይኖርም (11፥40፤ ሮሜ 3፥24-26፤ 4፥23-25 ይመ)።

12፥24 *የአዲስ ኪዳን መካከለኛ*፤ የ7፥22፤ 8፥6 እና ማብ ራሪያውን እንዲሁም 8፥13፤ 9፥15፤ 1ጢሞ 2፥5 ይመ። *ከአቤል ደም የተሻለ ቃል ወደሚናገረው*፤ የአቤል ደም ስለ ፍትሕና ስለ ፍርድ ሲጮኽ (የዘፍ 4፥10 ማብ ይመ)፣ በመስቀል ላይ የፈሰሰው የክርስቶስ ኢየሱስ ደም ግን ስለ ይቅርታና ስለ ዕርቅ ይጮኻል (9፥12፤ 10፥9፤ ቊላ 1፥20፤ 1ዮሐ 1፥7)።

12፥25 *የሚናገረውን*፤ እግዚአብሔርን ነው። *ከምድር ሆኖ ሲያስጠነቅቃቸው*፤ በሲና ተራራ ነው። *ከሰማይ የመጣው ሲያ ስጠነቅቀን*፤ ክርስቶስ ከሰማይም የሰማይም ነው (1፥1-3፤ 4፥14፤ 6፥20፤ 7፥26፤ 9፥24)። የተቀበልነው ታላቅ መገለጥ በመሆኑ ትልቅ ኀላፊነት አለብን፤ ስለዚህም ትልቅ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልገናል (2፥2-4)።

12፥26 *ያናወጠው ምድርን ነበር*፤ ዘፀ 19፥18፤ መሳ 5፥5፤ መዝ 68፥7-8 ይመ።

12፥27 *ደግሜ*፤ ክርስቶስ ጻዓም ተመልሶ ሲመጣ ታላቅ ነውጥ ይሆናል። *የማይናወጡት*፤ የሚመጣውን መንግሥት ነው (ቊ. 28)።

12፥28 *ደስ በሚያሰኘው መንገድ...እናምልከው*፤ ዮሐ 4፥19-24፤ ሮሜ 12፥1 ይመ።

12፥29፤ አማራጭ ትርጒሙን ይመ። ከዘፀ24፥17፤ ዘዳ9፥3 *ጋር ያነጻጽሩ*።

13፥2 *ሳያውቁ መላእክትን አስተናግደዋልና*፤ ይህም አብርሃም (ዘፍ 8)፣ ጌዴዎን (መሳ 6) እንዲሁም ማኑሄ (መሳ 13) እንዳደረጉት ነው።

13፥3 *በእስር ላይ ያሉትን...እንዲሁም በሰው እጅ የሚንገላቱትን ...ዐስቡአቸው*፤ 10፥32-34፤ 1ቆሮ 12፥26 ይመ።

13፥5፤ *ከፍቅረ ንዋይ*፤ ሉቃ 12፥15፡21፤ ፊል4፥10-13፤ 1ጢሞ6፥6-10፡ 17፥19 ይመ። *ረክታችሁ ኑሩ*፤ ፊል4፥11-12፤1ጢሞ6፥8 ይመ።

ሰው ምን ሊያደርገኝ ይችላል?" እንላለን።

7የእግዚአብሔርን ቃል የነገሯችሁን መሪዎ ቻችሁን ዐስቡ፤ የኑሮአቸውን ፍፁ ተመል ከቱ፤ በእምነታቸውም ምሰሉአቸው። 8ኢየ ሱስ ክርስቶስ ትናንት፣ ዛሬም ለዘላለምም ያው ነው።

9በልዩ ልዩ ዐይነት እንግዳ ትምህርቶች አትወሰዱ፤ ልባችን የሚጸናው በጸጋ እንጂ የምግብ ሥርዐት በመጠበቅ አይደለም፤ ይህንን ሥርዐት የሚጠብቁት እንኳ በዚህ አልተጠቀሙም። 10በድንኳኒቱም የሚያገለ ግሉ ከዚያ ሊበሉ መብት ያላገኙበት መሠ ዊያ አለን።

11ሊቀ ካህናቱ ስለ ኀጢአት ስርየት የሚሆነውን የእንስሳት ደም ይዞ ወደ ቅድ ስተ ቅዱሳን ይገባል፤ የእንስሳቱ ሥጋ ግን ከሰፈር ውጭ ይቃጠላል። 12እንዲሁም ኢየ ሱስ በራሱ ደም አማካይነት ሕዝቡን ሊቀ ድስ ከከተማው በር ውጭ መከራን ተቀበለ። 13ስለዚህ እኛም እርሱ የተሸከመውን ውር ደት ተሸክመን ከሰፈር ውጭ ወደ እርሱ እንውጣ። 14ምክንያቱም በዚህ ቋሚ ከተማ የለንም፤ ነገር ግን ወደፊት የምትመጣዋን ከተማ እንጠብቃለን።

15ስለዚህ ዘወትር የምስጋናን መሥዋዕት ይኸውም ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ በኢየሱስ አማካይነት ስለእግዚአብሔር እና ቅርብ። 16ደግሞም መልካም ማድረግንና ያላችሁንም ከሌሎች ጋር መካፈልን አት

13፥7 ቍ17:24፤ 1ቆሮ16፥16፤ ዕብ4፤12፥12 13፥8 መዝ102፥27፤ ዕብ1፥12 13፥9 ኤፌ4፥14፤ ቈላ2፥7፡16፤ዕብ9፥10 13፥10 1ቆሮ9፥13፤ 10፥18፤ዕብ8፥5 13፥11 ዘወጽ29፥14፤ ዘሌ4፥12፡21፤ዘኍ19፥11፤ 16፥15፡27 13፥12 ዮሐ19፥17፤ ሮሜ3፥25፤ኤፌ5፥26 13፥13 ሉቃ9፥23፤ ዕብ11፥26 13፥14 ፊል3፥20፤ ዕብ11፥10፡27፤ 12፥22፡27 13፥15 ኢሳ57፥19፤ ሆሴ14፥2፤ኤፍ2፥5 13፥16 ሮሜ12፥13፤ ፊል4፥18

13፥17 ቍ7:24፤ ኢሳ62፥6፤ሕሥ20፥28 13፥18 ሐሥ23፥1፤ 1ተሰ5፥25 13፥19 ፊሞ22 13፥20 ዘፍ9፥16፤ 17፥7፡13፡19፤ ኢሳ55፥3፤61፥8፤ ሕዝ37፥26፤ ማቴ26፥28፤ ዮሐ10፡11፤ሐሥ2፥24፤ ሮሜ15፥33

ርሱ፤ ስንዚአብሔር ደስ የሚሰኘው እንደዚህ ባለው መሥዋዕት ነውና።

17ለመሪዎቻችሁ ታዘዙ፤ ተገዙላቸውም። ምክንያቱም እነርሱ በብርቱ የሚያስጠይቃ ቸው ነገር ስላለባቸው፣ ስለ ነፍሳችሁ ጒዳይ ይተጋሉ። ስለዚህ ሥራቸውን በሐዘን ሳይ ሆን በደስታ ማከናወን እንዲችሉ ታዘዚ ቸው። አለበለዚያ አይበጃችሁም።

18ለእኛ ደግሞ ጸልዩልን። በሁሉም መን ገድ በመልካም አኗኗር ለመኖር የሚናፍቅ ንጹሕ ኅሊና እንዳለን እርግጠኞች ነን። 19ዙሪ ለይም ወደ እናንተ በፍጥነት ተመልሼ እን ድመጣ ትጸልዩልኝ ዘንድ ዐደራ እላችኋ ለሁ።

20በዘላለም ኪዳን ደም የበጎች ታላቅ እረኛ የሆነውን ጌታችን ኢየሱስን ከሞት ያስነሣው የሰላም አምላክ፣ 21ፈቃዱን እን ድታደርጉ በመልካም ነገር ሁሉ ያስታ ጥቃችሁ፤ ደስ የሚያሰኘውንም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእኛ ያድርግ፤ ለእ ርሱ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን።

22ወንድሞች ሆይ፤ የጻፍሁላችሁ መልእ ክት አጭር እንደ መሆኑ፣ የምክር ቃሌን በትዕግሥት እንድትቀበሉ ዐደራ እላች ኋለሁ።

13፥21 ሮሜ11፥36፤ 2ቆሮ9፥8፤ፊል2፥13፤1ዮሐ3፥22
13፥22 1ጴጥ5፥12

13፥7 *የእንዚአብሔርን ቃል የነገሯችሁን መሪዎቻች ሁን*፤ 2፥3፤ 5፥12 ይመ። *የኑሮአቸውን ፍፁ ተመልከቱ*፤ ምናል ባት ይህ የሚያመለክተው እነዚህ ምሳሌያዊ ሕይወት የኖሩ መሪ ዎች ሞተው ሊሆን ይችላል። *በእምነታቸውም ምሰሉአቸው*፤ 6፥12፤ 1ቆሮ 4፥16፤ ኤፌ 5፥1፤ 1ተሰ 1፥6-7፤ 2፥14፤ 3ዮሐ 11 ይመ።

13፥8 *ኢየሱስ ክርስቶስ...ያው ነው*፤ ክርስቶስ ከቶ እንደማይ ለወጥ የሚያሳይ ሲሆን፣ ከፍ ሲል ከሚገኘው ቀኖር ጋር እንደሚ ያያዝ ምንም ጥርጥር የለውም። የቀደሙት መሪዎቻቸው እምነት የተመሠረተው መቼም በማይለወጠው ክርስቶስ ላይ ነው። ትናንት፣ ምናልባት ክርስቶስ በዚህ ምድር በነበረበት ጊዜ የዐይን ምስክሮች እርሱን ያዩበት ጊዜ ይሆናል (2፥3)። *ዛሬም* የዐይን ምስክሮች ያዩት ክርስቶስ ዛሬም ያው ነው፤ ስለ እርሱም የተናገሩት ሁሉ እው ነት ነው። *ለዘላለምም* ሁልጊዜ የሚኖረው በዚህ ዐይነት ነው። የክርስቶስን ፍጹም ሉዓላዊነት እንደ ተራ ነገር በመቍጠር ከእርሱ እጅግ ወደሚያዝው ወደ አሮን ሥርዐተ ክህነትና ወደ መሥዋዕቱም መመለስ (ምዕ 5-10 ይመ) ግለት ወንጌልን መናቅ ግለት ነው።

13፥9 *የምግብ ሥርዐት*፤ የአይሁድ የሕግ መምህራን እንደ ሚሉት ነው። የቀድሞው የመሲ ሥርዐት ክርስቶስ በመሥቀል ላይ በሞተ ጊዜ ተሽሯል፤ ስለዚህ ዳንመኛ እንዲያንሰራራ መደረግ የለበትም።

13፥10 *መሠዊያ አለን*፤ የአሮን ሥርዐተ ክህነት መወገዱ ንና ክርስቶስ ልዩና ብቸኛ ካህን በሆነበት በመልከ ጼዲቅ ሥርዐተ ክህነት መተካቱን ለማመልከት ይሆናል። *ሊበሉ መብት ያላገኙ በት*፤ በስርየት ቀን ካህናቱ ከመሥዋዕቱ መብላት አይችሉም፤ እኛ ግን ከመሥዋዕቱ መካፈል እንችላለን፤ የምንካፈለውም በመ ንፈስ ክርስቶስን በመሥዋዕቱ በመቀበል ነው (ዮሐ 6፥48-58 ይመ)። በብሉይ ኪዳን ሥር ከነበሩት ካህናት ይልቅ እኛ እጅግ የሚበ ልጥ መብት አለን።

13፥11 *ከሰፈር ውጭ ይቃጠላል*፤ ዘሌ 4፥12 እና ማብራ ሪያውን እንዲሁም፤ 16፥17 ይመ።

13፥12 *እንዲሁም ኢየሱስ...ከከተማው በር ውጭ መከራን ተቀበለ*፤ ክርስቶስ ከዚየሩሳሌም ውጭ መሞቱ የሕዝቡ ኀጢአት መወገዱን ያሳያል፤ ለመሥዋዕት የሚቀርበው የእንስሳት አካል ከእስራኤል ሰፈር ውጭ ይጣል ነበር።

13፥13 *ከሰፈር ውጭ ወደ እርሱ እንውጣ* ከይሁዲነት ወደ ክርስቶስ ዘወር እንዲሉ የቀረበ ጥሪ ነው። እርሱ ከከተማው ውጭ በውርደት እንደ ሞተ፣ የዚህ መልእክት ተደራሲዎችም ከይሁዲነት ወደ ክርስቶስ ዘወር ሲሉ ውርደትን ለመቀበል ፈቃደኞች መሆን አለባቸው።

13፥14 *የምትመጣዋን ከተማ* የ11፥10፡14:16 ማስታወሻ ይመ።

13፥15 *የምስጋናን መሥዋዕት*፤ እዚህ ላይ "መሥዋዕት" የሚለው ቃል ተምሳሌታዊ በሆነ አገላለጽ የዝባው ለእግዚአብሔር የሚቀርበውን ስጦታ ለማመልከት ነው (ሮሜ 12፥1፤ ፊል 4፥18 ይመ)። እንስሳትን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ ፍጹም ቀርቶአል።

13፥17 *ለመሪዎቻችሁ*፤ በቍጥር 7 ላይ የተጠቀሱትንና የሞቱትን ሳይሆን፣ አሁን በሕወት ያሉትን መሪዎቻቸውን ነው። *ተገዙላቸውም*፤ ጸሓፊው እንዲህ ሲል ለፈላጭ ቈራጭ አመራር ቦታ መስጠቱ አይደለም (3ዮሐ 9-10 ይመ)፤ በመሳው አዲስ ኪዳን ውስጥ ባለሥልጣኖችን ማክበር፣ በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ሥርዐ ትን ማስፈን ተገቢ እንደ ሆነ ትምህርት ተሰጥቶአል።

13፥19 *ወደ እናንተ በፍጥነት ተመልሼ እንድመጣ* የዚህ መልእክት ጸሓፊ ግን እንደ ሆነና የትስ ሆኖ እንደሚጽፍ በውል ባይታወቅም፣ "ተመልሼ እንድመጣ" የሚለው ሐረግ ተደራሲዎቹን ለመጎብኘት ፈልጎ ምናልባት በአገልግሎቱ ምክ ንያት የዘገየ መሆኑን ያመለክታል። እስር ቤት እንዳልሆነ ግን ከቍ 23 በግልጽ መረዳት ይቻላል።

13፥20-21፤ ይህ ቃል ቡራኬ ለመልእክቱ ተገቢ መደምደ ሚያ ነው። *የሰላም አምላክ* በቃለ ቡራኬ ጊዜ ለእግዚአብሔር የሚውል አገላለጽ ነው (ሮሜ 15፥33፤ 16፥20፤ ፊል 4፥9፤ 1ተሰ 5፥23 ይመ)።

13፥20 *በዘላለም ኪዳን*፤ አዲሱን ኪዳን ነው (ዮ8፥8-12 ማብ ይመ)። ኢርምያስ በ31፥31 ላይ አዲሱ ኪዳን በማለት የጠ ራውን፣ በ32፥40 ላይ የዘላለም ኪዳን በማለት ይገልጸዋል (ኢሳ 55፥3 እና ማብራሪያውን እንዲሁም፤ 61፥8 ይመ)። ስለ ኪዳኑ ደም በተመለከተ የ10፥29 ማብ ይመ። *ታላቅ እረኛ* ለምሳሌ መዝ 23፤ ኢሳ 40፥11፤ ሕዝ 34፥11-16፤ 23፤ 37፥24፤ ዮሐ 10፥2-3፤ 11፤ 14፤ 27፤ 1ጴጥ 2፥25፤ 5፥4 ይመ።

13፥22-25፤ በስተመጨረሻ እንደ አዲስ ማሳሰቢያ የተሰጠ ክፍል ነው።

13፥22 *አጭር*፤ መልእክቱን አጭር የሚያሰኘው ክርስቶስ ከሁሉ የሚበልጥ መሆኑን ከዚህ በላይ መግለጽ ሲቻል፣ ከብዙ በጥቂቱ ብቻ የቀረበ በመሆኑ ነው። *የምክር ቃሌን*፤ የመልእክቱ

[23]ወንድማችን ጢሞቴዎስ እንደተፈታ ታውቋ ዘንድ እፈልጋለሁ፤ ቶሎ ከመጣ፣ ከእርሱ ጋር ላያችሁ እመጣለሁ።

13፥23 ሐሥ16፥1

13፥24 ቊ7:17፣ ሐሥ18፥2

13፥25 ቊ44፥18

[24]ለመሪዎቻችሁ ሁሉና ለቅዱሳን ሁሉ ሰላምታ አቅርቡልኝ። ከኢጣሊያ የሆኑትም ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።

[25]ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

ፍሬ ሐሳብ አማኞች በክርስትና ሕይወታቸው እየጎለበቱና እየበሰሉ እንዲሄዱ፣ ከክርስቶስም ተለይተው እንዳይወድቁ የሚያሳስብ ነው።

13፥23 *ጢሞቴዎስ እንደተፈታ* የመልእክቱ ተደራሲዎች በሚገባ የሚያውቁት ጢሞቴዎስ ከእስር ቤት የተፈታው በቅርቡ ነው።

13፥24 *ለመሪዎቻችሁ*፣ በቊ17 ላይ ተጠቅሰዋል። *ከኢጣሊያ የሆኑትም* ይህ መልእክት የተጻፈው ከኢጣሊያ ወይም ለኢጣሊያ ሰዎች ነው ማለት አይደለም። ጸሓፊው በኢጣሊያ ለሚገኙ አማኞች ሰላምታውን እያስተላለፈ ነው።

የያዕቆብ መልእክት

መግቢያ

ጸሓፊው

ጸሓፊው ራሱ ያዕቆብ እንደ ሆነ ገልጸአል (1፥1)፤ እርሱም የጌታ ወንድም እና በሐዋርያት ሥራ ም 5 ላይ ለተጠቀሰው ጉባኤ መሪ ሳይሆን አይቀርም። በአዲስ ኪዳን ውስጥ አራት ሰዎች በዚህ ስም ተጠርተዋል። ሐዋርያው ያዕቆብ የመጀመሪያው ሰማዕት ሆኖ በ44 ዓ.ም. ስለተሠየፈ፣ የዚህ መልእክት ጸሓፊ እርሱ ሊሆን አይችልም። "ያዕቆብ" በሚል ስም የተጠሩ ሌሎች ሁለት ሰዎች አሉ፤ ሆኖም እነርሱ እንዳልጻፉት ግልጽ ነው። በማቴ 13፥55 ላይ ከኢየሱስ ወንድሞች ስም ዝርዝር ውስጥ በመጀመሪያ የተጠቀሰው ያዕቆብ ከወንድሞቹ ሁሉ እርሱ ታላቅ ሳይሆን አይቀርም። ያዕቆብ በመጀመሪያ በጌታ አላመነም ነበር፣ ስለዚህም የተግዳሮት ሐሳብ በኢየሱስ ላይ ይሰነዝር ነበር (ዮሐ 7፥2-5)። በኋላ ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የላቀ ሞገስ ያለው ሰው ሆነ፤ ስለዚህም፦

1) ጌታ ኢየሱስ ከትንሣኤ በኋላ ራሱን ከገለጠላቸው ጥቂት ደቀ መዛሙርት መካከል እነሆ እርሱ አንዱ ነው (1ቆሮ 15፥7)፤

(2) ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን "ዐምድ" በማለት ጠቅሶታል (ገላ 2፥9)።

(3) ጳውሎስ ክርስቶስን አምኖ ከተለወጠ በኋላ በኢየሩሳሌም የመጀመሪያ ጉብኝቱን ሲያደርግ ከያዕቆብ ጋር ተገናኝቶአል (ገላ 1፥19)።

(4) ጳውሎስ ለመጨረሻ ጊዜ ኢየሩሳሌምን በጐበኘበት ጊዜም እንዲሁ ከያዕቆብ ጋር ተገናኝቶአል (ሐሥ 21፥18)።

(5) ጴጥሮስ ከእስር ቤት እንደወጣ ለያዕቆብ እንዲነገረው አሳስቦ ነበር (ሐሥ 12፥17)፤

(6) በኢየሩሳሌም ዐቢይ ጉባኤ ላይ ያዕቆብ መሪ ነበር (ሐሥ 15፥13)።

(7) ይሁዳ በመልእክቱ ውስጥ ማንነቱን የገለጸው፣ "የያዕቆብ ወንድም" (ይሁዳ 1፥1) በማለት ነው፤ ከዚህ እንደምንረዳው ያዕቆብ እጅግ ታዋቂ ሰው እንደ ነበረ ነው። ይኸው ያዕቆብ በሰማዕትነት ሕይወቱ ያለፈው በ62 ዓ.ም. ገደማ ነበር።

መልእክቱ የተጻፈበት ጊዜ

አንዳንዶች ይህ መልእክት የተጻፈው በ60 ዓ.ም. መግቢያ ላይ ነው ይላሉ፤ ይሁን እንጂ ከ50 ዓ.ም. በፊት የተጻፈ ስለ መሆኑ አንዳንድ ምልክቶች ያስገነዝባሉ፤

1. መልእክቱ የአይሁድን አስተሳሰብ ይዞ በመገኘቱ በቤተ ክርስቲያኒቱ አይሁድ ምእመናን በብዛት በሚገኙበት ወቅት የተጻፈ ነው።

2. በቤተ ክርስቲያኒቱ የሚገኙት ጉባሬዎችም "ሽማግሌዎችና" (15፥14) "አስተማሪዎች" (3፥1) ብቻ ነበሩ።

3. አሕዛብ መገረዝ አለባቸው የሚል ክርክር አልተሠማም ነበር፤

4. በግሪክ "ምኵራብ" የሚለው ቃል የክርስቲያኖችን ስብሰባ ለማመልከት (2፥2) ጥቅም ላይ መዋሉ ይህ መልእክት የተጻፈበትን ጊዜ በትክክል ያመለክታል፣ ይኸውም መልእክቱ ከአዲስ መጻሕፍት ሁሉ ቀዳሚ ሆኖ የተጻፈ ነው፤ ምናልባት ከዚህ መልእክት በፊት የተጻፈ አለ ከተባለ ወደ ገላትያ ሰዎች የተጻፈው መልእክት ብቻ ነው።

ተደራሲያኑ

የዚህ መልእክት ተደራሲያን እነማን እንደ ሆኑ በግልጽ የምናገኘው በ1፥1 ላይ ነው፤ ይኸውም "በአሕዛብ መካከል ተበትነው ለሚገኙት አሥራ ሁለት ነገዶች" የሚል ነው። አንዳንዶች ይህ አባባል በአጠቃላይ ክርስቲያኖችን ያመለክታል ቢሉም ፣ "ለአሥራ ሁለቱ ነገዶች" የሚለው ስያሜ በይበልጥ የሚያመለክተው የአይሁድ ክርስቲያኖችን ነው። ከዚህም በላይ መልእክቱ የአይሁድን የአገላለጽ ስልት ይዞ የሚንገዝ ስለ ሆነ ተደራሲያኑ አይሁድ መሆናቸው ግልጽ ነው (በ5፥4 ላይ "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር" የሚለው አይሁድ እግዚአብሔርን ለመጥራት የሚጠቀሙበት የማዕረግ ስም ተደራሲያኑ ያለ ጥርጥር አይሁድ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው)። የዚህ መልእክት ተደራሲያን ክርስቲያኖች ለመሆናቸውም ከ2፥1፤ 5፥7-8 መረዳት ይቻላል። እነዚህ ክርስቲያኖች የመጀመሪያዎቹ የኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች እንደ ነበሩ ይገመታል፤ እነርሱም እስጢፋኖስ በሰማዕትነት ከሞተ በኋላ በፊንቄ፣ በቆጵሮስና በሶርያዋ አንጾኪያ ተበትነው ይገኙ ነበር (ሐሥ 8፥1፤11፥19)። ያዕቆብ ስለ ፈተናና ስለ ጭቈና ማውሳቱ ተደራሲያኑ በቅርብ የሚያውቃቸው የኢየሩሳሌም ምእመናን መሆናቸውን የሚያመለክት ነው። ያዕቆብ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ መሆኑ፣ የተበተኑትንና በጭንቀት ላይ የሚገኙትን ምእመናን ለማስተማርና ለማጽናናት፣ የመጋቢነት ተግባሩን በጽሑፍ ሲያከናውን ይታያል።

የመልእክቱ ልዩ ባሕርይ

ይህን መልእክት ልዩ የሚያደርጉት ባሕርያት የሚከተሉት ናቸው፤

(1) የማያጠራጥር ግልጽ የሆነ አይሁዳዊ ገጽታው፣ (2) ሕያው በሆነው የክርስትና ሕይወት ላይ አጽንኦት ማድረጉ፤ ይህም የክርስትና ሕይወት በበጎ ሥራ የሚገለጽ ነው ማለቱ፣ (3) ቅልብጭ ያለው መዋቅሩ፣ (4) ከኢየሱስ የተራራ ስብከት ጋር ያለው ተጓዳኝነት (2፥5ን ከማቴ 5፥3፤3፥10-12ን ከ ማቴ 5፥12ን ከማቴ5፥15-20፤ 5፥12ን ከማቴ5፥33-37 ጋር ያነጻጽሩ)፣ (5) መጽሐፈ ምሳሌን ከመሳሰሉ የብሉይ ኪዳን የጥበብ መጻሕፍት ጋር ተመሳሳይ መሆኑና፣ (6) መልእክቱ የተጻፈበት የግሪክ ቋንቋ አጠቃቀም በጣም ግሩም መሆኑ ናቸው::

አስተዋፅኦ

1. ሰላምታ (1፥1)
2. ፈተናና መከራ (1፥2-18)
   ሀ. የእምነት መፈተን (1፥2-12)
   ለ. የመከራ መንሥኤ (1፥13-18)
3. መስማትና ማድረግ (1፥19-27)
4. አድልዎ መወገዙ (2፥1-13)
5. እምነትና ሥራ (2፥14-26)
6. አንደበትን መግዛት (3፥1-12)
7. ሁለት ዐይነት ጥበብ (3፥13-18)
8. ዓለማዊነትን በተመለከተ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (ም 4)
   ሀ. ጠበኝነት (4፥1-3)
   ለ. በመንፈሳዊ ረገድ ታማኝ ሆኖ አለመገኘት (4፥4)
   ሐ. ትዕቢት (4፥5-10)
   መ. ሐሜተኝነት (4፥11-12)
   ሠ. ጉረኝነት (4፥13-17)
9. ለጨቋኝ ባለ ጠጎች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (5፥1-6)
10. ልዩ ልዩ ምክሮች (5፥7-20)
    ሀ. በመከራ ስለ መታገሥ (5፥7-11)
    ለ. ስለ መሐላ (5፥12)
    ሐ. በእምነት ስለሚደረግ ጸሎት (5፥13-18)
    መ. ከእውነት ስላፈገፈጉ ሰዎች (5፥19-20)

1 የእግዚአብሔርና የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ የሆነው ያዕቆብ፥ ለዐሥራ ሁለቱ ነገዶች፥

ሰላም ለእናንተ ይሁን።

መከራና ፈተና

2 ወንድሞቼ ሆይ፥ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት 3 ምክንያቱም የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁና። 4 ምንም የማይጐድላችሁ ፍጹማንና ምሉዓን እንድትሆኑ ትዕግሥት ሥራውን ይፈጽም። 5 ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉም የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል። 6 ዳሩ ግን ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ ምክንያቱም የሚጠራጠር ሰው በነፋስ እንደሚገፋና እንደሚናወጥ የባሕር ማዕበል ነውና። 7 ያ ሰው፥ ከጌታ አንዳች ነገር አገኛለሁ ብሎ አያስብ፥ 8 እርሱ በሁለት ሐሳብ የተያዘና በመንገዱ ሁሉ የማወላውል ነው።

9 ዝቅ ያለው ወንድም ከፍ በማለቱ ይመካ። 10 ባለ ጸጋውም በመውረዱ ይመካ፥ እንደ ሣር አበባ ይረግፋልና። 11 ፀሓይ በነዳድ ሙቀቷ ወጥታ ሣሩን ታጠወልጋለችና፥ አበባውም ይረግፋል፥ ውበቱም ይጠፋል፤ እንዲሁም ባለ ጸጋ ሰው፥ በዕለት ተግባሩ ሲዋ ትት ሳለ ይጠፋል።

12 በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፥ ምክንያቱም ፈተናን ሲቋቋም እግዚአብሔር ለሚወዱት የሰጠውን ተስፋ፥ የሕይወትን አክሊል ያገኛል።

13 ማንም ሲፈተን፥ "እግዚአብሔር ፈተኝኝ" አይበል፥ ክፉ ነገር ሊፈተኑ የማይችሉ እርሱም ማንንም አይፈትንም። 14 ነገር ግን እያንዳንዱ የሚፈተነው በራሱ ክፉ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው። 15 ምኞትም ከፀነሰች በኋላ ኀጢአትን ትወልዳለች፥ ኀጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።

16 የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ አትታለሉ። 17 በጎ ስጦታና ፍጹም በረከት ሁሉ ከላይ ከሰማይ ብርሃናት አባት ይወርዳሉ፥ በእርሱ ዘንድ መለዋወጥ ከመዞር የተነሣ የሚያርፍ ጥላም የለም። 18 የፍጥረቱ በኵራት እንድንሆን በገዛ ፈቃዱ በእውነት ቃል ወለደን።

ሰምቶ በሥራ ላይ ማዋል

19 የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ይህን አስተውሉ፥ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ፥ ለመናገር የዘገየ፥ ለቍጣም የዘገየ ይሁን፥ 20 የሰው ቍጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አያመጣምና። 21 ስለዚህ ርኵሰትንና ተንሰራፍቶ የሚገኘውን ክፋትን አስወግዳችሁ ነፍሳችሁን ማዳን የሚችለውን፥ በውስጣችሁም የተተከለውን ቃል በትሕትና ተቀበሉ።

22 ቃሉ የሚናገረውን አድርጉ እንጂ ሰሚዎች ብቻ ሆናችሁ ራሳችሁን አታታልሉ። 23 ቃሉን የሚሰማ፥ ነገር ግን የሚፈጽመው የማይፈጽም ሰው ፊቱን በመስተዋት እንደሚያይ ሰው ነው፥ 24 ራሱንም አይቶ ይሄዳል፤ ወዲያውም ምን እንደሚመስል ይረሳል። 25 ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን ፍጹም ሕግ ተመል

1፥19 ቍ፥16፤ ምሳ10፥19፤ያዕ2፥5፤ 3፥3-12 1፥20 ማቴ5፥22 1፥21 ኤፌ1፥13፤ቈላ2፥12፤ 2፥22 ማቴ7፥21፤ ያዕ2፥14-20 1፥25 መዝ19፥7፤ ሮሜ8፥32፤13፥17፤ ገላ2፥4፤ያዕ2፥12

1፥1 ዘዳ32፥26፤ ዮሐ7፥35፤ ሐሥ15፥13፤ 23፥26፣7፤ሮሜ1፥1፤ ቲቶ1፥1፤ዕዮ1፥1 1፥2 ቍ፥12፤ ማቴ5፥12፤ ዕብ10፥34፤12፥11 1፥3 ዕብ10፥36፤ 1ጴጥ1፥7 1፥4 1ቆሮ2፥6 1፥5 1ነገ3፥9፤10፤ መዝ51፥6፤ምሳ2፥3-6፤ ዳን1፥17፤2፥21፤ ማቴ7፥7 1፥6 ማቴ21፥21፤ ማር11፥24 1፥8 መዝ119፥113፤ ያዕ4፥8፤2ጴጥ2፥14 1፥9 ማቴ23፥12 1፥10 ኢዮ14፥2፤ መዝ103፥15፤16፤ ኢሳ40፥6፣7፤ 1ቆሮ7፥31፤1ጴጥ1፥24 1፥11 ዝ102፥4፣11፤ ኢሳ40፥6፤8፣ሞት20፥12 1፥12 ቍ2፤ዘፍ22፥1፤ ዘፀ20፥6፤1ቆሮ2፥9፤ 8፥3፣9፥25፤ያዕ2፥5፤ 5፥11፤1ጴጥ3፥14 1፥14 ምሳ19፥3 1፥15 ዘፍ3፥6፤ ኢዮ15፥35፤መዝ7፥14፤ ዘፍ23፥19፤መዝ85፥12፤ 102፥27፤136፥7፤ ዳን2፥22፤ሚል3፥6፤ ዮሐ3፥27፤ያዕ3፥15፤ 17፥1ዮሐ1፥5 1፥18 ኤር2፥3፤ ዮሐ1፥13፤2ጢሞ2፥15፤ ራእ14፥4

1፥1 *ያዕቆብ*፡ በዚህ መጽሐፍ "መግቢያ" ላይ፣ "አሓፊው" የሚለውን ርእስ ይመልከቱ። *ለዐሌጋይ*፡ የሮሜ 1፥1 ማብ ይመ። *በሥራ ሁለቱ ወገኖች*፥ በመግቢያው ላይ፣ ተደራሲ የሚለውን ርእስ ይመ።

1፥2 *ወንድሞቼ*፡ ያዕቆብ በዚህ አጭር መልእክቱ ውስጥ ተደራሲያኑን 15 ጊዜ፣ "ወንድሞች" ይላቸዋል። መልእክቱ ብዙ ተግሣፅ ያዘለ ቢሆንም እንኳ፣ የሚገሥጻቸው በወንድማማች ፍቅር ነው። *መከራ*፡ እዚህ ላይ፣ "መከራ" የሚለውና በቍ 13 ላይ፣ ሲፈ ተን የሚለው ቃል በግሪኩ ሥርወ ቃላቸው አንድ ነው፤ ከቍ 2-3 ላይ ባለው ክፍል፣ መከራ የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው፣ በክርስቲያኖች ላይ ከውጪ የሚነሣውን መከራ ለማመልከት ሲሆን፣ ከቍ 13-15 ላይ ባለው ክፍል ደግሞ ኀጢአትን ለማድረግ ከውስጥ የሚመነጭን ፍላጎት ለማለፃት ጥቅም ላይ ውሉ ይገኛል።

1፥5 *ጥበብ*፡ አንድ ሰው መከራን፣ "እንደ ሙሉ ደስታ" እንዲቈጥረው (ቍ 2) የሚያስችል ማለት ነው። ጥበብ ዕውቀትን በመገብየት የሚኖር ብቻ ሳይሆን፣ መንፈሳዊ ትምህርትን ከሕይወት ጋር ማዛመድ ነው (ምሳ1፥2-4፤ 2፥10-15፤ 4፥5-9፤ 9፥10-12 ይመ)።

1፥6 *የባሕር ማዕበል*፡ ኤፌ 4፥14 ይመ።

1፥9-10 *ዝቅ ያለው ወንድም ... ባለጸጋውም*፡ ያዕቆብ ስለ ጥበብ (ቍ፥ 5-8)፣ ስለ ድኾና ስለ ባለ ጸጋ ሰው (ቍ፥ 9-11) የጻፈው ስለ መከራ በጻፈበት ክፍል መካከል (ቍ፥ 2-4 እና ቍ፥ 12) ስለሆነ፣ ከቍ፥ 5-11 ያለው ክፍል ከመከራ ጋር የሚገናኝ ሊሆን ይችላል። በድኸነት የሚሠቃይ ክርስቲያን አሁን በክርስቶስ ባገኘው መንፈሳዊ በረከትና (ራእ 2፥5 ይመ) ጌታ ዳግም ሲመጣ በሚያገኘው በረከት (ቍ፥ 9) ይመካ፣ ሀብታም ክርስ ቲያንም ዝቅ ሊያደርገው በሚችል መከራ እንኳ ይመካ (ቍ፥ 10)።

1፥12 *የተባረከ*፡ ኤር17፥7-8፤ ማቴ 5፥3-12 ይመ፣ እንዲሁም የመዝ 1፥1፤ ማቴ 5፥3፤ ራእ 1፥3 ማብ ይመ። *ሕይወት*፡ "የገኛል" የሚለው የዐረፍተ ነገሩ ማሰሪያ እንቀጽ የወደፊት ጊዜ ስለሆነ፣ የሚመለከተው ዘላለማዊ ሕይወትን ነው። *አክሊል*፡ ይህ ቃል በግሪኩ፣ ተወዳድሮ ባሸነፈ ሯጭ ወይም ድል ተጐናጸፎ ከጦር ሜዳ በተመለሰ መሪ ራስ ላይ የሚደፋን አበባ ጕንጕን የሚያመለክት ነው (2ጢሞ 4፥8፤ 1ጴጥ 5፥4 ይመ፤ ራእ 2፥10 እና ማብራሪያውን ይመ)።

1፥13 *ሲፈተን*፡ በቍ፥ 11-13 ላይ ግሡ አንድ ሰው ኀጢአትን ለመቋቋም ያለው ግብረ ገባዊ ጥንካሬ ምን ያህል እንደ ሆነ ለማወቅ የሚደረገውን ፈተና የሚያመለክት ነው (የማቴ 4፥1 ማብ ይመ)። *እግዚአብሔር ክፉ ለማድረግ አይፈተንም*፡ እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ በኀጢአት አይሳብም። ወይም *እርሱ ማንንም አይፈትንም*፤ የዘፍ 22፥1 ማብ ይመ።

1፥15፡ ሔዋን (ዘፍ 3፥6-22) እንዲሁም ዳዊት (2ሳሙ 11፥2-17) በተፈተኑ ጊዜ ደረጃ በደረጃ የተፈጸሙት ሦስት ነገሮች ምኞት፣ ኀጢአትና ሞት ናቸው።

1፥17 *በጎ ስጦታና ፍጹም በረከት ሁሉ ከሰማይ ብርሃናት አባት ከላይ ይወርዳሉ*፡ ቍ፥ 5፥3–17 ይመ። *ብርሃናት አባት*፡ እግዚአብሔር ለምድር ብርሃን የሚሰጡትን የሰማይ አካላት የፈጠራቸው እርሱ ስለሆነ፣ እነዚህ ነገሮች ቢለ ወጡ እንኳ እርሱ ጸንቶ ይኖራል።

1፥18 *ወለደን*፡ በሥጋ ሳይሆን እንደ ገና በመንፈስ መወለድን ያሳያል (ዮሐ 3፥3-8 ይመ)። *በእውነት ቃል*፡ የምሥራቹን ቃል ማለት ነው (1ጴጥ 1፥23-25 ይመ)። *በኵራት*፡ ዘሌ 23፥9-14 ይመ። በመከር ወቅት መጀመሪያ ላይ የሚገኘው የእህል ነዶ፣ ምርት እንዳለና የሚሰበሰብበትም ጊዜ ሩት እንዳለሆነ የሚያመለክት ዐይነተኛ ምልክት እንደሆነ ሁሉ፣ ቀደምት ክርስቲያኖችም ከእነርሱ በኋላ እጅግ ብዙ ሕዝብ ዳግም ልደት እንደሚያገኝ የሚያመለክቱ ናቸው።

1፥19 *ሰው ሁሉ...ለመናገር የዘገየ ይሁን*፡ ቍ፥ 26 ይመ።

1፥21 *ቃል*፡ የእግዚአብሔርን ቃል ማለት ነው።

1፥25 *ፍጹም ሕግ*፡ የክርስትና ግብረ ገባዊና ሥነ ምግባራዊ ትምህርት መሠረት ያደረገው ዐሥርቱ ትእዛዛትን

ክቶ የሚጸና፣ የሰማውን የሚያደርግና የማ
ይረሳ ሰው በሥራው የተባረከ ይሆናል።
26አንደበቱን ሳይገታ፣ ልቡን እያሳተ ሃይ
ማኖተኛ ነኝ የሚል ሰው፣ ራሱን ያታል
ላል፤ ሃይማኖቱም ከንቱ ነው። 27 በእግዚአብሔር
አብ ፊት ንጹሕና ነውር የሌለበት ሃይማኖት
ይህ ነው፤ ወላጆቻቸው የሞቱባቸውን ልጆችና
ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶች በችግራቸው
መርዳትና ከዓለም ርኵሰት ራስን መጠበቅ
ነው።

አድልዎ ማድረግ አይገባም

2 ወንድሞቼ ሆይ፤ ክቡር በሆነው በጌታ
ችን በኢየሱስ ክርስቶስ የምታምኑ እን
ደመሆናችሁ አድልዎ አታድርጉ። 2የወርቅ
ቀለበት ያደረገና ያማረ ልብስ የለበሰ ሰው
ወደ ጉባኤያችሁ ቢመጣ እንዲሁም ያደፈ
ልብስ የለበሰ ድኻ ሰው ቢገባ፣ 3ያማረ ልብስ
ለለበሰው የተለየ አክብሮት በማሳየት፣ "ለአ
ንተ የሚሆን መልካም መቀመጫ ይኸው
ልህ" ብትሉትና ድኻውን ሰው ግን፣ "አንተ
በዚያ ቁም" ወይም "ከእግሬ በታች በወለሉ
ላይ ተቀመጥ" ብትሉት፣ 4በመካከላችሁ አድ
ልዎ ማድረጋችሁ አይደለምን? ዳግሞስ
በክፉ ሐሳብ የተያዛችሁ ፈራጆች መሆና
ችሁ አይደለምን?

5የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ ስሙ፤
እግዚአብሔር በእምነት ባለጸጋ እንዲሆኑና
እርሱን ለሚወዱም ተስፋ የተሰጣቸውን መን
ግሥት እንዲወርሱ የዚህን ዓለም ድኾች
አልመረጠምን? 6እናንተ ግን ድኾችን አዋ
ረዳችሁ፤ እናንተን የሚያስጨንቋችሁ ሀብታ
ሞች አይደሉምን? ወደ ፍርድ ቤት የሚጐ
ትቷችሁስ እነርሱ አይደሉምን? 7በእናንተ
የተጠራውን ክቡር የሆነውን ስም የሚሳደቡ
እነርሱ አይደሉምን?

8በመጽሐፍ፣ "ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድ
ርገህ ውደድ" ተብሎ የተጻፈውን ክቡር ሕግ
ብትፈጽሙ መልካም እያደረጋችሁ ነው።
9አድልዎ ብታደርጉ ግን ኀጢአት መሥራ
ታችሁ ነው፤ በሕግም ፊት እንደ ሕግ ተላ
ላፊዎች ትቈጠራላችሁ፤ 10ምክንያቱም ሕግን
ሁሉ የሚፈጽም ነገር ግን በአንዱ የሚሰ
ናከል ቢኖር፣ ሁሉን እንደ ተላለፈ ይቈጠ
ራል። 11"አታመንዝር" ያለ እርሱ ራሱ "አት
ግደልም" ብሎአልና። ባታመነዝር፣ ነገር ግን
ብትገድል፣ ሕግ ተላላፊ ሆነሃል።

12ስትናገሩም ሆነ ስታደርጉ ነጻነት በሚሰ
ጠው ሕግ እንደሚፈረድባቸው ሰዎች ሁኑ፤
13ምክንያቱም ምሕረት ያላደረገ ሁሉ ያለ
ምሕረት ይፈረድበታል፤ ምሕረት በፍርድ
ላይ ያይላል።

እምነትና ሥራ

14ወንድሞቼ ሆይ፤ አንድ ሰው እምነት
አለኝ ቢል ሥራ ግን ባይኖረው ምን ይጠቅ
መዋል? እንዲህ ያለው እምነት ሊያድነው
ይችላልን? 15አንድ ወንድም ወይም አንዲት
እኅት የሚለብሱት ልብስም ሆነ የሚመገቡት
ምግብ አጥተው፣ 16ከእናንተ መካከል አንዱ፣
"በሰላም ሂዱ፤ አይብረዳችሁ፤ ጥገቡ" ቢላ
ቸው፣ ለሰውነታቸው ግን የሚያስፈልጋቸውን
ባይሰጣቸው፣ ምን ይጠቅማቸዋል? 17እንዲሁ
ሥራ የሌለው እምነት በራሱ የሞተ ነው።

1፥26 መዝ34፥13፤ 39፥1፤4፥31፥፬፡2-12፤ 1ጴጥ3፥10
1፥27 ዘጸ14፥29፤ ኢዮ31፥16፡17፡21፤ መዝ146፥9፤ ኢሳ1፥17፡23፤ ማቴ25፥36፤ሮሜ12፥21፤ ያዕ4፥12፤ዮሐ1፥4፤2፥20
2፥1 ቈላ2፥1፤ ዘሌ19፥15፤ዘዳ1፥17፤ ምሳ24፥23፤ሉቃ7፥21 10፥34፤1ቆሮ2፥8
2፥4 ዮሐ7፥24
2፥5 ኢዮ34፥19፤ ማቴ25፥34፤ሉቃ12፥21፤ 1ቆሮ1፥26-28፤ ያዕ1፥12፡16፡19፤ ራእ2፥9
2፥6 ሐሥ8፥31 16፥19፡1ቆሮ11፥22
2፥8 ዘሌ19፥18፤ ማቴ5፥43
2፥9 ቊ፡1፤ዘዳ1፥17
2፥10 ማቴ5፥19፤ ገላ3፥10፡5፥3፤ያዕ3፥2
2፥11 ዘፀ20፥13፡ 14፤ዘዳ5፥17፡18
2፥12 ማቴ16፥27፤ ያዕ1፥25
2፥13 ማቴ5፥7፤ 9፥13፤2ዮ7፥18፤32-35፤ ሉቃ6፥37
2፥14 ማቴ7፥26፤ ያዕ1፥22-25
2፥15 ማቴ25፥35፡36
2፥16 ሉቃ3፥11፤ 1ዮሐ3፥17፡18
2፥17 ቊ20፥26፤ዘሌ6

ያካተተውን የብሉይ ኪዳን ኃበረገባዊ ሕግ ነው (መዝ 19፥7 ይመ)፤ ነገር ግን ፍሉምነት ያገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ነጻ የሚያወጣውን፤ ክርስቲያን የኀጢአት ባሪያ ከሆነው ሰው ጋር ሲነጻ ጸር (ዮሐ 8፥34)፣ ኃበረገባዊ ሕግጋትን በመታዘዙ እግዚአብሔር ባዘጋጀለት ነጻነት ውስጥ በደስታ ይኖራል (2፥12 ተመልከት)።

1፥26 *ሃይማኖተኛ*፣ የሃይማኖት ውጫዊ መገለጫ የሆኑ ትን የሚያመለክት ነው፤ እነዚህም ለችግረኛ መመጽወት፣ ጸምና ምሕላ እንዲሁም ሥርዐተ አምልኮ ናቸው።

1፥27፣ ኤር 22፥16 ይመ። *ዓለም*፣ ግዑዛን ዓለም ሳይሆን፣ ሰዎች ለእግዚአብሔር ባለመታዘዝ በሚፈጸሙት ዐመፅና ክእር ሱም በመለየታቸው ምክንያት በውስጣቸው የነገሠውን ዓለም ነው (1ዮሐ 2፥15 ይመ)።

2፥1 *የምታምኑ እንደሆናችሁ አድልዎ አታድርጉ*፣ በእግዚአብሔር ዘንድ አድልዎ የለም፣ አማኞችም አድልዎ ሊያደ ርጉ አይገባም።

2፥2 *ጉባኤያችሁ*፣ ስብሰባችሁ፣ ቃሉ በገሪኩ ምኵራብ የሚል ትርጕም አለው።

2፥5-13፣ ያዕቆብ ለባለጠጎች ማድላት የማይገባ መሆኑን ለ ማስረዳት ሦስት የመቃወሚያ ሐሳቦችን ያቀርባል፦ (1) ባለጠጎች ድኾችን ማለትም ክርስቲያኖችን ያሳድዳሉ (ቊ. 5-7)፤ (2) አድ ልዎ የፍቅርን ክቡር ሕግ የሚቃረን በመሆኑ ኀጢአት ነው (ቊ. 8-11)፤ (3) አድልዎ ፍርድን ያስከትላል (ቊ. 12-13)።

2፥5 *እግዚአብሔር ... የዚህን ዓለም ድኾች አልመረጠ ምን*? ሉቃ 6፥20፤ 1ቆሮ 1፥26-31 ይመ። *መንግሥት*፣ አዲስ ልደት ያገኙ (ዮሐ 3፥3፡5) በመላት የሚገቡበት መንግሥት ነው (ማቴ 25፥34፡46)።

2፥8 *ክቡር ሕግ*፣ የፍቅር ሕግ (ዘሌ 19፥18) "ክቡር ሕግ" ይባላል፤ ምክንያቱም በሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት የሚጸናባ ቸው ሕጎች ሁሉ፣ *ሥረ መሠረታቸው* ይህ ታላቅ ሕግ ስለ ሆነ ነው። እንዲህ ላሉት የግንኙነት ሕጎች ሁሉ መነሻቸውም መድረ ሻቸውም ይህ ሕግ ነው (ማቴ 22፥36-40፤ ሮሜ 13፥8-10)።

2፥10 *ሁሉን እንደ ተላለፈ ይቈጠራል*፣ ሕጉ የእግዚአብሔር ባሕርይና ፈቃድ መግለጫ ነው፤ ስለዚህ ከሕጉ አንዲቱን ትእዛዝ መተላለፍ፣ ከእግዚአብሔር ፈቃድ መውጣትና ሕጉን ሙሉ በሙሉ መጣስ ማለት ነው (ከማቴ 5፥18-19፤ 23፥23 ጋር ያነጻ ጽሩ)።

2፥12 *እንደሚፈረድባቸው*፣ የያዕቆብን ተደራሲያን ቀድሞውኑ የመጨረሻ ዕጣ ፈንታቸውን (ዮሐ 5፥24) የሚያውቁ አማኞች ስለ ሆኑ (ቊ፡1)፣ ክፍሉ የሰውን ዕድል ፈንታ ስለሚወስነው የመጨረሻው ፍርድ የሚናገር አይደለም፤ ነገር ግን ይህ ፍርድ መጪረሻውን ለክርስቲያኖች ስለሚሰጠው ሽልማት ነው (1ቆሮ 3፥12-15፤ 2ቆሮ 5፥10፤ ራእ 22፥12)።

2፥13 *ምሕረት በፍርድ ላይ ያይላል*፣ አንድ ሰው መሓሪ ከሆነ፣ እግዚአብሔርም በፍርድ ቀን ምሕረት ያደር ግለታል (ምሳ 21፥13፤ ማቴ 5፥7፤6፥14-15፤ 18፥21-35 ይመ)።

2፥14-26፣ በቊ. 14-20፡24፡26 ላይ፣ "እምነት" የሚለው ቃል ድነት ስለሚያስገኘው እውነተኛ እምነት የተጻፈ አይደለም፤ ነገር ግን አጋንንት እንዲሚያምኑት ዐይነት (ቊ፡19)፣ ከንቱና (ቊ. 20) ሙት የሆነውን (ቊ. 26) እምነት ለማመልከት የገባ ቃል ነው። ይህ እምነት የክርስቶስን አዳኝነት ማመን ሳይሆን፣ በአእምሮ ዕውቀት ላይ የተመሠረተ ነው። ያዕቆብ ሰው በእውነ ተኛ እምነት ሳይሆን በሥራ ይድናል አላለም፤ ይልቁንም ሰው የሚጸድቀው በእምነት ብቻ ነው፤ የሚያድን እምነት ደግሞ ብቻ ውን ሳይሆን፣ ሥራን ገንዘቡ ያደረገ ነው። እውነተኛ እምነት በጎ ሥራ ይከተለዋል፤ ድነት የሚገኘው ግን ክርስቶስን በማመን ነው (ስለ መጽደቅ የበለጠ ለመረዳት የሮሜ 3፥24 ማብ ይመ)።

2፥15-16፣ ይህ እውነተኛ ስላልሆነ እምነት የቀረበው ገለጻ፣ በ1ዮሐ3፥17 ላይ እውነተኛ ስላልሆነ ፍቅር ከቀረበው ገለጻ ጋር ተጓዳኝ ነው፤ የመጀመሪያው ክፍል እውነተኛ እምነት በሥራ እንደሚገለጽ የሚያስተምር ሲሆን፣ ሁለተኛ ክፍል ደግሞ እውነ ተኛ ፍቅር ሥራን ገንዘቡ እንዳደረገ የሚገልጽ ነው።

18ነገር ግን አንድ ሰው “አንተ እምነት አለህ፤ እኔ ሥራ አለኝ” ይላል። እምነትህን ከሥራ ለይተህ አሳየኝ፤ እኔም እምነቴን በሥራዬ አሳይሃለሁ። 19አንድ እግዚአብሔር እንዳለ ታምናለህ፤ መልካም ነው፤ አጋንንትም ይህ ንኑ ያምናሉ፤ በፍርሀትም ይንቀጠቀጣሉ።

20አንተ ከንቱ ሰው! እምነት ያለ ሥራ ዋጋ የሌለው መሆኑን ለማወቅ ማስረጃ ትፈ ልጋለህን? 21አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው ላይ ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን? 22በዚህም እም ነት ከሥራው ጋር አብሮ ይሠራ እንደነበር ታያለህ፤ እምነትም በሥራ ፍጹም ሆነ። 23“አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት” የሚለው የመጽሐፍ ቃል ተፈ ጸመ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ወዳጅ ተባለ። 24እንግዲህ በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ።

25እንዲሁም ጋለሞታዪቱ ረዓብ መልእክ ተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻ ቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን? 26ከመን ፈስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ ከሥራም የተለየ እምነት የሞተ ነው።

አንደበትን መግታት

3ወንድሞቼ ሆይ፤ ከእናንተ ብዙዎች አስ ተማሪዎች አይሁኑ፤ ምክንያቱም እኛ አስተማሪዎች የሆንን የባሰ ፍርድ እንደ ምንቀበል ታውቃላችሁ። 2ሁላችንም በብዙ ነገር እንሰናከላለን፤ በንግግሩ የማይሰናከል ማንም ሰው ቢኖር እርሱ ሰውነቱን ሁሉ መቈጣጠር የሚችል ፍጹም ሰው ነው።

3ፈረሶች እንዲታዘዙልን ልጓም በአፋቸው ውስጥ ስናስገባ፤ መላ ሰውነታቸውን መምራት እንችላለን። 4ወይም መርከቦችን ተመልከቱ፤ ምንም እንኳ እጅግ ትልቅና በኀይለኛ ነፋስ የሚነዱ ቢሆኑም የመርከቡ ነጂ በትንሽ መሪ ወደሚፈልገው አቅጣጫ ይመራቸ ዋል። 5እንዲሁም ምላስ ትንሽ የሰውነት ክፍል ሆና ሳለ በታላላቅ ነገሮች ትኵራራ ለች፤ ትልቅ ጫካ በትንሽ እሳት እንዴት ተቃጥሎ እንደሚጠፋ አስተውሉ፤ 6ምላስም እንደ እሳት ናት፤ በሰውነት ክፍሎቻችን መካከል የምትገኝ የክፋት ዓለም ናት፤ ሰውነትን ሁሉ ታረክሳለች፤ ደግሞም የፍጥረትን ሩጫ ታቃጥላለች፤ ራሷም በገሃነም ትቃጠላለች።

7ማናቸውም ዐይነት እንስሳ፣ አዕዋፍ እንዲሁም በምድር ላይ የሚሳቡና፥ በባሕር ውስጥ የሚኖሩ ፍጥረታት ሁሉ መገራት ችለዋል፤ በእውም ተገርተዋል። 8ነገር ግን ምላ ስን መግራት የሚችል ማንም ሰው የለም፤ የሚገድል መርዝ የሞላባትና ዕረፍት የሌላት ክፉ ነገር ናት።

9በምላሳችን ጌታንና አብን እንባርካለን፤ በእርስዋም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩትን ሰዎች እንረግማለን። 10ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ፤ ወንድሞቼ ሆይ፤ ይህ ሊሆን አይገባም። 11ከአንድ ምንጭ ጣፋጭ ውሃና መራራ[ሀ] ውሃ ይመነጫልን? 12ወንድሞቼ ሆይ፤ በለስ ወይራን ወይንም በለስን ሊያፈራ ይችላልን? እንዲሁም ከጨው ውሃ ጣፋጭ ውሃ ሊገኝ አይችልም።

ሁለት ዐይነት ጥበብ

13ከእናንተ መካከል ጥበበኛና አስተዋይ የሆነ ሰው ማን ነው? ሥራውን ከጥበብ በሆነ በመልካም አኗኗር ያሳይ። 14ነገር ግን መራራ ቅንአትና ራስ ወዳድነት በልባችሁ ቢኖር ኵራት አይሰማችሁ፤ እውነትንም አትካዱ። 15እንዲህ ያለችዋ ጥበብ ከላይ አይደለችም፤ ነገር ግን ከምድር ከሥጋና ከአጋንንት ናት። 16ቅናትና ራስ ወዳድነት ባሉበት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ሥራ ሁሉ ይገኛሉ።

2፥18 ሮሜ7፥16፣17፤ ሮሜ3፥28፤ዕብ11፤ ያዕ3፥13
2፥19 ዘዳ6፥4፤ ማቴ8፥29፤ማር12፥29፤ ሉቃ4፥34፤1ቆሮ8፥4-6
2፥20 ቀኁ17፥26
2፥21 ዘፍ22፥9፡12
2፥22 ዕብ11፥17፤ 1ተሰ1፥3
2፥23 ዘፍ15፥6፤ 2ዜና20፥7፤ ኢሳ41፥8፤ሮሜ4፥3
2፥25 ዕብ11፥31
2፥26 ቀኁ17፥20
3፥1 ማቴ7፥1፤ሮሜ 2፥21፤ኤፌ4፥11
3፥2 1ነገ8፥46፤ መዝ39፥1፱ምሳ10፥19፤ ማቴ12፥37፤ ሮሜ3፥9-20
ያዕ1፥26፣2፥10፤ 1ጴጥ3፥10፤1ዮሐ1፥8
3፥3 መዝ32፥9
3፥5 መዝ12፥3፤41 73፥8፡9
3፥6 ምሳ16፥27፤ ማቴ5፣22፤15፥11፡18፡ 19
3፥8 መዝ140፥3፤ ሮሜ3፥13
3፥9 ዘፍ1፥26፡27፤ 1ቆሮ11፥7
3፥12 ማቴ7፥16
3፥13 ያዕ2፥18፤ 1ጴጥ2፥12
3፥14 ቀኁ16፤ 2ቆሮ12፥20፤ያዕ5፥19
3፥15 ቀኁ17፤ 1ጢሞ4፥1፤ያዕ1፥17
3፥16 ቀኁ14፤ ዳን2፥20፡21

2፥18 *ለንተ እምነት አለህ፤ እኔ ሥራ አለኝ፤* ስሕተቱ፣ “የእምነት” ክርስቲያን እና፣ የሥራ ክርስቲያን በማለት እምነትንና ሥራን ለየብቻ በተናጠል ማቅረቡ ነው። *እምነትህን ከሥራ ለይተህ አሳየኝ፤ ያዕቆብ* ይህ ምፀት እንጂ በፍጹም ሊሆን የማይችል ነገር እንደ ሆነ ይገልጻል።

2፥19 *አንድ እግዚአብሔር፣* በአይሁድ ትምህርተ ሃይ ማኖት በጣም የታወቀውና በዕብራይስጡ፣ “ሽማ” (ሰማ) የሚል አምላክ አንድ ብቻ መሆኑን የሚገልጽ የእምነት አንቀጽ ነው (ዘዳ 6፥4፤ ማር 12፥29)።

2፥21፤ ክፍሉን ከዐውዱ ነጥለን ኩተመለከትነው፣ ሰው ድኑት የሚያገኘው ውጭኑት እንጂ በሥራ አይደለም ከሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የሚቃረን ይመስላል (ሮሜ 3፥28፤ ገላ 2፥15-16)። ያዕቆብ የሚለው ግን የጽድቅ ሥራ የእውነተኛ እምነት መገለጫ እንጂ ለድኑት የሚያበቃ አይደለም፣ ለዚህ ማስረጃ አድርጎ የሚያ ቀርበው፣ “አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረ ለት” (ቁ. 23) የሚለውን ነው፤ ከዚህ ክፍል የምንማረው፣ ድድቅ ሆኖ የተቈጠረለት እምኑቱ እንጂ ሥራው አይደለም። (በዘፍ 15፥6) የሚለው። የሚያድን እምነት ሰነ ሥራን ገንዘቡ ያደረገ ነው።

2፥23 *የእግዚአብሔር ወዳጅ፣* ይህ አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ወዳጅነትና (2ዜና20፥7 ይመ) እግዚአብሔር ምን ያህል እንደ ተቀበለው የሚያስገነዝበን ነው።

2፥24 *በእምነት ብቻ ሳይሆን፣* (የ2፥14-26 ማስታወሻ ይመ)።

2፥25 *ጋለሞታዪቱ ረዓብ፣* በዚህ ስፍራ የረዓብ ስም በመል ካም የተወሳው፣ ያዕቆብ የግልሙትናን ሕይወን እንደ በጎ ነገር ስለቈጠረው ሳይሆን፣ ሰላዮቹን በመረዳድ (ኢሱ 2) የታየውን እምነት በማድነቅ ብቻ ነው (ዕብ 11፥31 ይመ)።

3፥1 *ቦሀሰ ፍርድ እንደምንቀበል፤* አስተማሪ ከሌላው ይልቅ ተጽዕኖ ማድረግ ስለሚችል፣ ያለበት ኀላፊነት የዚያኑ ያህል ከባድ ነው (ሉቃ 20፥47 ይመ፤ ኮሎቴ 23፥1-33 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥2 *ፍጹም ሰው፣* ምላስን መቈጣጠር አስቸጋሪ ስለሆነ፣ ምላ ስን መቈጣጠር የሚችል፣ ቦማጅነውም ረገድ ሕይወቱን መቈጣጠር ይችላል።

3፥6 *የክፋት ዓለም፣* ዓለም በውድቀት ገጽታዋ እንደ ምትመስለው ማለት ነው። *ራስዋም በገሃነም ትቃጠላለች፣* ይህ ከምላስ ለሚወጣው የክፋት መርዝ ምንጩ ዲያብሎስ መሆኑን የሚያመለክት ሥዕላዊ ገለጻ ነው (ዮሐ 8፥44 ይመ)። የማቴ 5፥22፤ ሉቃ 16፥23 ማብ ይመ።

3፥9 *በእግዚአብሔር አምሳል፣* ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ስለ ሆነ (ዘፍ 1፥26-27)፣ ሰውን መርገም እግዚአብሔርን እንደ መርገም ይቈጠራል (ዘፍ 9፥6 ይመ)፤ እንዲሁም የዘፍ 1፥26 ማብ ይመ።

3፥13 *ጥበበኛ፣* የ1፥5 ማብ ይመ።

3፥15 *ከላይ፤* ከእግዚአብሔር ማለት ነው (1፥5፡17፤ 1ቆሮ 2፥6-16 ይመ)።

3፥16 *ሁከትና፣* “እግዚአብሔር የሰላም አምላክ እንጂ፣ የሁከት አምላክ አይደለም” (1ቆሮ 14፥33)።

17ከሰማይ የሆነችው ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት፤ በኋላም ሰላም ወዳድ፣ ታጋሽ፣ እሺ ባይ፣ ምሕረትና መልካም ፍሬ የሞላባት፣ አድልዎና ግብዝነት የሌለባት ናት። 18የጽድቅም ፍሬ ሰላምን ለሚያደርጉ በሰላም ይዘራል።

ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ

4 በእናንተ መካከል ያለው ጦርነትና ጠብ ከየት የመጣ ነው? በውስጣችሁ ከሚዋጋ ጉት ምኞታችሁ አይደለምን? 2ትመኛላችሁ፤ ነገር ግን አታገኙም። ትገድላላችሁ፤ በብር ቱም ትመኛላችሁ፤ ልታገኙም አትችሉም። ትጣላላችሁ፥ ትዋጋላችሁ፤ አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም።

3ትለምናላችሁ ግን አትቀበሉም፤ ለራሳ ችሁ ሥጋዊ ደስታ በማሰብ በክፉ ምኞት ትለምናላችሁና።

4አመንዝሮች ሆይ፤ ከዓለም ጋር ወዳጅ መሆን የእግዚአብሔር ጠላት መሆን እንደ ሆነ አታውቁ ምን? ስለዚህ የዓለም ወዳጅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል። 5ወይስ በውስጣችን ያሳደረው መንፈስ አብ ዝቶ ይቀናል^ በማለት መጽሐፍ የተናገረው በከንቱ ይመስላችኋልን? 6ነገር ግን ጸጋን አብ ዝቶ ይሰጠናል፤ መጽሐፍም፣

"እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤
ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል"

ያለው ስለዚህ ነው።

7እንግዲህ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ፤ ዲያ ብሎስን ተቃወሙት፤ ከእናንተም ይሸሻል። 8ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ፥ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል። እናንተ ኀጢአተኞች እጃችሁን አንጹ፥ እናንተ በሁለት ሐሳብ የምትዋልሉ ልባ ችሁን አጥሩ። 9ተጨነቁ፤ አዘኑ፤ አልቅሱም። ሳቃችሁ ወደ ኀዘን፤ ደስታችሁም ወደ ትካዜ ይለወጥ። 10በጌታ ፊት ራሳችሁን አዋርዱ፤ እርሱም ከፍ ከፍ ያደርጋችኋል።

11ወንድሞች ሆይ፤ እርስ በርሳችሁ አትወነጃጀሉ፤ ወንድሙን የሚወነጅልና በወንድሙም ላይ የሚፈርድ በሕግ ላይ ክፉ ይናገራል፤ በሕግም ላይ ይፈርዳል። በሕግ ላይ ብትፈርድ ፈራጅ እንጂ ሕግን አድራጊ አይደለህም። 12ሕግን የሚሰጥና የሚፈርድ አንድ ብቻ ነው፤ እር ሱም ሊያድንና ሊያጠፋ የሚችል ነው፤ ነገር ግን በባልንጀራህ ላይ የምትፈርድ አንተ ማን ነህ?

ስለ ነገ መመካት

13እናንተ "ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህች ወይም ወደዚያች ከተማ እንሄዳለን፤ በእርሷም አንድ ዓመት እንቈያለን፤ እንነግዳለን፤ እናተርፋለ ንም" የምትሉ እንግዲህ ስሙ። 14ነገ የሚሆነውን እንኳ አታውቁም። ሕይወታችሁ ምንድን ናት? ለጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እን ፋሉት ናችሁ። 15ይልቁንም፣ "የጌታ ፈቃድ ቢሆን እንኖራለን፤ ይህን ወይም ያንን እናደ ርጋለን" ማለት ይገባችኋል። 16አሁን ግን በትዕቢታችሁ ትመካላችሁ፤ እንዲህ ያለው ትምክህት ሁሉ ክፉ ነው። 17እንግዲህ መል ካም የሆነውን ነገር ማድረግ እንዳለበት እያ ወቀ የማያደርግ ሰው ኀጢአት ያደርጋል።

ለጨካኝ ሀብታሞች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

5 እንግዲህ እናንተ ሀብታሞች ስሙ፤ ስለ ሚደርስባችሁ መከራ አልቅሱ፤ ዋይ ዋይም በሉ። 2ሀብታችሁ ሻግቶአል፤ ልብሳችሁንም ብል በልቶታል። 3ወርቃችሁና ብራችሁ ዝጎልል፤ ዝጉቱም በእናንተ ላይ ይመሰክራል፤ ሥጋችሁንም እንደ እሳት ይበላዋል፤ ለመጨ ረሻው ዘመን ሀብትን አከማችታችኋል። 4ልብ በሉ፤ አርሻችሁን ሲያጭዱ ለዋሉ ሠራተኞች ያልከፈላችሁት ደመወዝ በእናንተ ላይ ይጮኻል፤ የአጫጆቹም ጩኸት ሁሉን ቻይ

3፥17 አድልዎ፤ 2፥1-13 ይመ።

3፥18 ለሳምን ለሚያደርጉ፣ ከቍ. 16 ጋር ያነጻጽሩ። መለያየት ጽድቅን አያመጣም።

4፥2 ትገድላላችሁ፤ ጥላቻን አግዝፎ ለማሳየት የቀረበ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው።

4፥4 ለመንዘሮች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ታማኝነት የጐደ ላቸው፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ዓለምን የሚወዱ ማለት ነው። መንፈሳዊ አመንዝራነትን በተመሳሰለ አር 31፥32 ይመ። ዓለም፤ የ1፥27 ማብ ይመ።

4፥5 መጽሐፍ፤ ያዕቆብ የትኛውን መጽሐፍ ለማለት እንደፈለገ ግልጽ አይደለም መንፈስ ለብዝቶ ይቀናል፤ "በውስጣ ችን ያሳደረው መንፈስ" ሰውን የፈጠረው እግዚአብሔር መሆኑን ያመለክታል (ዘፍ 2፥7)። የሰው ልጅ በኀጢአት ከመውደቁ የተነሣ፣ መንፈሱ "ለብዝቶ ይቀናል"፤ የእግዚአብሔር ጸጋ ግን (ቍ. 6) የሰውን ትዕት ሟሸሸ ይችላል። አማራጭ ትርጕሙን ይመ።

4፥6፤ 1ጴጥ 5፥5 ይመ።

4፥7-10፤ በግሪኩ እነዚህ ቍጥሮች እያንዳንዳቸው በኀጢ አት የተሞላውን የትዕቢት ዝንባሌ ነቅሎ ለመጣል ወዲያውኑ እርምጃ እንዲወሰድ የሚጠይቁ ዐሥር ትእዛዞች ይዘዋል።

4፥7 ዲያብሎስን ተቃወሙት፤ ኤፌ 6፥11-18፤ 1ጴጥ 5፥8-9 ይመ።

4፥8 እጃችሁን አንጹ፤ የዘመነ ብሉይ ካህናት የምስክሩ ድንኳን ወዳለበት ወደ እግዚአብሔር ፊት ከመቅረባቸው በፊት እጅና እግራቸውን በኖሱ መታጠቢያ ውስጥ መታጠብ ነበረባቸው፤ ይህም ከርኩሰታቸው እንደነጹ የሚያመለክት ነበር (ዘፀ 30፥17-21)። "ንጹሕ እጅና ቅን ልብ" የሚለውን በመዝ 24፥4 ላይ ይመ።

4፥9 ተጨነቁ፣ አዘኑ፤ አልቅሱ፤ ንስሓ ግቡ ማለት ነው።

4፥10፤ ማቴ 23፥12 ይመ።

4፥11 ወንድሙን የሚወነጅል...በሕግም ላይ ይፈርዳል፤ የ2፥8 ማብ ይመ፤ እንዲሁም ዘፀ 20፥16፤ መዝ 15፥3፤ 50፥19-20፤ ምሳ 6፥16፤ 19 ይመ። በወንድም ላይ ክፉ መናገር የፍቅርን ሕግ መናቅ ነው።

5፥1 ሀብታሞች፤ እንደ 2፥2፡6 እነዚህም ሰዎች ክርስቲያኖች አይደሉም፤ ምክንያቱም እያስጠነቀቃቸው ነውና። ከቍ. 1-6 ላይ ያለው ክፍል፣ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ በአሕዛብ ላይ ከተነገሩት የፍርድ ዐዋጆች ጋር ተመሳሳይ ናቸው፤ ወይም ደግሞ ለእግዚአብሔር ሕዝብ በቀጥታ የተነገሩ ናቸው (ኢሳ 13-23፤ ኤር 46-51፤ ሕዝ 25-32፤ አሞ 1፥3-2፥16፤ ሶፎ 2፥4-15)።

5፥2 ልብሳቸሁም፣ በጥንቱ ዓለም ብልጽግና ከሚለካቸው ነገሮች አንዱ ልብስ ነበር (ሐዋ 20፥33 ይመ)።

5፥3 ዝገቱ፤ የማከማቻት ውጤት ነው፤ ይህም በስስታም ባለጠጎች ላይ የሚመሰክርባቸውና፣ የሚፈርድባቸው ነው። ለመጨ ረሻው ዘመን፤ የሐሥ 2፥17፤1ጢሞ 4፥1፤2ጢሞ 3፥1፤የዕብ 1፥1፤ የዮሐ 2፥18 ማብ ይመ።

*5 ወይም፣ እግዚአብሔር በውስጣችን እንዲኖር ሰላደረገው መንፈስ በቅናት ይመኛል፤ ወይም በውስጣችን እንዲኖረው ያደረገው መንፈስ በቅናት ይመኛል ማለት ነው።

ወደ ሆነው ጌታ ጆሮ ደርሶአል። ⁵በምድርም ላይ በምቾትና በመቀማጠል ኖራችኋል፤ ለዕርድም ቀን ልባችሁን አወፍራችኋል። ⁶እናንተን ያልተቃወሙትን ንጹሑን ሰዎች ኩንኖችኋል፤ ገድላችኋልም።

በመከራ ውስጥ መታገሥ

⁷እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ታገሡ። ገበሬ መሬቱ መልካምን ፍሬ እስከሚሰጥ ድረስ እንዴት እንደሚታገሥ፤ የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ እንዴት እንደሚጠባበቅ አስተውሱ። ⁸እናንተም እን ዲሁ ታገሡ፤ ልባችሁንም አጽኑ፤ ምክንያቱም የጌታ መምጫ ተቃርቦአል። ⁹ወንድሞች ሆይ፤ እርስ በርሳችሁ አታጕረምርሙ፤ ያለ ዚያ ይፈረድባችኋል፤ እነሆ ፈራጁ በበር ላይ ቆሞአል።

¹⁰ወንድሞች ሆይ፤ በጌታ ስም የተናገሩትን ነቢያት የመከራና የትዕግሥት ምሳሌ አድርጋችሁ ተመልከቱ። ¹¹በትዕግሥት የጸኑትን የተባረኩ አድርገን እንደምንቈጥር ታውቃ ላችሁ፤ ኢዮብ እንዴት ታግሦ እንዶ ጸና ሰምታችኋል፤ ጌታም በመጨረሻ ያደረገ ለትን አይታችኋል። ጌታ እጅግ ርኅሩኅና መሐሪ ነው።

¹²ከሁሉም በላይ ወንድሞቼ ሆይ፤ በሰማይ ወይም በምድር ወይም በማናቸውም ነገር ቢሆን አትማሉ፤ "አዎ" ቢሆን አዎ ይሁን፤ "አይደለም" ቢሆን አይደለም ይሁን፤ ያለዚያ ይፈረድባችኋል።

ከእምነት የሆነ ጸሎት

¹³ከእናንተ መካከል በመከራ ውስጥ ያለ አለ? እርሱ ይጸልይ፤ የተደሰተ አለ? የምስ ጋና መዝሙር ይዘምር። ¹⁴ከእናንተ መካከል የታመመ ሰው አለ? የቤተ ክርስቲያን ሽማ ግሌዎችን ይጥራ፤ እነርሱም በጌታ ስም ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። ¹⁵በእምነት የቀረበ ጸሎት የታመመውን ሰው ይፈው ሰዋል፤ ጌታም ያስነሥዋል፤ ኀጢአትም ሠርቶ ከሆነ፣ ይቅር ይባላል። ¹⁶ስለዚህ ኀጢአታችሁን እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ፤ ትፈወሱም ዘንድ አንዱ ለሌላው ይጸልይ። የጻድቅ ሰው ጸሎት ኀይል አለው፤ ታላቅ ነገርም ያደር ጋል።

¹⁷ኤልያስ እንደ እኛ ሰው ነበረ፤ ዝናብ እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፤ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ተኩል ዝናብ አልዘነበም። ¹⁸እንደ ገናም ጸለየ፤ ዝናብም ከሰማይ ዘነበ፤ ምድርም ፍሬዋን ሰጠች።

¹⁹ወንድሞቼ ሆይ፤ ከእናንተ አንዱ ከእው ነት ቢስትና ሌላው ቢመልሰው፣ ²⁰ይህን አስተ ውሉ፤ ኀጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልስ ሰው ነፍሱን ከሞት ያድነዋል፤ ብዙ ኀጢአትንም ይሸፍናል።

5፥5 ⁵በምድርና በማቀማጠል፤ ሉቃ 16፥19-31 ይመ። ለዕርዱ ቀን፤ የፍርድ ቀን ማለት ነው። ከፋዎቹ ባለጠጎች ስለሚመ ጣባቸው ጥፋት ፈጽሞ ደንታ እንደሌላቸውና እስከሚታረዱበት ቀንም ድረስ የሚሰቡትን የዕርድ ከብቶች ይመስላሉ።

5፥7 እንግዲህ ወደ ኋላ ሄዶ ከቍ 1-6 ጋር በማያያዝ ለመን ደርደሪያነት የገባ ቃል ነው። ክርቲያኖች በክፉ ባለጠጎች እጅ መከ ራን እየተቀበሉ ስለሆነ፣ የጌታን ዳግም ምጽአት በትዕግሥት መጠባ በቅ ይኖርባቸዋል። የሥራችሁንና የለፋችሁን ዝናብም ፤ በእኩሉል የጸደይ ዝናብ የሚዘንበው ዘር ወዲያውኑ እንደተዘራ በጥቅምትና በኅዳር ሲ ሆን፣ የበልግ ዝናም የሚዘንመው ደግሞ ከመከር በፊት በመጋቢትና በሚያዝያ ነው (ዘዳ11፥14፤ ኤር5፥24፤ ሆሴ 6፥3፤ ኢዮ 2፥24)።

5፥9 አታጕረምርሙ፤ የያዕቆብ ክርስቲያኖችንም ሆነ ክር ስቲያን ያልሆኑ ሰዎችን እንዲታገሡ ያሳስባል (ቍ. 7-8)። ፈራጁ በበር ላይ ቆሞአል፤ ይህ የክርስቶስን ዳግም ምጽአት (ቍ. 7-8 ይመ)። እንዲሁም በዚያን ጊዜ የሚሆነውን ፍርድ የሚያመለክት ነው። በኤሳያ ኬጎን ለምኃል ሮሜ13፥12፤ ዕብ 10፥25፤ጴጥሮ7፤ራእ 22፥20 አያ ሱስ በቶሎ ይመጣል የተባለውን "የመጨረሻዎቹ ቀናት" የጀመሩት አየሱስ ወደዚህ ምድር ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ነው፤ ከሚለው ትም ህርት የተነሣ ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያሉት፣ "የመጨረሻዎቹ ቀናት" (ቍ3) ስለሆኑ፣ አሁን እኛ እየኖርን ያለነው በእነዚህ ቀናት ውስጥ ነው (የዕብ 11 ማብ ይመ)። ይህ መቼ እንደሚሆን አዲስ ኪዳን የሚነግረን ነገር የለም፤ ነገር ግን የምጽአቱ አይቀሬነት አጠያያቂ ስላልሆነ፣ ክርስቲያኖች ምጽአቱን በንቃትና በአንክሮ መጠበቅ ይኖርባቸዋል። እንግዲህ ያዕቆብ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በቅርብ እንደሚሆን የገለጸው ከዚህ የተነሣ ነው።

5፥11 ኢዮብ እንዴት ታገሠ እንደ ጸና፤ ኢዮብ ታጋሽ ሰው አልነበረም (ኢዮ 31 12፥1-31 16፥1-31 21፥4)፤ ነገር ግን በመከራው ውስጥ እንቶ ቆሞአል። (ኢዮ1፥20-22፤ 2፥9-10፤ 13፥15)፤ ምንም እንኳ ኢዮ 5፥13፤ በ1ቆሮ 3፥19 ላይ ቢጠቀስም፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የኢዮብ ስም የተነሣው እዚህ ስፍራ ብቻ ነው።

5፥12 ለትማሉ፤ ይህ የያዕቆብ ቃል ክርስቶስ ስለዚህ ጕዳይ ካስተማረው ትምህርት ጋር አንድ ወይነት ነው (ማቴ 5፥33-37)። ያዕቆብ የከለከለው እግዚአብሔር ለአብርሃም እንደ ማለለት ያለውን መሐላ (ዕብ 6፥13) ወይም ቀያፋ ኢየሱስን በመ ሐላ እንደያዘው ዐይነት የሆነውን (ማቴ 26፥63-64) ወይም ጳውሎስ የተናገረውን (በሮሜ 1፥9፤ እንዲሁም 9፥1) ወይም አንድ ሰው በእግዚአብሔር ፊት የሚያደ ርገውን ዐይነት መሐላ (ዘፀ 22፥11) አይደለም። ያዕቆብ የከለከለው አንድ ሰው የንግግሩን እውነተኛነት ለማስረገጥ ሲል የእግዚአብሔ ርን ስም መጥራትን ወይም በተቀደሰ ነገር መማልን ነው።

5፥14 ሽማግሌዎች፤ የ1ጢሞ 3፥1፤ 5፥17 ማብ ይመ። ቤተ ክርስቲያን፤ የማቴ 16፥18 ማብ ይመ። ዘይት፤ እጅግ ከታወቁት ከዛንቱ ዘመን ፍቱን መድኀኒቶች መካከል አንዱ ነው (ፍቱን መድኀ ኒትነቱን በእስክንድርያ ይኖር የነበረው አይሁዳዊ ምሁር ፊሎ፣ ጵሊኒ እንዲሁም ባለ መድኀኒቱን ጋሌን ጨምሮ በየመጽሐፋቸው ላይ ገልጸዋል፤ እንዲሁም ኢሳ 1፥6፤ ሉቃ 10፥34 ይመ)። አንዳንድ ሰዎች በዚህ ላይ ያዕቆብ ዘይትን የጠቀሰው ከመድኀኒትነቱ አንጻር ነው ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ በአምነት ለሚደረግ ጸሎት ምሳሌ ሆኖ (ቍ. 15፤ ማር 6፥13 ይመ) እግዚአብሔር ለሚሰጠው ፈውስ ውጫዊ ምልክት ነው ይላሉ።

5፥17 ኤልያስ...ጸለየ በ1ነገ 17፥1፤ 18፥41-46 ላይ ኤልያስ የጸለየውን ማለት ነው። ሦስት ዓመት ተኩል (ሉቃ 4፥25 ይመ)፤ የሚለው ቍጥር በ1ነገ 18፥1 መሠረት በማጠ ጋጋት (የስባት ዓመት ገማሽ) የተገኘ ነው እና ማብራሪያውን (የ1ነገ 18፥1 ማብ ይመ፤ ከራሉ 11፥1-6 ጋር ያነጽጽሩ)።

5፥19 ከእውነት ቢስት፤ ከእውነት የራቀው ሰው አንድም ዝም ብሎ የይስሙላ ክርስቲያን የሆነ (ከዕብ 6፥4-8፤ ከ2ጴጥ 2፥20-21 ጋር ያነጽጽሩ) ወይም በንስሓ መመለስ የሚያስፈልገው በኀጢአት የወደቀ ክርስቲያን ሊሆን ይችላል። በቍ. 20 ላይ የተጠቀሰው ሞት የደስሙላ ክርስቲያን ስተነሳው "ሁለተኛ ሞት" (ራእ 21፥8) ሊሆን። ለጊዜው በኀጢአት ለወደቀው ክርስቲያን ግን የሥጋ ሞት ነው (ከ1ቆሮ 11፥30 ጋር ያነጽጽሩ። የ1ዮሐ 5፥16 ማብ ይመ።

5፥20 ብዙ ኀጢአትንም ይሸፍናል፤ ከእውነት የራቀው ሰው ቢመለስ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ያገኛል።

5፥5 ¹በሬ...ጌታ፤ የዘፍ 17፥1፤ የ1ሳሙ 1፥3 ማብ ይመ።

5፥5 ²በምቾትና በማቀማጠል፤ ሉቃ 16፥19-31 ይመ። ለዕርዱ ቀን፤ የፍርድ ቀን ማለት ነው። ከፋዎቹ ባለጠጎች ስለሚመ ጣባቸው ጥፋት ፈጽሞ ደንታ እንደሌላቸውና እስከሚታረዱበት ቀንም ድረስ የሚሰቡትን የዕርድ ከብቶች ይመስላሉ።

5፥7 ³እንግዲህ ወደ ኋላ ሄዶ ከቍ 1-6 ጋር በማያያዝ ለመን ደርደሪያነት የገባ ቃል ነው። ክርቲያኖች በክፉ ባለጠጎች እጅ መከ ራን እየተቀበሉ ስለሆነ፣ የጌታን ዳግም ምጽአት በትዕግሥት መጠባ በቅ ይኖርባቸዋል። የሥራችሁንና የለፋችሁን ዝናብም የሚዘንመው ደግሞ ከመከር በፊት በመጋቢትና በሚያዝያ ነው (ዘዳ11፥14፤ ኤር5፥24፤ ሆሴ 6፥3፤ ኢዮ 2፥24)።

5፥9 ⁴አታጕረምርሙ፤ የያዕቆብ ክርስቲያኖችንም ሆነ ክርስ ቲያን ያልሆኑ ሰዎችን እንዲታገሡ ያሳስባል (ቍ. 7-8)። ፈራጁ በበር ላይ ቆሞአል፤ ይህ የክርስቶስን ዳግም ምጽአት (ቍ. 7-8 ይመ)። እንዲሁም በዚያን ጊዜ የሚሆነውን ፍርድ የሚያመለክት ነው። በኤሳያ ኬጎን ለምኃል ሮሜ13፥12፤ ዕብ 10፥25፤ጴጥሮ7፤ራእ 22፥20 አያ ሱስ በቶሎ ይመጣል የተባለውን "የመጨረሻዎቹ ቀናት" የጀመሩት አየሱስ ወደዚህ ምድር ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ነው፤ ከሚለው ትም ህርት የተነሣ ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያሉት፣ "የመጨረሻዎቹ ቀናት" (ቍ3) ስለሆኑ፣ አሁን እኛ እየኖርን ያለነው በእነዚህ ቀናት ውስጥ ነው (የዕብ 11 ማብ ይመ)። ይህ መቼ እንደሚሆን አዲስ ኪዳን የሚነግረን ነገር የለም፤ ነገር ግን የምጽአቱ አይቀሬነት አጠያያቂ ስላልሆነ፣ ክርስቲያኖች ምጽአቱን በንቃትና በአንክሮ መጠበቅ ይኖርባቸዋል። እንግዲህ ያዕቆብ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በቅርብ እንደሚሆን የገለጸው ከዚህ የተነሣ ነው።

5፥11 ⁵ኢዮብ እንዴት ታገሠ እንደ ጸና፤ ኢዮብ ታጋሽ ሰው አልነበረም (ኢዮ 31 12፥1-31 16፥1-31 21፥4)፤ ነገር ግን በመከራው ውስጥ እንቶ ቆሞአል። (ኢዮ1፥20-22፤ 2፥9-10፤ 13፥15)፤ ምንም እንኳ ኢዮ 5፥13፤ በ1ቆሮ 3፥19 ላይ ቢጠቀስም፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የኢዮብ ስም የተነሣው እዚህ ስፍራ ብቻ ነው።

5፥12 ⁶ለትማሉ፤ ይህ የያዕቆብ ቃል ክርስቶስ ስለዚህ ጕዳይ ካስተማረው ትምህርት ጋር አንድ ወይነት ነው (ማቴ 5፥33-37)። ያዕቆብ የከለከለው እግዚአብሔር ለአብርሃም እንደ ማለለት ያለውን መሐላ (ዕብ 6፥13) ወይም ቀያፋ ኢየሱስን በመ ሐላ እንደያዘው ዐይነት የሆነውን (ማቴ 26፥63-64) ወይም ጳውሎስ የተናገረውን (በሮሜ 1፥9፤ እንዲሁም 9፥1) ወይም አንድ ሰው በእግዚአብሔር ፊት የሚያደ ርገውን ዐይነት መሐላ (ዘፀ 22፥11) አይደለም። ያዕቆብ የከለከለው አንድ ሰው የንግግሩን እውነተኛነት ለማስረገጥ ሲል የእግዚአብሔ ርን ስም መጥራትን ወይም በተቀደሰ ነገር መማልን ነው።

5፥14 ⁷ሽማግሌዎች፤ የ1ጢሞ 3፥1፤ 5፥17 ማብ ይመ። ቤተ ክርስቲያን፤ የማቴ 16፥18 ማብ ይመ። ዘይት፤ እጅግ ከታወቁት ከዛንቱ ዘመን ፍቱን መድኀኒቶች መካከል አንዱ ነው (ፍቱን መድኀ ኒትነቱን በእስክንድርያ ይኖር የነበረው አይሁዳዊ ምሁር ፊሎ፣ ጵሊኒ እንዲሁም ባለ መድኀኒቱን ጋሌን ጨምሮ በየመጽሐፋቸው ላይ ገልጸዋል፤ እንዲሁም ኢሳ 1፥6፤ ሉቃ 10፥34 ይመ)። አንዳንድ ሰዎች በዚህ ላይ ያዕቆብ ዘይትን የጠቀሰው ከመድኀኒትነቱ አንጻር ነው ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ በአምነት ለሚደረግ ጸሎት ምሳሌ ሆኖ (ቍ. 15፤ ማር 6፥13 ይመ) እግዚአብሔር ለሚሰጠው ፈውስ ውጫዊ ምልክት ነው ይላሉ።

5፥17 ⁸ኤልያስ...ጸለየ በ1ነገ 17፥1፤ 18፥41-46 ላይ ኤልያስ የጸለየውን ማለት ነው። ሦስት ዓመት ተኩል (ሉቃ 4፥25 ይመ)፤ የሚለው ቍጥር በ1ነገ 18፥1 መሠረት በማጠ ጋጋት (የስባት ዓመት ገማሽ) የተገኘ ነው እና ማብራሪያውን (የ1ነገ 18፥1 ማብ ይመ፤ ከራሉ 11፥1-6 ጋር ያነጽጽሩ)።

5፥19 ⁹ከእውነት ቢስት፤ ከእውነት የራቀው ሰው አንድም ዝም ብሎ የይስሙላ ክርስቲያን የሆነ (ከዕብ 6፥4-8፤ ከ2ጴጥ 2፥20-21 ጋር ያነጽጽሩ) ወይም በንስሓ መመለስ የሚያስፈልገው በኀጢአት የወደቀ ክርስቲያን ሊሆን ይችላል። በቍ. 20 ላይ የተጠቀሰው ሞት የደስሙላ ክርስቲያን ስተነሳው "ሁለተኛ ሞት" (ራእ 21፥8) ሊሆን። ለጊዜው በኀጢአት ለወደቀው ክርስቲያን ግን የሥጋ ሞት ነው (ከ1ቆሮ 11፥30 ጋር ያነጽጽሩ። የ1ዮሐ 5፥16 ማብ ይመ።

5፥20 ¹⁰ብዙ ኀጢአትንም ይሸፍናል፤ ከእውነት የራቀው ሰው ቢመለስ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ያገኛል።

---

¹⁵5 ወይም ለድኀስ